በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

ሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ ኮሙኒኬሽንና ጋዜጠኝነት ኮሌጅ፣ የአማርኛ ቋንቋ ሥነ-ፅሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል የድህረ-ምረቃ መርሃ-ግብር


# የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች የመጻፍ ክሂል ብቃት ትንተና

## (በቀርሳ ማሊማ ወረዳ፣በሌማን ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተተኳሪነት)


በየነች ቡሩሴ

አማካሪ፡-ጌታቸው አዱኛ (ዶ/ር)



መስከረም 2016 ዓ/ም

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

**በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ**

**ሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ ኮሙኒኬሽንና ጋዜጠኝነት ኮሌጅ፣ የአማርኛ ቋንቋ ሥነ-ፅሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል የድህረ-ምረቃ መርሃ-ግብር**

# የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች የመጻፍ ክሂል ብቃት ትንተና

**(በቀርሳ ማሊማ ወረዳ፣በሌማን ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተተኳሪነት)**

**በየነች ቡሩሴ**

**አማካሪ፡-ጌታቸው አዱኛ (ዶ/ር)**

**መስከረም 2016 ዓ/ም**

**አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ**

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

በሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ ኮሙኒኬሽንና ጋዜጠኝነት ኮሌጅ፣ የአማርኛ ቋንቋ ሥነ-ፅሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል የድህረ-ምረቃ መርሃ-ግብር

ለአማርኛ ቋንቋ ማስተማር ኤም.ኤ.ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት

# የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች የመጻፍ ክሂል ብቃት ትንተና

(በቀርሳ ማሊማ ወረዳ፣በሌማን ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተተኳሪነት)

በየነች ቡሩሴ

የፈታኝ ቦርድ አባላት

የአማካሪ ስም____________________ ፊርማ______________ ቀን__________

የፈታኝ ስም____________________ ፊርማ______________ ቀን__________

የፈታኝ ስም____________________ ፊርማ______________ ቀን__________

# ምስጋና

በቅድሚያ በነገሮች ሁሉ ለረዳኝ ለልዑል እግዚአብሔር ምስጋና ይገባዋል፡፡ በመቀጠል ከጥናቱ ጀምሮ እስከፍፃሜ ድረስ ፅሑፉን በማንበብና ተፈላጊውን መልክ በማስያዝ ድጋፋቸው ያልተለየኝ ለአማካሪዬ ዶ/ር ጌታቸው አዱኛልባዊ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

እዚህ ደረጃ ላይ እንድደርስ ውድ ጊዜውን በመስጠት ከጎኔ ሆኖ የሚያስፈልገኝን ሁሉ አሟልቶ እገዛ ላደረገልኝ ለመምህር ስንታየው ወዳጄ ምስጋናዬ ከልብ ነው፡፡

ይህን ጥናታዊ ጽሁፍ በምሰራበት ወቅት የገንዘብ ድጋፍ ላደረገልኝ ለአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ምስጋናዬ ከፍ ያለ ነው፡፡በትምህርት ቆይታዬ እውቀታቸውን ላካፈሉኝና ምክራቸውን ለለገሱኝ ለአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ መምህሮቼም ምስጋናዬ ይድረሳቸው፡፡

ጥናታዊ ፅሑፉን ለመስራት መረጃ በምሰበስብበት ጊዜ ከፍተኛ ትብብር ላደረጉልኝ የሌማን ሁለተኛ ደረጃ ትምህርትቤት ዋና ርእሰመምህር ንጉሴ አራርሶና ምክትል ርእሰመምህር ተሊላ ገብሬ እንዲሁም የአማርኛ ቋንቋ መምህራንና ተማሪዎችን አመሰግናለሁ፡፡

ጥናታዊ ጽሁፍ በምፅፍበት ወቅት የሞራል ድጋፍ ላደረጉልኝ በስም ያልጠቀስኳቸው ቤተሰቦቼና ጓደኞቼን በሙሉ አመሰግናለሁ፡፡

# የይዘት ማውጫ ገጽ

**ጥዘቶች** **ገጽ**

ምስጋና ............ i

አጠቃሎ ............ v

ምዕራፍ አንድ ............ 1

መግቢያ ............ 1

1.1.የጥናቱ ዳራ ............ 1

1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ............ 4

1.3. የጥናቱ ዓላማ ............ 4

1.4. የጥናቱ መሪ ጥያቄዎች ............ 5

1.5. የጥናቱ ጠቀሜታ ............ 5

1.6. የጥናቱ ወሰን ............ 6

ምዕራፍ ሁለት ............ 7

ክለሳ ድርሳናት ............ 7

2.1 መጻፍን የማስተማር ዘዴ ............ 7

2.2 ዘውጋዊ የመጻፍ ክሂል ማስተማርያ ዘዴ ............ 10

2.3 የመጻፍ ክሂል ትምህርት ዘውጋዊ አቀራረብ ............ 12

2.4 ዘውጋዊ የመጻፍ ክሂል ትምህርት አቀራረብ ንድፈ ሀሳቦች ............ 14

2.5 ዘውጋዊ የመፃፍ ክሂልን ማስተማርያ አቀራረብ ጠቀሜታዎች ............ 14

2.6 ዘውግ ተኮር የመጽሀፍ ክሂል አቀራረብ ባህሪ ............ 16

2.7መጻፍን በማስተማር ወቅት የዘውግ እና የሂደት ተኮር አቀራረቦች ጥምረት ............ 18

2.8 የዘውግና የሂደት ተኮር የመጻፍ ትምህርት አቀራረብ የክፍል ውስጥ አተገባበር ............ 19

2.9 ንድፈ ሀሳባዊ ቅኝት ............ 22

ምዕራፍ ሦስት ............ 23

የጥናቱ ንድፍና ዘዴ ............ 23

3.1. የጥናቱ ንድፍ ............ 23

3.2. የተጠኚዎች አመራረጥ ............ 23

3.2.1 የትምህርት ቤት ናሙና አመራረጥ ............ 23

3.2.2. የክፍል ደረጃ ናሙና አመራረጥ ............ 24

3.2.3.የተማሪ ናሙና አመራረጥ ........ 24
3.3.የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ........ 24
3.3.1 ምልከታ ........ 24
3.3.2 የጽሁፍ መጠይቅ ........ 25
3.3.3 ቃለመጠይቅ ........ 25
3.4 የመረጃ መተንተኛ ዘዴዎች ........ 25
ምዕራፍ አራት ........ 27
የመረጃና የጥናቱ ውጤት ትንተና ........ 27
4.1.የትምህርት ይዘት የመጻፍ ክሂልን ለማስተማር ያለው እገዛ ........ 27
4.1.1.በክፍል ምልከታ የተገኘው መረጃ ........ 27
4.2.የተተኳሪ መምህራን ዳራዊ መረጃ ........ 29
4.2.1 መምህራን በቋንቋ ትምህርት የመጻፍ ክሂል አቀራረብ ላይ ያላቸው ግንዛቤ እና እውቀት ........ 29
4.2.2 ለመምህራን ከቀረቡት ቃለ-መጠይቅ የተገኘ ምላሽ ........ 30
4.3.የመምህራን የመፃፍ ክሂል ትምህርት አቀራረብ ........ 31
4.3.1.ከምልከታ የተገኘ መረጃ ትንተና ........ 32
4.3.2 ለመምህራን ከቀረበው ቃለመጠይቅ የተገኘ መረጃ ........ 33
4.4.መምህራን የመፃፍ ክሂልን ለማስተማር የሚጠቀሙባቸው ብልሃቶች ........ 33
4.4.1 ከክፍል ምልከታ የተገኘ መረጃ ........ 34
4.4.2. ለመምህራን ከቀረበ ቃለመጠይቅ የተገኘ መረጃ ........ 36
4.4.3. ለተማሪዎች ከቀረበ የፅሁፍ መጠይቅ የተገኘ መረጃ ........ 38
4.5.መምህራን የመጻፍ ክሂሎትን የማሳደግ ሚና ........ 40
4.6 መምህራን የመጻፍ ክሂሎትን ለማስተማር ተግባራቸውን በአግባቡ ስለመወጣታቸው ........ 42
4.6.1 ከምልከታ የተገኘ መረጃ ........ 42
4.6.2.የመምህራንን ሚና እና ተግባር ለማወቅ ለመምህራን ከቀረበው ቃለ መጠይቅ የተገኘ መረጃ ........ 43
4.6.3 ለተማሪዎች ከቀረበው የጸሑፍ መጠይቅ የተገኘ መረጃ ........ 44
4.7 ተማሪዎቸ የመጻፍ ክሂልን ለመማርና ለመጠቀም ያላቸው ፍላጐት ........ 45
4.7.1 ከምልከታ የተገኘ መረጃ ትንተና ........ 45
4.7.2 ለተማሪዎች ከቀረቡት የፅሁፍ መጠይቅ የተገኘ መረጃ ትንተና ........ 47

4.8. ተማሪዎች በመጻፍ ክሂል ትምህርት ወቅት ሚናቸውንና ተግባራቸውን በአግባቡ ስለመወጣታቸው....47
4.9. የመጻፍ ክሂልን ትኩረት ሰጥቶ ለማቅረብ እንቅፋት የሆኑ ጉዳዮች....48
4.10. የጥናቱ ግኝት ማብራሪያ ....50
ምዕራፍ አምስት ....51
ማጠቃለያና የመፍትሔ ሃሳቦች....51
5.1.ማጠቃለያ ....51
5.2.የመፍትሄ ሐሳቦች ....53
ዋቢ ምንጮች ....55
አባሪዎች ....59
ማረጋገጫ....72

# አጠቃሎ

የዚህ ጥናት ዋና አላማ በቀርሳ ማሊማ ወረዳ በሌማን ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች የመጻፍ ክሂል ብቃታቸው ምን ላይ እንደሚገኝ መመርመር ነው፡፡ይህ አላማ ግብ መች እንዲሆን ጥናቱ በክፍል ውስጥ የመጻፍ ክሂል መቅረብ ባለበት ሁኔታ ቀርቧል?እንዲሁም መምህራን የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል ብቃት ለማሳደግ የክፍል ውስጥ አተገባበር ምን ያህል በሚገባ ቀርቧል?የሚሉ መሪ ጥያቄዎችን ይዞየተነሳ ነው፡፡ይህ ጥናት በኦሮሚያ ክልል በደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞን በቀርሳማሊማ ወረዳ በሚገኝ በሌማን ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ በመማርናማስተማር ስራ ላይ በተሰማሩት የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን እናተማሪዎች ላይ ብቻ የተወሰነ ነው፡፡ በዚህ ትምህርትቤት በሚገኙ መምህራን የአላማ ተኮር ስልትን በመጠቀም የክፍል ምልከታ ፣ቃለመጠይቅ እና የጽሁፍ መጠይቅ መረጃ ለመሰብሰብ ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡ የተሰበሰቡት መረጃዎች በአሃዝ እና በፐርሰት ከተሰሉ በኋላ በሰንጠረዥ በፈርጃቸው ተደራጅተው ተተንትነዋል፡፡የተገኘው ውጤት አንዱ መምህር ክህሉን ትኩረት ሰጥቶ የሚያስተምር እና የሚያቀርብ ሲሆን አንደኛዋ መምህርት በዚህ መልኩ እያቀረበች እንዳልሆነ እና የጥቂት ተማሪዎች ተነሳሳሽነትም ከፍተኛ ሲሆን የአብዛኛዎቹግን ዝቅተኛ ነው፡፡

# ምዕራፍ አንድ

# መግቢያ

## 1.1. የጥናቱ ዳራ

መጻፍ ሥዕላዊ ትዕምርቶችን ፈጥሮ በወረቀት ወይም በሌላ ጠፍጣፋ ገፅ ላይ ከማስፈር ይበልጥየሚተላለፈውንፅንሰ ሀሳብም ያካተተ ነው፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ የምንፅፋቸው ዐረፍተ ነገሮች እርስ በእርሳቸው የሀሳብ ቁርኝት ያላቸው፣ተጠይቃዊ የሆኑ፣ፍሰታቸውን የጠበቁ መሆን አለባቸው፡፡

መጻፍ እንደመናገር ሁሉ በተወለዱበት የመጀመሪያዎቹ ጥቂት ዓመታት ውስጥ የምናውቀው ወይም በራሱ ጊዜ ጠብቆ ቀን ቆጥሮ የሚመጣ አይደለም፡፡ ነገር ግን ፅህፈት ያንድን ቋንቋ የንግግር ድምጾች የሚወክሉ ምልክቶችን በመቅረፅ የቋንቋ ተናጋሪዎች በተስማሙበትና በለመዱት ስርዓት ትርጉም እንዲሰጡ አገጣጥሞ ቃል በመመስረት፣ ቀጥሎም ቃላትን በሐረግ፣ ሐረጋትን በዓረፍተነገር፣ ዓረፍተነገሮችን በአንቀፅ በማቀናበር የሚካሄድ ክሂል ነው፡፡

እንግዲህ ይህን የነገሮች ቅንብር ተጠቅመን ሀሳባችንን እንገልፅበታለን፣ መረጃ እናስተላልፍበታለን፣ መረጃ እናስቀምጥበታለን፡፡ በመሆኑ ፅህፈት ፀሐፊው ባለበት ወይም በሌለበት ቦታ መልዕክት የሚተላለፍበት በመሆኑ ድርጊቱ ይበልጥ ትኩረትን የሚፈልግና ጥንቃቄ የሚሻ ነው፡፡ መልዕክቱ በንግግር ወይም በአካል እንቅስቃሴ ሊታጀብም ላይታጀብም ይችላል፡፡ ይህንን አስመልክቶ UR (1996) መጻፍ ሁሌም ዘላቂነት፣ ግልፅነት፣ ጥሩ አደረጃጀትና የቋንቋ መደበኛነት ሊኖረው እንደሚገባ አበክረው ይገልጻሉ፡፡ ለዚህ እንደምክንያት የሚገልፁት ፀሀፊው እና አንባቢው ግንባር ለግንባር ፀሀፊው ለአንባቢው የሚያስረዳው ነገር ስለማይኖር ነው ይላሉ፡፡

የመጻፍ ክሂል ኢ-መደበኛ በሆነ መልኩ ለቋንቋ ተጋላጭ በመሆን ብቻ የሚዳብር ሳይሆን መደበኛ በሆነ የትምህርት አውድ ውስጥ በመገኘት የሚጎለብት ነው፡፡ ለዚህ ነው የሰው ልጆች ሀሳባቸውን በፅሁፍ ቀርፆ ለማቆየትም ሆነ ለሌሎች ለማስተላለፍ ይችሉ ዘንድ የመጻፍ ክሂል ትምህርት ያስፈልጋቸዋል የሚባለው፡፡ በተለይ በሁለተኛ ቋንቋ ለመዳ ሂደት ፅህፈትን ተጠቅሞ ሐሳብን ለመግለፅ ሲሞክር የታላሚውን ቋንቋ ሰዋሰው ህግና ማህበራዊ ቋንቋ አጠቃቀምን ጠንቅቆ ማወቅ ይገባዋል Brown (1994)፡፡

ታድያ በመማር ብቻ ከምናገኛቸው ክሂሎች አንዱ መጻፍ ነው፡፡ በዚህ ክሂል በመጠቀም ንግግር በሚደረግበት ግዜ ዋና ዋና ነጥቦችን በመያዝ ተናጋሪው እንዳይረሳና የንግግር ፍሰቱ የተጠበቀ እና እንዳይቆራረጥ ነገሮችን በሥርዓት አስቀድሞ አደራጅቶ ለመያዝ ያስችላል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ለምርምር ስራ አጋዥ ኃይል ነው፡፡ ማንኛውንም የምርምር ስራ ለማከናወን የፅህፈትና የንባብ ክሂሎች በተቻለ መጠን ማዳበር ወሳኝነት አለው፡፡ ይህም በምርምር ሂደቱ የተደረሰባቸውን የተለያዩ ግኝቶችን ማወቅና መረዳት የሚቻለው በማንበብ ሲሆን የራሳችን የፈጠራ ስራ ግኝት የሆኑትን ደግሞ ለሌሎች የምናስተላልፈው በጽሕፈት አማካኝነት ነው፡፡

የፅህፈት ትምህርት ውስብስብ በመሆኑ አብዛኛዎቹ የቋንቋ ተማሪዎች የአፍመፍቻም ይሁን የሁለተኛ ቋንቋ ትምህርታቸውን አጠናቀው ከትምህርት ቤት ሲወጡ በቂ የሆነ የፅህፈት ችሎታ አያዳብሩም፡፡ ይህ ችግር በከፍተኛ ትምህርት ተቋሞች ጭምር ጎልቶ የሚታይ በመሆኑ ተማሪዎች በኮሌጅ በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ተካተው የሚሰጡ የድርሰት ትምህርትን ከፍተኛ ፍራቻና ጭንቀት ስለሚመለከታቸው በእጅጉ አስቸጋሪና ረዘም ያለ ጊዜን የሚጠይቁ ሆነው ይታያሉ Richards (1990)Nunan(1989) ፡፡

የመጻፍ ክሂል በትምህርት የሚገኝ በመሆኑ የአፈ-ፈትነት ማህበራዊ መነሻ አይወስነውም፡፡ ስለሆነም በመጻፍ አማካኝነት የሚደረግ ተግባቦት የትምህርት ውጤት በመሆኑ ከፊደል አጣጣል ጀምሮ እስከ አንቀፅ አወቃቀር በየደረጃው መማር ያስፈልጋል፡፡ የመጻፍን ክሂል በትክክል ለመተግበር የንግግር ድምጾችን ወካይ በሆኑ ምልክቶች በአግባቡ ጥቅም ላይ ማዋል ይጠቅማል፡፡ ምክንያቱም ሀሳብ በጽሑፍ ለማስተላለፍ ሲፈለግ እንደ ማዳመጥና መናገር ክሂሎች አጋዥ ስሜታዊና አካላዊ መግለጫዎች (የፊት ገፅታ የድምፅ ቅላጼ፣ ድግግሞሽ፣ የሰውነት እንቅስቃሴ ወዘተ) ጽሑፍን አጅበው ስለማይቀርቡ መልዕክቱን በትክክል ለማስተላለፍ ይቻል ዘንድ በቋንቋ አጠቃቀም፣ በሃሳብ አደረጃጀት፣ በቃላት አመራረጥና አሰላለፍ በኩል በጥንቃቄና በማያሻማ መልኩ ተዘጋጅቶ መቅረብ ይጠበቅበታል Byrne(1991) እና Hedge (1988)፡፡

Heaton (1991) እንደሚገልጸው የመጻፍ ክሂል ማስተማር በመደበኛ ትምህርት ሊዳብሩ የሚችሉ የተለያዩ ችሎታዎችን ለማዳበር እንደሚያስችል ያስረዳሉ፡፡ ይህም ማስተላለፍ ለሚፈለገው ጭብጥ ተገቢ የሆኑ የአጻጻፍ ስልቶች፣ የሀሳብ አደረጃጀትን፣ የሰዋሰው ስርዓትንና ሌሎችን የሚጠይቅ ተግባር መሆኑ ተማሪዎች እነዚህን ተግባራት በማከናወን የመጻፍ ችሎታቸውን እንዲያዳብሩ የሚያስችል ነው፡፡

በሀገራችን ውስጥ በሚገኙ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በመጻፍ ክሂል ላይ ጥናታቸውን ያደረጉ የመጻፍ ክሂል ማስተማርያ ዘዴ የክፍል ውስጥ አተገባበር ለመመርመር ጥናታቸውን አካሂደዋል፡፡ ከእነዚህ አጥኚዎች ማረው (1987)፣ ስዩም (1988) እና ሰለሞን (1991) ይገኙበታል፡፡ እነዚህ ጥናቶች የፅህፈት ክሂል ትምህርትን ለማስተማር በመማርያ መፃህፍት ውስጥ የቀረቡት ይዘቶች አደረጃጀት ብቁ ሆኖ አለመገኘት፣ የይዘቶችና ክንውኖች የማስተማርያ ዘዴ ትግበራ ተማሪውን የሚያበረታታ ሆኖ ያለመቅረብና የመምህራን ፅህፈትን የማስተማርያ ዘዴያቸው የተማሪዎችን የመጻፍ ስትራቴጂ ብቃት የሚያሳድግ ሆኖ አለመገኘቱን ገልፀዋል፡፡ በአንጻሩ የተማሪዎች የጽህፈት ብቃት ለማሳደግ በቡድን ድርሰት ማጻፍ፣ እርማትና ጽህፈትን በሂደታዊ ዘዴ ማስተማር ለክሂሉ መዳበር ጠቀሜታዎች የጎላ ሆነው መገኘታቸውን የጠቆሙ ጥናቶች ናቸው፡፡

በተለይ ተማሪዎች ዕውቀታቸውን፣ ችሎታቸውን፣ እንዲሁም የትምህርት ፍላጎታቸውን ለማሳደግ የሚያስችሉ በክፍል ውስጥ በተወሰነ ጥረት ብቻ ሳይሆን ከክፍል ውጭም በሚደረግ የግልና የቡድን ጥረት በእጅጉ ያስፈልጋል፡፡ ይሁን እንጂ በተጨባጭ እንደሚታየው ብዙ ተማሪዎች ከትምህርት ክፍለ ጊዜያትና ውጭ ከትምህርት ቅጥር ጊቢ ውስጥም ሆነ ከቤታቸው ውስጥ ትርፍ ጊዜያቸውን ተጠቅመው ከሚጠበቀው ውጤት ላይ ለመድረስ ተገቢውን ጥረት ሲያደርጉ አይታይም፡፡

ለዚህም እንደ አስረጂነት መጥቀስ የሚቻለው ብዙ መምህራን ተማሪዎቻቸውን በአብዛኞቹ የትምህርት አይነት የተሰጣቸውን የቤት ስራዎች ሳይሰሩ ወደትምህርት ቤት እንደሚመጡና በሁኔታው እጅግ የተማረሩ መሆናቸውን በተለያየ ትምህርት ነክ ስብሰባዎች ላይ መናገራቸው ነው፡፡ ይህ ችግር የተማሪዎችን ውጤት ለማሳደግ ያቀዱትን እቅድ ተግባራዊ ማድረግ እንዳላስቻላቸው በተለያዩ መድረኮች ላይ ሲናገሩ ይታያል፡፡ ከብዙዎቹ መምህራን እንደሚደመጠው ችግሩ የቤት ሥራዎችን ባለመስራት ብቻ የተወሰነ ሳይሆን በክፍል ውስጥ የተማሪዎች ተሳትፎ እጅግ ዝቅተኛ እንደሆነ የሚገልፅ ነው፡፡

ከዚህ የምንረዳው የተማሪዎቻቸውን ለመማር ከሚያደርጉት ጥረት አንፃር ሲታይ ተነሳሳሽነታቸው ዝቅተኛ መሆን ነው፡፡ ከላይ የቀረቡትን ሀሳቦች መነሻ በማድረግ በሌማን ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ የመጻፍ ክሂላቸውን እንዴት ማሳደግ እንደሚቻል ጥናትና ምርምር ተካሂዷል፡፡

## 1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

በአፍ መፍቻም ሆነ በሁለተኛ ቋንቋ መጻፍን መማር ለተማሪዎች አስቸጋሪ ከመሆኑም በላይ ከመካከላቸው መጻፍን በሚገባ የሚጽፉት ጥቂቶች መሆናቸው ይስተዋላል፡፡ከዚህም የተነሳ በጽሁፍ ሀሳብን መግለጽ ለብዙ ተማሪዎች አስቸጋሪ ሂደት ተደርጎ የሚታይ ከመሆኑም በላይ በጣም የሚያስጨንቃቸው መሆኑን Richards(1990) ያስገነዝባሉ፡፡ሆኖም ግን በአሁኑ ጊዜ ተማሪዎች ለቋንቋ ትምህርት ያላቸው ተነሳሳሽነት እና ተሳትፎዋቸው ዝቅተኛ መሆን በጉልህ ይታያል፤ከዚህም በመነሳት አራቱን የቋንቋ ክሂሎች ከአቅም እና ከጊዜ አንፃር ማጥናት የሚቸግር መሆኑን በመረዳት በመጻፍ ክሂል ላይ ጥናት ማካሄድ አስፈልጓል፡፡

ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋንም ሆነ ሌሎች የትምህርት አይነቶችን ለመማር ያላቸው ተነሳሳሽነት አነስተኛ ቢሆንም ሁሉንም የመማር ችግር በአንድ ጊዜና በአንድ ሰው ተጠንቶ ችግሮቹን ለመፍታት የማይወጡት ዳገት ነው፡፡ ስለዚህ ይህ ጥናት የመጻፍ ክሂል ከአራቱ የቋንቋ ክሂሎች አንዱ ሆኖ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ በመሆኑ የመጻፍ ክሂል በተፈለገው መጠን በአሁኑ ጊዜ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በመጻፍ ክሂል ላይ ያላቸውን የመጻፍ ብቃት አነስተኛ በመሆኑ ከላይ ከተባሉት ማሳያዎች በመረዳት የሚታየውን የተማሪዎችን የመጻፍ ችግር ለመፈተሽ ጥናቱን ማካሄድ አስፈልጓል፡፡

## 1.3. የጥናቱ ዓላማ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በቀርሳ ማሊማ ወረዳ በሌማን ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች የመጻፍ ክሂል ብቃት ምን ላይ እንደሚገኝ ለማየትና ይህንን ለማሻሻልና መፍትሔ ለመስጠት ነው፡፡ ስለዚህ የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል ብቃታቸውን መመርመር ሲሆን ዝርዝር ዓላማዎች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

- ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ሀሳባቸውን በፅሑፍ መግለፅ መቻል አለመቻላቸውን መፈተሽ፣
- የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የመጻፍ ክሂል ትምህርት እንዴት እየተገበሩ እንደሆነ መመርመር፣
- በመማርያ መጸሐፍት ውስጥ ከቀረቡት ይዘቶች አኳያ የፅሕፈት ክሂልን በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ የሚታየውን ጠንካራና ደካማ ጎኖቹ መገምገም ነው፡፡

## 1.4. የጥናቱ መሪ ጥያቄዎች

ይህ ጥናት የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል ለማሻሻል የመጻፍ ትምህርት የክፍል ውስጥ አተገባበር የሚፈትሽ ነው፡፡ የሚከተሉ ንዑሳን ጥቄዎችን ይመልሳል፡፡

1. በክፍ ውስጥ የመጻፍ ክሂል መቅረብ ባለበት ሁኔታ ቀርቧል?
2. መምህራን የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል ለማሳደግ የክፍል ውስጥ አተገባበር ምንያህል በሚገባ ቀርቧል? የሚሉት ጥያቄዎች በዚህ ጥናት መልስ የሚሰጥባቸው ይሆናሉ፡፡

## 1.5. የጥናቱ ጠቀሜታ

የመጻፍ ክሂል በአንድ ጊዜ የሚዳብር አይደለም፡፡ ተማሪዎች በደረጃ ልምድን እያገኙና እየተጠቀሙበት የመጻፍ ክሂል ትምህርት በተሻለ መልኩ እየቀረበላቸውና እገዛ እየተደረገላቸው ክሂሉን እንዲያዳብሩ ማስቻል ያስፈልጋል፡፡ ስለዚህ የመጻፍ ክሂል አቀራረብ ያለበትን ችግር በመመልከት ጠቃሚ ሀሳብ ለሚከተሉት አካላት አስፈላጊነት ይኖረዋል፡፡

- በሌማን ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የመጻፍን ክሂል ትምህርትን እንዴት መተግበር እንዳለባቸው ጥቆማ ይሰጣል፡፡
- በመጻፍ ወቅት ስህተት ለመፈፀም ምክንያት የሚሆኑ የተማርዎችንችግሮች አውቀው እና ለችግሩ መፍትሄ ለመፈለግ ያግዛቸዋል፡፡
- ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትኩረት በመስጠት በክፍል ውስጥም ሆነ ከክፍል ውጭ ተገቢውን ልምምድ በማድረግና ሀሳባቸውን በፅሁፍ በመግለፅ ከበፊቱ በተሻለ ሁኔታ የመጻፍ ፍላጎታቸውንና ብቃታቸውን ከፍ ለማድረግ ያስችላቸዋል፡፡
- የአማርኛ ቋንቋ የመጻፍ ክሂል በማዳበር ተማሪዎች ሀሳባቸውን አቀነባብረው በሚገባ እንዲገልፁ ይረዳቸዋል፡፡
- ለትምርህት ባለሞያዎች፣ ለሥርዓተ ትምህርት አዘጋጆችና ለመማርያ መጽሐፍት አዘጋጆች የመጻፍ ክሂል ማስተማርያ ዘዴዎችን፣ አቀራረቦችን የማስተማርያ መጽሐፍ ዝግጅት ለመፈተሽና ማስተካከያ ለመስጠት ጥቆማ ይሰጣል፡፡

## 1.6. የጥናቱ ወሰን

ከቦታ አንፃር የዚህ ጥናት ወሰን የሌማን ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ሲሆኑ ከይዘት አንጻር ደግሞ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ የክፍል ውስጥ የመጻፍ ክሂል አተገባበር ላይ ብቻ ትኩረት በማድረግ ተካሂዷል።

# ምዕራፍ ሁለት

# ክለሳ ድርሳናት

## 2.1 መጻፍን የማስተማር ዘዴ

ማስተማር ተማሪዎች እንዲያከናውኑ የሚፈለገውን ግብ ወስኖ ወደዚያ ግብ ለመድረስ የሚከናወን ተግባር እንደሆነ Ornstayin and Lsli (2000) ይገልፃሉ፡፡ ቋንቋንም ማስተማር የቋንቋውን ክሂል እና እውቀት ለማስተማር የሚከናወን ተግባራዊ ሂደት ነው፡፡ እንደ Richardson (1968) ደግሞ የተወሰኑ የቋንቋ ክሂል እና እውቀትን ለማስገንዘብ የሚከናወን ነው፡፡ የክፍል ውስጥ እንቅስቃሴ ማስተማርያ ዘዴ ከሚቀርበው የትምህርት ይዘት አይነት ጋር በጥብቅ የተያያዘ ነው በማለት ያስረዳሉ፡፡ ተማሪዎች እንዲማሩ የሚፈለገው የአፍ መፍቻ ወይም የሁለተኛ ቋንቋ ከሆነ ለምን? ምን? ማስተማር እንደሚገባ ማወቅ ያስፈልጋል፡፡

ሰው በመፃፍ በኩል ይማራል፣ ያስባል፣ እውቀትን የግል ገንዘቡ ማድረግ ይችላል፡፡ በተጨማሪም መጻፍ አዲስ ሀሳብን የማመንጨት ዘዴ መሆን ሀሳብን በሚታይና ግልፅ በሆነ መልኩ መዝግቦ ለሌሎች ለማስተላለፍ፣ ምሁራን እውቀታቸውን እንዲያንፀባርቁበት፣ ማህበራዊ ህይወትም ውስጥ ማስታወሻ ለመያዝና ዘገባዎችን ለማቅረብ አስፈላጊ ይሆናል በማለት Triyohub(1990) ያስረዳሉ፡፡ እንደ Brown (2004) የመፃፍ ትምህርት የፊደላትን ቅርፅ ከማስለየት ጀምሮ ተማሪዎች ቃላት፣ አረፍተ ነገሮችን እና አንቀፆችን ከዚያም ሲያልፍ አንድ የተሟላ ፅሑፍን መፃፍ የሚችሉበትን ክሂል እንዲያገኙ በየደረጃው ይቀርባል፣ ለተማሪዎች የምናቀርበው የመፃፍ ትምህርት በእለት ተእለት ህይወታቸው ውስጥ የሚገለገሉበትን እና የሚያገለግሉበትን ክሂል የሚያስገኝላቸው ሊሆን እንደሚገባ ያስረዳሉ፡፡ በአሁን ጊዜ በስፋት እየተሰራባቸው ያሉ ዋና ዋና የመፃፍ ክሂል ትምህርት አቀራረብ ዘዴዎች ሁለት መሆናቸውን ምሁራን ይገልፃሉ፡፡ እነሱም ውጤት ተኮር ፅህፈት (Product Focused Writing) እና ሂደታዊ ፅህፈት (Process Writing) ናቸው Richards(1990) እና Nunan(1989)፡፡

### 2.1.1 ውጤት ተኮር ፅህፈት

ውጤት ተኮር ፅህፈት አቀራረብ የሚያተኩረው በሂደቱ ላይ ሳይሆን ተማሪዎች በሚፅፉት የመጨረሻ ስራ ላይ ነው፡፡ አላማውም ተማሪዎች በሚያከናውኗቸው የፅህፈት ተግባራት ትክክለኛ ሆነው እንዲገኙ ማስቻል ነው፡፡ ስለሆነም ተማሪዎች የፃፏቸውን ፅሁፎች

ከተነባቢነት፣ የሰዋሰው ስርአትን ከመጠበቅ፣ ከአረፍተ ነገር አወቃቀር፣ ከስርዓተ ነጥብ አጠቃቀም አኳያ ይገመገማልNunan(1989)።

ውጤት ተኮር ፅህፈት ተማሪዎች የተለያዩ ፅሁፎችንና አንቀፆችን እንዲያዋቅሩ ልምምድ ያደርጋሉ። ዋና ትኩረቱም ስህተት የሌለበት ፅሁፍ እንዲያዘጋጁ ማድረግ ስለሆነ የሰዋሰው ህጎች በተለያዩ ዓረፍተ ነገሮች እንደሞዴል ሆነው ይቀርባሉ። ይህ የሚሆነው ተማሪዎች በራሳቸው በሚፈፅሙብትወቅት በትክክል እንዲተገብሩ ለማሳየት ነው። በደንብ እንዲለማመዱ ደግመው እንዲፅፉ ይደረጋል፤ ከዚያም ውስን በሆኑ መልመጃዎች ከተለማመዱ በኋላ ቀስ በቀስ ወደ ነፃ ፅህፈት ይሸጋገራሉ። Richards(1990) ውጤት ተኮር ፅህፈት ሶስት የፅህፈት ደረጃዎች አሉት። እነሱም ውስን ፅህፈት (Guided Writing)፣ መር ፅህፈት (Free Writing) እና ነፃ (ልቅ) ፅህፈትናቸውRichards(1990) እና Byrne (1991)።

የውስን ፅህፈት መልመጃ በአመዛኙ በጀማሪ ተማሪዎች ለሚካሄድ የፅህፈት ትምህርት የሚቀርብ ሲሆን፣ ተማሪዎች ወደ መር-ፅህፈት ከመሸጋገራቸው በፊት የሚለማመዱበት የመጀመርያ ክንውን ነው። በዚህ የፅህፈት ደረጃ ተማሪዎች የፅህፈቱን ስራ የሚያከናውኑት በመምህሩ የሚሰጠውን ትዕዛዝ በመከተል የሚቀርብላቸውን ሞዴል ፅሁፍ ደጋግመው በመፃፍ ነው። የዚህም ዋና አላማ ስህተት የሌለው ፅሁፍ እንዲያዘጋጁ ለማድረግ ነው Richards(1990)።

መር-ፅህፈት ይህ የፅህፈት ደረጃ ተማሪዎችን ወደ ነፃ ፅህፈት የሚያሸጋግር ድልድይ ሲሆን ከውስን ፅህፈት በተሻለ ተማሪዎች የራሳቸውን ሃሳብ ጨምረው እንዲፅፉ እድል የሚሰጥ ነው። በመሆኑም ሞዴል ፅሁፎችን ከተገነዘቡ በኋላ በራሳቸው ተነሳሽነት ሃሳብ እያፈለቁ ለመፃፍ ጥረት የሚያደርጉበት የፅህፈት ደረጃ ነውByrne(1991)።

ነፃ ፅህፈት ከመር-ፅህፈት ቀጥሎ የሚመጣ፣ በውጤት ላይ ያተኮረ የመጨረሻ ደረጃ ነው። ይህ የፅህፈት ደረጃ ከውስንም ሆነ ከመር ፅህፈት የበለጠ ለተማሪዎች ነፃነት የሚሰጥ ነው። ስለሆነም ተማሪዎች በውስንና በመር-ፅህፈት መልመጃ ያገኙትን እውቀትና ልምድ በማዋሃድ በተሰጣቸው ወይም እራሳቸው በመረጡት ድርሰት ይፅፋሉByrne(1991)።

ከምሁራን ሃሳብ መረዳት እንደሚቻለው ውጤት ተኮር ፅህፈት ትኩረት የሚያደርገው በፅሁፍ ሂደት ላይ ሳይሆን የመጨረሻ ውጤት ላይ ነው። በመሆኑም የተማሪዎች ፅሁፍ የሚገመገመው ከሰዋሰው ትክክለኛነት፣ ከአንቀፅ አደረጃጀትና ከቃላት አጠቃቀም አንፃር ስለሆነ ስህተት እንዳይፈፅሙ ከፍተኛ የሆነ ጥንቃቄ ይደረግበታል።

### 2.1.2. ሂደት ተኮር ፅህፈት

ሂደታዊ ፅህፈት ከቅርብ ጊዜ የውጤት ተኮር ፅህፈት ምትክ ሆኖ እንዲሰራ የተጀመረ ዘዴ ሲሆን፣ ትኩረቱም የፅሁፍ የመጨረሻ ውጤት ላይ ሳይሆን ሂደቱ ላይ እንደሆነ ምሁራን ይገልፃሉ፡፡

ከነዚህም መካከልEnekue and Nathalie(2007) "በሂደታዊ አቀራረብ ፀሀፊው የተለያዩ ደረጃዎችን ማለፍ ይጠበቅበታል፣ ደረጃዎቹም ማቀድ፣ ሀሳብን ማደራጀት፣ መተርጐምና የመጨረሻውን ፅሁፍ ማሻሻል ናቸው" በማለት የገለፁት ሲሆን፣Brown (2001) ደግሞ "ሂደታዊ ፅህፈት በቋንቋ ትምህርት ሂደት ዋነኛ ዘዴ ነው" በማለት አጠናክረውታል፡፡

በሂደታዊ የፅህፈት ትምህርት መምህራን በተቻለ መጠን በክፍል ውስጥም ሆነ ውጪ እንዲለማመድ ተማሪዎችን ማበረታታትና ፅህፈት በሚያስተምሩበት ጊዜም ከመጀመርያው ደረጃ ጀምረው እስከ መጨረሻ ከእነሱ ጋር መቆየት አለባቸው፡፡ በዚህ ሂደትም ከተማሪዎች ስራ የአንዱን በመውሰድ የራሳቸውን ማስተካከያ አክለውበት ሠሌዳ ላይ ማፃፍ ከዚያም ተማሪዎች ጥንድ ጥንድ ሆነው ልዩነቱን እንዲወያዩበት በማድረግ ለመጀመሪያ ረቂቃቸው የማሻሻያ መንገዶችን እንዲፈልጉ ማበረታታት ያስፈልጋልHedge (2005)፡፡

ሂደታዊ ፅህፈት ሶስት የተግባር ደረጃዎች ያሉት መሆኑን ምሁራን ይገልፃሉ፡፡ እነሱም፡- ቅድመ ጽህፈት (pre-writing)፣ ማርቀቅ፣ (drafting) እና መከለስ (revising) ናቸውRichards (1990)እናHedge (1998)፡፡

**ቅድመ ፅህፈት፡-** ይህ በሂደታዊ ፅህፈት የመጀመሪያ ደረጃ ነው፡፡ ተማሪዎች ለመጻፍ ብዕርና ወረቀት ከመያዛቸው በፊት ራሳቸውን የሚያዘጋጁበት፣ የመጻፊያ ርዕስ የሚመርጡበት፣ ሀሳብ የሚያሰባስቡበት፣ ስለፅሁፍ አላማ የሚያስቡበትና ለማን እንደሚፅፉ አንባቢያቸውን የሚለዩበት ደረጃ ነው፡፡ የፅህፈትን አላማ በተመለከተ Hedge(1988) "የማስመሰል ዘገባ ነው የምንፅፈው? ወይስ አንድ ነገር እንዴት እንደሚሰራ ግልፅና ዝርዝር የሆነ መረጃ ለመስጠት ነው? ለንደኛ ግብዣ የሚላክ ደብዳቤ ነው? ወይስ የስራ ማመልከቻ ደብዳቤ ነው?" በማለት ገልፀውታል፡፡ ስለዚህ ተማሪዎች ስለፅሑፍ አላማ ግንዛቤ ካዳበሩ ከርዕሱ ጉዳይ ጋር አብረው የሚሄዱ ቃላት ለመምረጥና ለማቃናት ቀላል ይሆንላቸዋል፡፡"

**ማርቀቅ**፡- ሁለተኛ የፅህፈት ደረጃ ሲሆን፣ በቅድመ ጽህፈት የተሰበሰቡ ሀሳቦችን ወረቀት ላይ የማስፈር ሂደት የሚከናወንበት ነው፡፡ በዚህ የፅህፈት ሂደት ተማሪዎች ትኩረታቸውን ይዘቱ

ላይ የሚያደርጉበት፣ ሃሳባቸው የሚያብራሩበት፣ ፅሁፉን ቅርፅ የሚያስይዙበት፣ ተጨማሪ ሃሳብ የሚያመነጩበት፣ ግልፅና አሻሚነት በሌለው ቋንቋ የሚፅፉበት ደረጃ ነው፡፡ በማርቀቅ ሂደት ቅድሚያ የሚሰጠው ለይዘት ትክክለኛነት ቢሆንም ለፅሁፉ ተግባር ላይ የዋሉ እንደ ስርዓተ ነጥብ፣ ሰዋሰው፣ የቃላት ምርጫ የሆሄያት አጣጣል፣ ወዘተ ትኩረት ይደረግባቸዋል፡፡ ተማሪዎች ያረቀቁትን ፅሁፍ መግቢያ፣ ዋና ሃሳብና መደምደሚያ በማለት ይከፋፍላሉ Richards (1990) እና Guth(1989)፡፡

<u>**መከለስ**</u>፡- የሂደታዊ የፅህፈት አተገባበር የመጨረሻ ደረጃ ነው፡፡ ተማሪዎችቀደም ሲል ያረቀቁትን ፅሁፍ መለስ ብለው ከሰዋሰው፣ ከስርዓተ ነጥብ አጠቃቀም፣ ከሃሳብ ተያያዥነት እና ከመልዕክት ግልፅነት አኳያ ትክክለኛ መሆኑን የሚያረጋግጡበት የክንውን ደረጃ ነው፡፡ በመሆኑም የፃፉትን ደጋግመው በማንበብ ለአንባቢ ያስቸግራሉ የሚሏቸውን ቃላት የሚያወጡበትና በሌላ የሚተኩበት፣ እንዲሁም የተዘለሉ ሃሳቦች የሚሟሉበት ክፍል ነውRichards(1990)፡፡

ከላይ ለመረዳት እንደተቻለው ለውጤታማ ፅህፈት በነዚህ አፃፃፍ ሂደቶች ያለፈ ከሆነ ነው፡፡ ክሂሉን ለማዳበር እነዚህ ሂደቶች ጠቃሚ ከመሆናቸውም በላይ ለፅሁፍ ተግባቦትም የራሣቸው የሆነ ድርሻ አላቸው፡፡ በአጠቃላይ ሂደታዊ ፅህፈት ትኩረቱ የተለያዩ የፅህፈት ደረጃዎችን በማለፍ የመጨረሻ ውጤት ላይ መድረስ ስለሆነ ተማሪዎች ደረጃዎቹን በትክክል በመተግበር ጥሩ ፅሁፍ እንዲያዘጋጁ ማበረታታት ያስፈልጋል፡፡

## 2.2 ዘውጋዊ የመጻፍ ክሂል ማስተማርያ ዘዴ

ይህ አይነት መሰረት የሚያደርገው ተማሪው በበቂ ሁኔታ ለቋንቋው ከተጋለጠ ተፈጥሮአዊ በሆነ መንገድና በአጋጣሚ ቋንቋውን ይማራል የሚል ነውErasnen and rerrel, (1983)፡፡ መምህራን ተፈጥሮአዊ አቀራረብን ስራ ላይ ሲያውሉ ግብዓቱን ካቀረቡ በኋላ ብዙ ጊዜ ጣልቃ መግባት አይፈልጉም ለዚህ ምክንያት ጣልቃ መግባት በትምህርት ላይ ችግር ይፈጥራል የሚል ነው፡፡ በዚህ መሰረት በተፈጥሮአዊ አቀራረብ አብዛኛውን ጊዜ ክፍል ውስጥ የሚደረግ መስተጋብር በተማሪዎች መካከል ነው፡፡ የመምህሩ ሚና የቀረቡ ግብዓቶችን በመቆጣጠር የተገደበ ነው፡፡ በዚህ አቀራረብ ተማሪዎች ቋንቋን በመማር ረገድ ከነሱ ስለሚጠበቀው ነገር ያላቸው ግምት አነስተኛ ነው፡፡

በቅርብ ጊዜያት ይህ ተፈጥሯዊ አቀራረብ ነቀፌታ ተሰንዝሮበታል። ለዚህ ምክንያቱ የማይታይ ስነትምህርታዊነትን (invisible pedagogy) መሰረት ያደረገ መሆኑ ነው። ብዙ ምሁራን የመማርማስተማር አቀራረብ "የሚታይ ስነ ትምህርታዊ"መሰረት ያደረገ መርህ እንዲኖር ሀሳብ ያቀረቡ ሲሆን ሀሳባቸው ተማሪዎች በግልፅ ምን መማር እና መዳሰስ እንዳለባቸው የሚገልፅና እንዲሁም በዚህ ግልፅ አቀራረብ በመማርናማስተማሩ ሂደት መምህሩ ከተማሪዎች ጋር የሚቀራረብበትን ዘዴ እንዲጠቀም ሚያስችሉ እና እንዲሁም ተማሪዎች እውቀታቸውን እና ክሂላቸውን እንዲያሳድጉ ተገቢውን ድጋፍ ሊያደርግላቸው የሚያስችል መሆን ይኖርበታልBernstien, (1990)።

ተማሪዎች ዐውዳዊና ስነልሳናዊ ገፅታዎችን በሚገባ በማስተዋል ፅሁፍን ቅርፅ ለማስያዝ እና ለማዋቀር እንዲችሉ ግንዛቤያቸውን ማሳደግ ያስፈልጋል። ለዚህ የዘውግ ተኮር አቀራረብ ጥሩ ጠቀሜታ ይኖረዋል። በትምህርትና በሌሎች መስኮች የዘውግ አቀራረብን በማስተዋወቅ ረገድ አውስትራሊያ የመጀመርያዋ ተጠቃሽ ሀገር ናትMacken-horarik (2001)። የዘውግ አቀራረብ ትኩረት የሚያደርገው ተማሪው ስለቋንቋ ግልፅ የሆነ ዕውቀት እንዲኖረው ማድረግ ሲሆን በመምህሩ እና በተማሪው እንዲሁም በተማሪውና በተማሪ መካከል ለሚኖረው መስተጋብር ዋጋ ይሰጣል።

በVygotskyየዕድገት እሳቤ መሰረት የሚያደርገው የመማር ሞዴል ስለ ቋንቋ መማር ሁለት ሀሳቦችን ያቀርባል።

- መምህሩ በቋንቋ ምን እንደሚሰሩ ብቻ ትኩረት የሚያደርግ ከሆነ ይኸውም ተማሪው በራሱ ብቻ የሚከውን ከሆነ ምንም አይነት መሻሻል አያመጣም።
- መምህሩ ተማሪዎችን የሚደግፍ ከሆነ ያለባቸውን ክፍተት ይሞላል። እውነተኛ ትምህርት እና መሻሻል ይገኛል።

ይህ ሞዴል እንደሚያመለክተው ተማሪዎች ግብአት ቀርቦላቸው በራሳቸው ችሎታ ብቻ መማራቸው በቂ አለመሆኑን ያሳያል። Vygotskyባቀረቡት ሀሳብ ትምህርት በተማሪው እና በመምህሩ ትብብር የሚከናወን ነው። ይህ ትብብር የሚያሳየው በቋንቋ ትምህርት ሂደት በመምህሩ እና በተማሪው መካከል የሚካሄድ ግንኙነት መኖሩን ነው።

የዘውግ (አይነት) ተኮር የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ ትኩረት የሚያደርገው ስለቋንቋ ያለን እውቀት ለተማሪዎች በቀላሉ ወይም ግልፅ በሆነ መንገድ ማቅረብ ላይ ነው። ዘውግ

የሚያመለክተው የፅሁፍን ይዘትና ቅርፅ ክፍፍል ነው፡፡ በሌላ በኩል ዘውግ እንደፅሁፍ ባህርይ ሊገለፅ ይችላል፡፡ እንደStan (2000)ገለፃ ዘውግ ስርዓታዊ ሂደት ሲሆን በየጊዜው እንደነበሩት ንድፈሀሳብ (Contermpory theories) ሁልጊዜ የሚለዋወጥ ነው፡፡ በመሆኑም የተለያዩ ባህሎችና ፍላጐቶችን ለማሟላት ወጥነት ባለው መልኩ የሚከናወን ነው፡፡ በዚህ መሰረት ዘውግ ስንትነትና ዋነኛውና ማዕከላዊ ነጥብ አላማ ነው፡፡ የተለያዩ አይነት ጽሁፎች ወይም ዘውጐች ይሄውም የቅሬታ ደብዳቤ፣ የግብዣ ወረቀት፣ የህግ ዘገባዎች ለተለያዩ ይውላሉ፡፡ Swalles (1990) ዘውግ ሲገለፅ ተመሳሳይ ተግባቦታዊ አላማዎችን የሚጋሩ ሰዎች ተግባቦታዊ ሁነቶች የሚከናወኑበት ነው፡፡

የዘውግ ተኮር አቀራረብ በ1980ዎቹ የተገኘ ሲሆን በዋናነት ተገቢ በሆነ መልኩ የተለያዩ አላማዎች ለመረዳት በማህበራዊ አውዶች መጻፍን ስናስተምር መዋቅሮችን እና ስነልሳናዊ ገፅታዎችን ግምት ውስጥ ማስገባት አለብን Yak(2005)፡፡

በሌላ በኩል አገባብ፣ መዋቅር አላማ እና ስነልሳናዊ ገፅታዎችን እንደዘውጋቸው በተለያዩ ፅሁፎች ውስጥ መንፀባረቅ ያለባቸው ሲሆን በዚህ አቀራረብ ለአንባቢው እና ለፅሁፍ አላማ ትኩረት መስጠት አስፈላጊ ነውKim (2007)፡፡

የዘውግ ተኮር አቀራረብ ከውጤት ተኮር ጋር ሲነፃፀር ግብዓት በተመለከተ በመካከላቸው ግልፅ መመሳሰል ይታያልBadge and white (2000)፡፡ ይሁን እንጂ የዘውግ ተኮር አቀራረብ ተማሪው የበለጠ ውጤታማ ሆነው የሚማሩት ምሳሌዎችና ፅሁፎች ሲቀርብላቸው መሆኑን ግምት ውስጥ ያስገባል፡፡

## 2.3 የመጻፍ ክሂል ትምህርት ዘውጋዊ አቀራረብ

የመጻፍ ክሂልን ለማስተማር የዘውግ ተኮር አቀራረብ ሁለት የተለያዩ አስተሳሰቦች አሉ፡፡ የመጀመሪያ ተማሪዎች አንድን የተለየ ዘውግ በተሳካ ሁኔታ በተመሳሳይ መንገድ እንዴት እንደሚጠቀሙበት መነሻ ነጥብ ሆኖ በሚገባ እንዲያስቡ ያግዛቸዋል፡፡ በዚህ መሰረት በተገለፀው ዘውግ እና ይህን ገፅታ ለተማሪዎች ለማቅረብ ውጤታማ የሆነውን የመፃፍ ገፅታ ለመለየት ይሞከራል፡፡ ዘውጎችን መለየት የሚያስገኘውን ትምህርታዊ ጠቀሜታ Shales (1990) እንደሚከተለው ገልፀውታል፡፡


ግንዛቤ የንግግር እና ስነልሳን ገፅታዎችን ግንኙነት የሚመሰረተው እና ሊያደርግ የሚችለው በዘውግ ውስጥ ብቻ ነው፡፡ እንዲሁም ቋንቋ በተሟላ ሁኔታ ስምምነት ላይ የሚደረስበት እና

የተግባቦት አላማ እና ደረጃ በቂ በሆነ ሁኔታ ለመመስረት ስነትምህርታዊ ተተግባሪነት በአገልግሎትና በቅርፅ መካከል የሚኖረውን ግንኙነት የሚያመለክት መሆን አለበት፡፡

በቋንቋ መማርናማስተማር ሂደት የዘውግ ተኮር አቀራረብ ዓላማ ለተማሪዎች ስለመዋቅርና ንድፍ ያላቸውን ግንዛቤ ከፍ ማድረግ ነው፡፡ ይህንን ሁኔታ ከፍ ለማድረግ ተጠቃሚዎች ተግባቦታዊ ተግባራቸውን ሲያከናውኑ ያለው የስትራቴጂ ደረጃ ተማሪዎች ይህንን ሁኔታ እንዲረዱ የትኛው ስነ ልሳናዊ ገለፃ እንዳለ ለማሳየት ያግዛል፡፡ በአጠቃላይ የዘውግ ተኮር የመፃፍ ትምህርት አቀራረብ አላማ ለተመረጡ መዋቅሮች ስትራቴጂዎች እና ስነ-ልሳናዊ ገፅታዎች ማህበራዊ እና ስነ ልሳናዊ ገለፃዎችን ማቅረብ ነውDvies (1988)::

በሌላ በኩል ዘውግ በተለየ ማህበራዊ አውድ ውስጥ ለተግባቦታዊ ተግባር የተፈጠረ በመሆኑምተለይቶ የሚታወቅ ሲሆን ስነትምህርታዊ ዘውግ ተማሪዎች መፃፍ ሲማሩ የበለጠ ውጤታማ የሚሆኑት ስለቋንቋ ግልፅ የሆነ ግንዛቤ ሲኖራቸው ነው የሚለውን አስተሳሰብ መሰረት ያደርጋልHyland (2003)፡፡ በመሆኑ እንደ ዘውግ አቀራረብ በፅሁፍ ላይ የሚደረግ ትንተና ለተማሪዎች የፅሁፍ ተግባር ይጠቅማል፡፡

ከዚህ በላይ የቀረቡት አስተያየቶች በማህበረሰቡ ውስጥ የዘውግ አስፈላጊነት የሚያሳዩ ሲሆን ዘውግ ሰዎች በሚገባ የተደራጀውን የፀሀፊውን መልዕክት በተለየ መንገድ እንዲረዱ የሚያደርግ ነው፡፡ የዘውግ ተኮር አቀራረብ ተጠቅሞ ተግባቦትን በመፍጠር ለማስተማር የሚያስችሉ የንድፈ ሀሳብ ድጋፎች አሉ፡፡ ተማሪው ለተለያዩ ፅሁፎች መጋለጡ ብቻ ሳይሆን ፅሁፍ የተደራጀበት ሞዴል ያስፈልገዋል፡፡ ከዚህ በኋላ የራሱን ፅሁፍ የሚፅፍ ሲሆን የሚከተሉትን ማለትም ማቀድ፣ መንደፍ፣ መከለስ፣ ማስተካከያ በማቅረብ መዋቅሩ ትክክለኛ የሆነና ተገቢነቱም የፅሁፉን የሚያንፀባርቅ መሆን ይኖርበታል፡፡ S.MBE(2010) ተማሪዎች በመፃፍ ትምህርት ውጤታማ እንዲሆኑ በቋንቋ መማር ሂደታቸው መፃፍን መማር እንደ አንድ አይነተኛ ጉዳይ አድርገው ማቀድ ይኖርባቸዋል፡፡ ከዚህ በላይ በቀረበው አስተያየት ለመጻፍ ትምህርት ውጤታማነትየሞዴል አስፈላጊነት ተጠቅሷል፡፡ በዚህ መሰረት Copa እና Kalantize (1995) መፃፍን ለማስተማር የሚያገለግለውን ሞዴል አቅርበዋል፡፡




ዘውግ ተኮር አቀራረብ መጻፍ ከቋንቋ እውቀት ጋር የተገናኘ እና ከማህበራዊ አላማ ጋር ቁርኝነት ያለው ነው፡፡

## 2.4 ዘውጋዊ የመጻፍ ክሂል ትምህርት አቀራረብ ንድፈ ሀሳቦች

Hyon (1996) Flowrdevs and swalesን ጠቅሰው እንዳብራሩት የዘውግ (አይነት) አቀራረብ በማቀድ ተማሪዎች ተግባቦታዊ አላማዎችን እና ፅሁፎችን ስነልሳናዊ ገፅታ ተገንዝበው ንግግር እንዲያደርጉ ዘውጐችን መለየት ያስፈልጋል፡፡ ይሁን እንጂ እነዚህ ምሁራን ለይዘትና ለማህበራዊ አካባቢ የሰጡት ትኩረት አነስተኛ በመሆኑ ዘውግ ተማሪዎች የተለዩ ሁኔታዎችን ለምሳሌ እንግሊዝኛን ለትምህርታዊ አላማ በክፍል ውስጥ ለሚደረግ ተግባቦት እንደ ፈተና መሳሪያ እና የተፃፉ ፅሁፎችን ለማስተማር የሚያገለግል አድርገው ወስደውታል፡፡ በሌላ በኩል አንዳንድ ተመራማሪዎች ዘውግን ስርዓታዊ ስነልሳናዊ አገልግሎት "systematic functional linguistics" በማህበራዊ ሁኔታ ውስጥ በቋንቋ እና አገልግሎት መካከል ያለን ግንኙነት የሚያመለክት ነው በማለት ገልፀውታል፡፡Hyon,(1996)፡፡ ከዚህ በላይ ከቀረቡት ሀሳብ መገንዘብ የሚቻለው በመፃፍ ክሂል ትምህርት ወቅት የቀረበን ፅሁፍ በቋንቋው የተለየ ገፅታ ላይ ትኩረት በማድረግ መመልከት የሚያስፈልግ መሆኑ ነው፡፡

## 2.5 ዘውጋዊ የመፃፍ ክሂልን ማስተማርያ አቀራረብ ጠቀሜታዎች

በማህበረሰቡ ውስጥ የመጻፍ ክሂልን ለማሳደግ በተደረጉ ጥረቶች በዘውግ አቀራረብ ላይ ትኩረት ሊደረግ ችሏል፡፡ በዘውግ በማህበረሰቡ በቋንቋ ለመፃፍ ተቀባይነት ያገኘ ነው ብሎ መግለፅ ይቻላል፡፡ Hylon (2003) እንዳብራሩት ዘውግ በባህል ውስጥ ተቀባይነት ያለው በማንኛውም ተግባር ለምሳሌ ገለፃ የዜና ዘገባ፣ ግጥም፣ ትረካ የመሳሰሉት በማህበረሰቡ ውስጥ ዕውን የሚሆን ድርጊቶችን ይመለከታል፡፡

ሌላኛው የዘውግ ተኮር አቀራረብ ጠቀሜታ ለተለያዩ አካዳሚያዊ ሁኔታዎች ያለው አስተዋፅኦ ነው፡፡ ተማሪዎች የተለያዩ ፅንሰ ሀሳቦችን የጽሁፍ ሞዴሎችን ተገንዝበው የራሳቸውን

ተመሳሳይ ፅሁፍ እንዲፅፉ ያደርጋቸዋል፡፡ በወቅቱ በነበረው የውጭ ቋንቋ የማስተማርያ ስልት ምትክ የዘውግ አቀራረብ አንቀፅ በማጠናከር ረገድ የተለያዩ የዘውግ ሞዴሎችን በማምጣት የመጻፍ ምድቦችን በማደራጀት እና ልዩ ልዩ አሰራሮችን ስራ ላይ እንዲያውሉ ከፍ ያለ ጠቀሜታ ሰጥቷቸዋል፡፡ Devit (2003) በመጻፍ መማርያ ክፍል ውስጥ የዘውግን ስነ ትምህርታዊ ፋይዳ እንደሚከተለው አብራርተዋል፡፡

የዘውግ ስነ ትምህርታዊነት መምህሩ ትኩረቱን ባቀረበው ፅሁፍ ላይ እንዲያደርግ ተማሪዎችም በታለመላቸው ዐውድ እንዲፅፉ ያስችላቸዋል፡፡ የዘውግ ንድፈ ሃሳብ እና ምርምር ግለሰቦችን በሁለተኛ ቋንቋ እንዲያስተምሩ ለማዘጋጀት ለፅሁፍ መማርያ የሚሆኑ የማስተማርያ መሳሪያዎች እና የተለያዩ መልመጃዎችን እንዲያዘጋጁ ለመምከር ለትምህርት ባለሞያዎች ከፍ ያለ ጥቅም ይሰጣል፡፡

በተጨማሪDevit (2003) እንዳብራሩት የዘውግ ተኮር የመጻፍ ክሂል ትምህርት አቀራረብ መምህሩ ተማሪዎቹ የሚፅፉትን እንዲገምቱና የተማሪዎችን ፅሁፍ ሲገመግም ምን ላይ ትኩረት ማድረግ እንዳለበት ግንዛቤ ይፈጥርላቸዋል፡፡ ዘውግ ፅሁፍን የማሳደግ ጠቀሜታ የቋንቋ ልምድ ለማጥናት ያግዛል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዙ Bawarashi (2003) እንዳብራሩት የዘውግ ትንተና ተማሪው የቋንቋ ተናጋሪ ማህበረሰብ ዘንድ ለመድረስና የማህበረሰቡ አባላት ምን እንደሚያውቁ እና እንደሚሰሩ በአጠቃላይ የቋንቋ ልምምዳቸው ምን እንደሚመስል ለማወቅ ያስችላቸዋል፡፡

የመጻፍ ትኩረት፣ ትርጉም፣ ትንተና ክርክር ወዘተ ሲሆን መጀመሪያ ተማሪዎች ድርሰቱን አጥንተው ከተገነዘቡ በኋላ ሞዴሉን ይከታተላሉ፡፡ ከዚህ ባሻገር ዘውግ ውስጥ የተለየ የቋንቋ አጠቃቀምን ተከትለው የራሳቸውን ፅሁፍ ይፅፋሉ፡፡ Devit (2003)፡፡ ከዚህ በኋላ ውጤታማ የሆነ ድርሰት ለመጻፍ ተማሪዎች ራሳቸው ተስማሚ የሆነ ዘውግና ራሳቸውን ከተለየ የቋንቋ አይነት ወይም ስልት ጋር በመለማመድ በዘውግ ውስጥ በተለየ ሁኔታ የተማሩት አይነት ግምት ውስጥ በማስገባት የራሳቸውን ፅሁፍ ይፅፋሉ፡፡ የዘውግ አቀራረብ በመጻፍ መማሪያ ክፍል ውስጥ ስራ ላይ ለማዋል የተለያዩ ሁኔታዎችን ግምት ውስጥ ማስገባት ያስፈልጋል፡፡ Christen (1987) በዚህ መሰረት ዘውግ በአካዳሚያዊ አውድ ውስጥ የተፃፈ የተተነተነ፣ የተቀዳ ሲሆን በስነ-ልሳናዊ በቃላት እና በፅሁፋዊ ሁኔታው መፈተሽ ያለበት ነው፡፡

በስነ.ልሳን የትንተና ደረጃ ተማሪዎች የቋንቋ አጠቃቀም ገፅታ ከተግባቦታዊ ዓላማ አንፃር መታሰብ አለበት፡፡ በሌላ በኩል የፅሁፍ አወቃቀር ሲተነተን ተማሪዎች ለቋንቋ ምድቦች

ማለትም፣ ለቃላት፣ ለዓረፍተነገር ለንግግር እና ለመሳሰሉት ፍቺ የሚሰጠው እንዴት ነው? የሚሉትን ነጥቦች ማሰብ ያስፈልጋል፡፡

Rimand Kim (2005) Bhatia (1993) ጠቅሰው ባቀረቡ አስተያየት በፅሁፍ ወቅት መደበኛና አገልግሎታዊ የቋንቋ ክፍሎችን አንድ ላይ በማስተማር ተማሪዎች ስነ ልሳናዊ ደንቦች በተለይም በንግግር ወቅት የሚሰጡትን አገልግሎት እንዲረዱ ግንዛቤ ይፈጥርላቸዋል፡፡ Hylanck (2007) የዘውግ ተኮር የመጻፍ ክሂል ትምህርት አቀራረብ ጠቀሜታዎች እንደሚከተለው አቅርበውታል፡፡


- ግልፅ (Explicit) መጻፍን ማለማመድ ለማመቻቸት በትምህርትነት የሚቀርበውን ነገር ግልፅ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡
- ፍላጎትን ያማከለ (Needs based) የፅሁፍ አላማ እና ይዘት መነሻው የተማሪዎች ፍላጎት መሆን አለበት፡፡
- ሀላፊነት መሰጠት (Empowering) ደንቦችና በፅሁፍ ውስጥ ሊኖር የሚችለውን ልዩነት የሚያሳይ ነገሮች ማቅረብ፣
- ደጋፊነት (Supportive) የተማሪዎች የመማርያዎችን የመማርና የፈጠራ ችሎታ ለማሳደግ ለመምህሩ ትልቅ ሚና መስጠት
- ጥልቅ (critical) ለተማሪዎች መረጃዎችን በማቅረብ ንግግሮችን እንዲገነዘቡ እና በጥልቀት እንዲመለከቷቸው ማድረግ
- ንቃትን ከፍ ማድረግ (conciousnes rating) ስለ መፅሀፍ እና ተማሪዎች በፅህፈት ጊዜ በራሳቸው እንዲተማመኑ ለመምከር የመምህሩን ንቃት ከፍ ማድረግ

## 2.6 ዘውግ ተኮር የመጽሀፍ ክሂል አቀራረብ ባህሪ

የዘውግ ተኮር የመጽሀፍ አቀራረብ ቋንቋን ለማስተማር በመጀመሪያ ብቅ ያለው በአውስተትራልያ በማህበረሰቡ ውስጥ ከተነጠሉ ቡድኖች ጋር ለመስራት በማሰብ ነው Feez (2002)፡፡ በተደጋጋሚ የተለየ ቦታ የማይሰጣቸው ተማሪዎች ከተለያዩ ዘውጐች ጋር መላመድ ያለባቸው ሲሆን ከዘውግ ጽሁፎች ጋር እንዲለማመዱ ለማድረግ ሲታሰብ ስነልሳን እና ስለማህበረሰቡ ደንቦች በቂ ግንዛቤ የሌላቸው ተማሪዎች ተከስተዋል፡፡ በመሆኑ መፃፍን በዘውግ ማስተማሪያ ክፍሎ ውስጥ ጠንካራ በሆኑ ስርአቶች መምህሩን ሞዴል በማድረግ ተማሪዎች

የተለያዩ የሚያቀርቡበት ሁኔታ ታይቷል፡፡ በዚህ መሰረት በተከታታይ በዘውግ ተኮር አቀራረብ አጠቃላይ የመጻፍ ሂደት ከሞዴል ወደ ቁጥጥር የሚደረግበት የፅሁፍ አልምምድ እና በመጨረሻም ራስን ችሎ ወደ መፃፍ የሚያመራ ነውHyland (2007)::

ከዚህ በላይ የቀረበውን የመፃፍ ሂደት ባህርይ ተደጋጋሚ ሞዴል ፅሁፍን በጋራ መገንባት እና በግል ፅሁፍን ማደራጀት የሚያመለክት ነው፡፡




Hyland's gener based wiring process Hyland, K. (2007)

በሞዴል ደረጃ መምህሩና ተማሪው ስለ ፅሁፍ መዋቅር ዐውድ እና ቋንቋ ውይይት ከማካሄዳቸውም በላይ ፅሁፉን በጋራ ያጠናክራሉ፡፡ በግልፅ የመጻፍ ደረጃ ተማሪዎች የግላቸውን ፅሁፍ ሲፅፉ በመምህርና ተማሪ ውይይት ደረጃ ፅሁፉን ለማጠናቀቅ የመልስ ክለሳና የአርትኦት ስራ ይከናወናልHyland K. (2004)፡፡

እነዚህ የተለያዩ ደረጃዎች የዘውግ ተኮር የመፃፍ ሂደትን ተፈጥሮአዊ ስርአት የሚያመለክቱ ደረጃዎች የሚያመለክቱ ሲሆኑ ተማሪዎች በሌሎች ድጋፍ በነፃነት ራስን ችለው ወደ መፃፍ ለውጥ መድረሳቸው ነው፡፡

## 2.7 መጻፍን በማስተማር ወቅት የዘውግ እና የሂደት ተኮር አቀራረቦች ጥምረት

መፃፍ በባህሪው ውስብስብ ተግባር ነው፡፡ እንደHyland(2003) አስተያየት መፃፍ የማህበራዊ ግንዛቤ ድርጊት ነው፡፡ በመሆኑ ፀሀፊዎች ድርሰት በሚፅፉበት ወቅት ስለ አውድ እና አንባቢ የተወሰነ የቋንቋ እውቀትና ክህሎት ሊኖራቸው ይገባል፡፡ በተመሳሳይ Trribble (1996) ባቀረቡት ሃሳብ የፀሀፊው ፍላጎት እንዴት እንዳለበት ብቻ ሳይሆን በአውድ ውስጥ ምን መጻፍ እንዳለበት ግንዛቤ ሊኖረው ይገባል፡፡ ከዚህም ሌላ ሰዎች በተስተካከለ ሁኔታ የመጻፍ ችሎታቸው እንዲያድግ ሁለት ጠቃሚ ሀሳቦችን አቅርበዋል፡፡

- ፀሐፊው በድርሰት ፅሁፍ ውስጥ ሲሳተፍ ተገቢውን ሂደት ለማሟላት ያለው የችሎታ መጠን እና
- በተለየ የተግባቦት ሂደት አውድና ይዘት ዘውግ ፅሁፍ ላይ የሚኖረው ተፅዕኖ ለመረዳት የፀሐፊውን ችሎት መጠን ግምት ውስጥ መግባት አለበት፡፡

ሁለቱም አቀራረቦች ማለትም ሂደትና ዘውግ ተኮር አቀራረቦች ባላቸው ጉድለት የተነሳ የተለያዩ ቅኝቶች የተሰነዘሩባቸው ሲሆን እያንዳንዱ አቀራረብ መጻፍን ከተለየ አይነት አንፃር እንደሚቃኙት ግልፅ ነው፡፡ በተመሳሳይ መልኩ Badger and White (2000) ባቀረቡት አስተያት የነዚህ ሁለት አቀራረቦች ልዩነት በክፍል ውስጥ የሚደረገውን ልምምድ ባልተፈለገ አቅጣጫ በመምራት ችግር ሊያስከትሉ ይችላሉ፡፡ ምክንያቱም ውጤት ሂደት እና ቦታ ከአውድ አገልግሎትና ዳራ አንጻር በቅርብ የተሳሰሩ እና ግንኙነት ያላቸው ናቸው፡፡ ከዚህ አንፃር የሂደት እና የዘውግ ተኮር አቀራረብ ጥምረት አንዱ የእያንዳንዱን ክፍተት ለመሙላት የቆመ አድርጎ መውሰድ ይችላል፡፡

በሌላ በኩል የዘውግ ስነ ትምህርታዊነት መሰረት የሚያደርገው ተማሪዎች ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ በሚደረግ ሂደት ከሚማሩ ይልቅ በአውድ ውስጥ የቋንቋ አጠቃቀም በግልፅ በማሳየት ማስተማር የተሻለ ነው የሚል ሲሆን ይህ ማለት ግን የሂደት ተኮር አቀራረብን መተካት ማለት እንዳልሆነ ገልፀዋልHyland (2004)፡፡ ይህንን ሀሳብ Swales (1990) ሲያጠናክሩ "ድርሰትን ስንፅፍ ቅድመ መፃፍን እና የፈጠራ ሀሳብን ማሳደግ ልምምድን ማበረታታት እና ስለራሳቸው ፅሁ ያላቸው ግንዛቤ ይሄውም የንድፍን ጠቃሚነት እና በርዕስ መረጣ ወቅት የግለሰብን ፍላጎት መጠበቅን ችላ ማለት ብልህነት አይደለም" ብለዋል፡፡

የዘውግ ስነትምህርታዊነት የተማሪዎችን የመጻፍ ችግር ለማቃለል ሰዋሰው አስፈላጊ መሆኑን ከማብራራት ይልቅ የመጻፍ ትምህርት ሂደት ከመጀመርያ አንስቶ ተማሪዎች አውድን መሰረት አድርገው ተገቢ የሆነ ፅሁፍ እንዲፅፉ ስለስነልሳናዊ ገፅታ ግልፅ የሆነ ግንዛቤ ሊኖራቸው ይገባል፡፡ አንዳንድ መምህራን ማቀድ ንድፍ እና አርትኦት ጠቃሚ ነገሮች መሆናቸውን አይቀበሉም፡፡ ይሁን እንጂ እነዚህ ነገሮች በተለየ አውድ ውስጥ አላማን ለማሳካትና ፅሁፍን ለመጻፍ ለብቻቸው በቂ አይደሉም Hyland (2004)፡፡

የተለያዩ ምሁራን Badger and White (2000)፣ Hyland (2004) Trribble (1996) የመጻፍን ክሂል ለማስተማር የዘውግና ሂደት ተኮር አቀራረቦችን የማቀናጀት ሀሳብ አቅርበዋል፡፡ Badger and White (2000) በሰጡት አስተያየት የሁለቱ አቀራረቦች ጥምረት አንዱ የአንዱን ክፍተት ለመሙላት ያገለግላል ብለዋል፡፡ ከዚህ ሁኔታ የምንገነዘበው የዘውግና የሂደት ተኮር አቀራረቦች መፃፍን በማስተማር ረገድ በተናጠል ክፍተት ያለባቸው በመሆኑ ይህንን ክፍተት ለመሙላት የሁለቱ አቀራረቦች ቅንጅት አስፈላጊ መሆኑ ነው፡፡

በተለያዩ ሀገራት የቋቋ መምህራን ላይ በተደረገ ቅኝት Ray and Dudey Evan (1998) የዚህ ሁለት አቀራረቦች ውህደት ተቀባይነት አግኝቷል፡፡ በአጠቃላይ የሂደት ተኮር አቀራረብ ከዘውግ ተኮር አቀራረብ ጋር ሲቀናጅ ስለዘውግ ውጤት ያለን እውቀት፣ ዕቅድ፣ ንድፍ፣ ክለሳና የአርትኦትን ስራ አንድ ላይ በማቀናጀት እና የእርስ በርስ ግንኙነት እንዲኖር የሚያስችል እድል በመፍጠር የመጻፍ ክሂልን ለማሻሻል ያስችላል፡፡

## 2.8 የዘውግና የሂደት ተኮር የመጻፍ ትምህርት አቀራረብ የክፍል ውስጥ አተገባበር

የዘውግና የሂደት ተኮር ጥምረት አተገባበር መሰረታዊ መርህ ተማሪዎች መፃፍ የግንዛቤ እና ማህበራዊ ድርጊት መሆኑ ሊገነዘቡት ይገባል፡፡ ከዚህም ሌላ ስለ ዘውግ ያላቸው እውቀትና ፅሁፍ የሚከናወንበት ሂደት ግምት ውስጥ መግባት አለበት፡፡

የዘውግእና ሂደት ተኮር የማስተማር ሞዴል በክፍል ውስጥ ስራ ላይ የሚውልበት አቀራረብ የFeez and Joce's (1998) የመማርና ማስተማር ውህደት አምስት ደረጃዎች ማለትም አውድን መገንባት፣ ፅሁፍን በጋራ መገንባት፣ ፅሁፍን በግል መጻፍ ተዛማጅነት ያላቸውን ፅሁፎች ማግኘት መሰረታዊ ነገሮች ናቸው፡፡ ይህ የመፃፍ ሞዴል መሰረት የሚያደርገው

በመማር ማስተማር ሂደት ዘውግን መሰረት ከሚያደርገው የአውስትራሊያው የዘውግ ትምህርት ቤት የእንግሊዝኛ ቋንቋን ለማስተማር መሰረት ከሚያደርገው መርህ ነው።

ይህ መፃፍን የማስተማር አቀራረብ መሰረት የሚያደርገው የUggotsky Zone of Proximal Development እና Bruner (1986) ስራዎች ላይ ነው። መምህሩ ትምህርቱ ሲጀመር ጀምሮ ጠንካራ ድጋፍ ማድረግ ያለበት ሲሆን ይህ ሁኔታ በኋላ ላይ ተማሪዎች መሻሻል እያሳዩ ሲሄዱ እየቀነሰ ይሄዳል።

በተጨማሪ የዘውግና የሂደት ተኮር አቀራረቦች ጥምረት ትግበራ ተማሪዎች ከሚፅፉት ታላሚው ዘውግ ጋር ተያያዥነት ያለው ነው White and Tmers (1991)። ይህ ሁኔታ ተማሪዎች የፅሁፍን ውስብስብነትና ተደጋጋሚነት እንዲገነዘቡና ፅሁፉን ሲያጠናክሩ ስለዘውግ ያላቸው እውቀት እንዲጠቀሙበት ያስችላቸዋል። የዚህ መጻፍን ለማስተማር አቀራረብ ማቀድ በዋናነት መሰረት የሚያደርገው የFeez እና Soce's (1998) የፅሁፍ ሞዴል ነው።

ሂደታዊ ዘውጋዊ የመጻፍ ክሂል አቀራረብ ስድስት የተለያዩ የማስተማር ተግባራት ሂደቶችን ይከተላሉ። እነሱም፡-

- ዝግጅት
- ሞዴል ማቅረብን ማጠናከር
- ማቀድ
- በጋራ መስራት
- በግል መስራት እና
- መከለስ ናቸው (Yan 2005)።

እነዚህ ስድስት ደረጃዎች ቅደም ተከተላዊ ትስስሮ ያላቸው ተግባራት በመሆናቸው ምክንያት በመካከላቸው ግልፅ የሆነ ድንበር መፍጠር ባይችልም በተናጠል ሲታዩ ግን ምንም ማለት እንደሆኑ (Yan 2005) እንደሚከተለው አስድተዋል።

- **ዝግጅት፡-** መምህሩ ተማሪዎቹ ለፅህፈት እንዲዘጋጁ ለማድረግ ይቻላቸው ዘንድ በአንድ የአፃፃፍ አይነት ለምሳሌ በአመዛዛኝ (በአከራካሪ) ጽሁፍ ሊቀርብ የሚችል ወቅታዊ አነጋገር የሆኑ ሁኔታ በማንሳትና አስፈላጊ ገለፃ በማድረግ ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ ማነሳሳት ይቻላል።

- **ሞዴል ማቅረብ እና ማጠናከር፡-**በዚህ ደረጃ ላይ መምህሩ የተመረጠውን የፅሁፍ አይነት በማስተዋወቅ ተማሪዎቹ የአንባቢያቸውን ማንነት እና የሚኖረውን ማህበራዊ ፋይዳ እንዲያገናዝቡ መፍቀድ ይኖርባቸዋል፡፡ ለምስሳሌ የፅሁፍ አይነት አመዛዛኝ ከሆነ ጽሁፍ ከሆነ አላማው ሊሆን የሚችለው አንባቢን በማሳመን አንድ ድርጊት እንዲከወን ማድረግ ነው፡፡ በመቀጠልም መምህሩ ፅሁፉን እንዴት በማዋቀርና በማደራጀት ዓላማውን ማሳካት እንደሚችል ምክክር ወይም ገለፃ ያከናውናሉ፡፡ ተማሪዎቹም የተማሩትን የፅህፈት አይነት ለማጠናከር ይችሉ ዘንድ ምክክሩ ወይም ገለፃውን ከአንድ ፅሁፍ ጋር ሊያነፃፅሩት ይችላሉ፡፡
- **ማቀድ፡-** በዚህ ደረጃ በርእሰ ጉዳይ የተማሪዎቹን ምናብ (ግንዛቤ) የሚያዳብሩ በርካታ ተግባራት ያከናውናሉ፡፡ ከዚህ ተግባራት መካከል ማሰላሰል መወያየት እና ተዛማጅ ጽሁፎችን ማንበብ ይጠቀሳሉ፡፡ የተግባራቱ መሠረታዊ ዓላማም ርዕሰ ጉዳይን ከተማሪዎቹ ቀደምት ልምድ እና ግንዛቤ ጋር በማስተሳሰር የተነሳሱት ስሜታቸውን ማጎልበት ነው፡፡
- **በጋራ መስራት/መገንባት፡-** ይህ ደረጃ ቀጣዩን ግላዊ የፅህፈት ትግበራ ሒደት የሚያመቻች ሲሆን ፅሁፋዊ ስራውን ለመጀመር ይቻል ዘንድ መምህሩ እና ተማሪዎቹ በጋራ ይሰራሉ፡፡ ስለዚህም የማሰላሰል የማርቀቅና ሐሳቦችን በማቅረብ ሲሳተፉ በተመሳሳይ መምህሩም በተማሪዎቹ የቀረቡትን ሐሳቦችና መረጃዎች በማደራጀት በጥቁር ሰሌዳ ወይም በኮምፒውተር ላይ ይጽፋሉ፡፡ በዚህ መልክ በቅንጅት የተገነባው ጽሁፋዊ ስራ የመጨረሻ ረቂቅም ተማሪዎች ግላዊ ፅሁፋቸውን ሲያዋቅሩ እንዲገለገሉበት በሞዴል ይቀርባል፡፡
- **በግል መስራት፡-** ይህ ደረጃ ተማሪዎች በቀረቡላቸው ሞዴል ላይ ተመስርተው ተመሳሳይ በሆነ ርዕሰ ጉዳይ ላይ ግላዊ ስራቸውን የሚከውኑበት ነው፡፡ ይህን ተግባር ለማከናወን የተመደበው የትምህርት ክፍለ ጊዜ በቂ ላይሆን ስለሚችል አተገባበር ሂደቱን በተመለከተ የመምህሩ እገዛ፣ ገለፃና ምክር ሳይለያቸው ስራውን በክፍል ስራ፣ በቤት ስራ ወይም በአሳይመንት መልክ ሊያከናውኑት ይችላሉ፡፡
- **መከለስ፡-** ተማሪዎቹ የመጀመሪያውን ረቂቅ ካጠናቀቁ በኋላ የመምህራቸው ተግባር የሚሆነው የተማሪዎችን ስራ አንድ በአንድ በመሰብሰብ ውጤት መስጠት ሳይሆን በድጋሚ በሚሰጣቸው መመርያዎች እየታገዙ ስራዎቻቸውን በማረም በመገምገም ወዘተ የማሻሻል ተግባራት እንዲያከናውኑ ማድረግ ነው፡፡

## 2.9 ንድፈ ሀሳባዊ ቅኝት

በዚህ አውድ ስር ከጥናቱ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ንድፈ ሐሳባዊ ጽሑፎች በሰፊው ተዳሰዋል እነዚህ ንድፈ ሐሳቦች እና ጽሁፎች ጥናቱ ከመነሻ እስከ መጨረሻ በማገዝ ረገድ ጉልህ ሚናን ተጫውተዋል፡፡

# ምዕራፍ ሦስት

# የጥናቱ ንድፍና ዘዴ

## 3.1. የጥናቱ ንድፍ

ይህ ጥናት የተጠቀመው መጠናዊ እና አይነታዊ የጥናት ዘዴን ነው፡፡ ጥናቱ ሁለቱን (ቅይጥ) ዘዴ የተከተለበት ምክንያት የመጻፍ ማስተማርያ ዘዴ የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል ብቃት በማሻሻል ረገድ ያለውን ውጤታማነት ለመፈተሽ በተደረገው አተገባበር ላይ በምልከታ፣ በቃለመጠይቅ እና በጽሁፍ መጠይ የተገኙትን መረጃዎች በአይነት እየተመደቡና በመጠን እየተለኩ እንዲገለፁ ስለሚያስቻሉነው፡፡

## 3.2. የተጠኚዎች አመራረጥ

የዚህ ጥናት አላማ የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል ብቃት ምን ላይ እንዳለ መፈተሽ ነው፡፡ ጥናቱ ተተኳሪ አድርጐ የተካሄደው በሌማን ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት በ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ ነው፡፡ ጥናቱ የተካሄደው እጣናሙናን በመጠቀም በ2015 ዓ/ም በሌማን ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት በ12 ምድብ ካሉት 840 የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ውስጥ በእጣ ናሙና 9ኛA እና 9ኛD በጥናቱ ተሳትፈዋል፡፡ የጾታ ስብጥራቸውን ስንመለከት 9ኛA ወንድ 38 እና ሴት 32 ሲሆኑ በድምሩ 70 ተማሪዎች ተዋቅረዋል፡፡ 9ኛD ደግሞ ወንድ 33 እና ሴት 27 ሲሆኑ በድምሩ 60 ተማሪዎች ይገኙበታል፡፡

### 3.2.1 የትምህርት ቤት ናሙና አመራረጥ

በቀርሳ ማሊማ ወረዳ ከሚገኙ ሶስት ትምህርትቤቶች ማለትም ከጊብሶ፣ ከአዳዲ ማርያም እና ከሌማን ሁለተኛ ደረጃ ትምህርትቤቶች ውስጥ የሌማን ሁለተኛ ደረጃ ትምህርትቤት ተተኳሪ ሆኗል፡፡ ትምህርት ቤቱ የተመረጠበት ምክንያት ለአጥኝዋ ካለው የቦታ ቅርበት ችግሩን በቅርቡ ተገኝተው ለመመልከት ስለሚያስችል አመቺ ናሙና ስልት በመጠቀም ነው፡፡

ሁለቱ ያልተመረጡበት ምክንያት ደግሞ የትራንስፖርት ችግር በብዛት የሚታይበትና አጥኚዋን ለወጭና ለጊዜ እጥረት የሚያጋልጥ ሆኖ በመገኘቱ እና እንዲሁም በአሁኑ ጊዜ በሁለቱም ት/ቤቶች አካባቢ እጅግ የከፋ የፀጥታ ችግር እና የሰላም እጦት የሚታይበት ከመሆኑ የተነሳ ለአጥኚዋ ተፈላጊውን መረጃ በየጊዜው ለማግኘት አዳጋች ሲለሆነ ጥናቱን በሁለቱ ት/ቤቶች ላይ ማካሄድ አልተቻለም፡፡

### 3.2.2. የክፍል ደረጃ ናሙና አመራረጥ

ለጥናቱ የተመረጡት የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የ9ኛ ክፍል ተማሪዎችና መምህራን ናቸው፡፡ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች እንዲሆኑ የተደረገው ሁሉም በተመሳሳይ የእርከን ደረጃ ላይ

ስለሚገኙና በሁለተኛ ደረጃ የፅህፈት ክሂላቸውን እንዴት እየተገበሩ እንደሆነ አስተማማኝ መረጃ ስለሚገኝ ነው፡፡ በዚህ ጥናት የ10ኛ፣ የ11ኛ እና የ12ኛ ክፍል ተማሪዎች አልተመረጡም፡፡ ምክንያቱም የ10ኛ ክፍል መምህርት አጥኚዋ በመሆኗ እንዴት እየተገበርኩ ነው? የሚል ብቻ ሳይሆን መምህራን የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል በክፍል ውስጥ እንዴት እየተገበሩ እንደሆነም ጭምር ጥናቱ ስለፈተሸ ሲሆን የ11ኛ ክፍል እና የ12ኛ ክፍል ተማሪዎች ያልተመረጡበት ምክንያት ደግሞከአማርኛናኦሮሚኛ አንዱን በመምረጥ የሚማሩ ስለሆነ ሁሉም ተማሪዎች የኦሮምኛ ቋንቋ ብቻ መርጠዋል፡፡

### 3.2.3. የተማሪ ናሙና አመራረጥ

ጥናቱ በተመረጠው በቀርሳ ማሊማ ወረዳ በሌማን ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት በ12 ምድብ ላይ የሚገኙ 840 ተማሪዎች ናቸው፤ ይሁን እንጂ እነዚህ ሁሉ ተማሪዎች የጥናቱ ተተኳሪ አልሆኑም፡፡

ስለዚህ ከሌማን ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ከ12 ምድብ ተማሪዎች ውስጥ ሁለቱ ምድብ 9ኛA እና 9ኛD ክፍል ተማሪዎች በእጣ ናሙና ተመርጠዋል፡፡ የሁለቱ ክፍል ተማሪዎች ድምር 130 ተማሪዎች ለጥናቱ ተመርጠዋል፡፡ ይህም ከ840 ተማሪዎች ውስጥ 130 ተማሪዎች ብቻ እንዲመረጡ የተደረገበት ምክንያት በአንድ ምርምር ሁሉንም ተማሪ ማዳረስ አዳጋች ስለሆነ ነው፡፡

## 3.3. የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች

የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ምልከታ፣ የጽሁፍ መጠይቅና ቃለ መጠይቅ ለዚህ ጥናት ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡

### 3.3.1 ምልከታ

ምልከታ የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል ብቃት ማስተማርያ ትግበራን አስመልክቶ ጥቅም ላይ ውሏል፡፡ ምልከታ እንደ ቃለ መጠይቅ ወይም እንደ ፅሑፍ መጠይቅ ለመላሹ ጥያቄ ቀርቦለት መላሹ ከራሱ የሚመልሰው ሳይሆን ተመራማሪ ተጠኚዎች በሚገኙበት ቦታ በመሆን በዚህ

ወቅት ምን እንደሚሰሩ፣ እንዴት እንደሚሰሩ፣ እርስ በርሳቸው እንዴት እንደሚረካከቡ፣ ምንእንደሚናገሩ፣ እራሱን በሚመቸው፣አስተማማኝና ትክክለኛ በሚያስገኝለት መንገድ መረጃ የሚሰበስብበት ዘዴ ነው ያለው(2001)። በመሆኑም ለዚህ ጥናት በተመረጠው ሊጠና በታቀደው ርዕስ ላይ ብቻ ትኩረት በማድረግ የምልከታ መረጃ በቼክ ሊስት በመሰብሰብ ስራ ላይ ውሏል።

### 3.3.2 የጽሁፍ መጠይቅ

የጽሁፍ መጠይቅ በዚህ ጥናት የመረጃ መሰብሰቢያ መሳርያ ሆኖ ስራ ላይ ውሏል።አጥኝዋ የተጠቀመችበት የጽሁፍ መጠይቅ አይነት ዝግ ጥያቄዎች(Close-ended Items)የሚባሉትን ነው።በጽሁፍ መጠይቅ የተካተቱት ጥያቄዎች ዘጠኝ ሲሆኑ አምስት አማራጭ መልሶች ቀርበዋል።እነሱም፦ ሀ. ሁልጊዜ ለ. ብዙጊዜ ሐ. በመጠኑ መ. አንዳንድ ጊዜ እና ሠ. በጭራሽየሚሉት የፅሁፍ መጠይቅ የቀረበው ለ130 ተማሪዎች ነው። ሁሉም ተተኳሪ

ተማሪዎች መጠይቁን ሞልተው መልሰዋል። የፅሁፍ መጠይቅ ትኩረት ተጠኚ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ በግልና በቡድን የሚያከናውኗቸውን ተግባራት ይመለከታል።

### 3.3.3 ቃለመጠይቅ

የተማሪዎችን የመፃፍ ክሂል ብቃት ትግበራን አስመልክቶ መረጃ ለመሰብሰብ ቃለ መጠይቅ ጥቅም ላይ ውሏል። ቃለ መጠይቅ ከፅሁፍ መጠይቅ የሚለይበት መጠይቁ የሚደረግላቸው ተማሪዎች ወይም መምህራን መጠይቁን በሚያካሂደው ሰው ጋር የፊት ለፊት ቃለ ምልልስ መኖሩ ነው። ጠያቂው ለተጠያቂው ጥያቄዎችን ያቀርባል፣ ያብራራል፣ ከመላሹ ጋር ፊት ለፊት ሆኖ የተቻለውን ያህል መረጃ ለማግኘት ጥረት ያደርጋል፣ መላሹም ደግሞ ለተጠየቀው ነገር መልሱን በቃል ይሰጣል ያለው (1998)።

ቃለመጠይቅ ለመምህራን የቀረበ ሲሆን ዓላማውም በመማር ማስተማሩ ሂደት ለተማርዎች የሚቀርበው የቋንቋትምህርት በተለይም የመጻፍ ክሂልን እንደት እነደሚያስተምሩ እና በተያያዥ ጉዳዮች ላይ ያተኩራል።

## 3.4 የመረጃ መተንተኛ ዘዴዎች

በተለያዩ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች የተገኙት መረጃዎች በአግባቡ ከተደራጁ በኋላ ተተንትነዋል። በምልከታና በቃለመጠይቅ የተገኙት መረጃዎች በአይነታዊና በመጠናዊ የመረጃ መተንተኛ ስልት ተተንትኗል። መጠናዊ የመረጃ መተንተኛ ስልት የተመረጠበትምክንያት

ከስሙ መረዳት እንደሚቻለው መጠንን ገላጭ ስለሆነ ነው፡፡ አጥኚዋ ይህን መረጃዎች በተለይ ከፅሁፍ መጠይቅ የተገኙትን በመቶኛ ስላስቀመጠች ነው፡፡ አይነታዊ የመረጃ መተንተኛ ስልት መረጃዎችን በቃላት የሚገልፅ በመሆኑ ተጠቅማለች፡፡

# ምዕራፍ አራት

# የመረጃና የጥናቱ ውጤት ትንተና

## 4.1.የትምህርት ይዘት የመጻፍ ክሂልን ለማስተማር ያለው እገዛ

በቋንቋ መማርናማስተማር ሂደት የመጻፍ ክሂልን ትኩረት ሰቶ ለማቅረብ የትምህርቱ ይዘት የሚያሳድረው ተፅዕኖ ቀላል አይደለም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ይዘቱ ከተማሪው ህይወት ጋር ግንኙነት ከሌለው ቋንቋን በማስተማር ሂደት የመጻፍ ክሂል ትምህርት በማቅረብ በኩል አሉታዊ ተፅእኖ ሊያሳድር ይችላል፡፡ ለዚህም የመጀመሪያ ይዘቱን መፈተሽ አስፈላጊ ሆኗል፡፡ በአማርኛ ክፍለ ጊዜ ሁለቱ መምህራን በተደረገው የአምስት አምስት ጊዜ የክፍል ምልከታዎች የክፍለ ጊዜው ይዘት የመጻፍ ክሂልን ለማስተማር ያለው እገዛ በተመለከተ የምልከታ ነጥብና የተገኘው መረጃ ከዚህ ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

### 4.1.1. በክፍል ምልከታ የተገኘው መረጃ

**ሰንጠረዥ1፡- በዚህ ክፍል ከምልከታ የተገኙትን መረጃዎች ለማመልከት በቀረበውሰንጠረዥ ላይ “ሀ” በጣም ከፍተኛ “ለ” ከፍተኛ “ሐ” መካከለኛ “መ” አነስተኛ “ሠ” በጣም አነስተኛ ያመለክታል፡፡**

| ተ/ቁ | የመከታተያ ነጥብ | መምህር | ሀ | ለ | ሐ | መ | ሠ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የክፍለ ጊዜ ይዘት | 1 | 5 | - | - | - | - |
| 1.1 | የመጻፍ ክሂልን ለማስተማር ያለው እገዛ | 2 | 5 | - | - | - | - |
| | | | 10 | | | | |

ከሰንጠረዥ አንድ መረዳት እንደሚቻለው በሁለቱ የጥናቱ ተሳታፊ መምህራን በተደረገው በክፍል ምልከታ ወቅትበአምስት ተከታታይ የመጻፍ ክሂል ትምህርት ይዘቶች የክፍል ውስጥ አተገባበር ሙሉ በሙሉ (100%) በጣም ከፍተኛ ነው፡፡ በምልከታ የነበሩት የክፍለ ጊዜ ይዘቶች እንደሚከተለው ተዘርዝረዋል፡፡

**ምልከታ 1፡ አያያዥ ቃላትን በባዶ ቦታ ላይ መጻፍ**

በዚህ ምልከታ አጥኚዋ እንደተመለከተችው በክፍል ውስጥ ካሉት ተማሪዎች ጥቂቶቹ በሚፅፉበት ጊዜ ቃላትን በትክክል የማይፅፉ መሆናቸውን ተገንዝባለች፡፡ ለዚህም እንደምክንያት የሚጠቀሰው ከመምህራን ቃለ መጠይቅ ምላሽ የተገኘው የተማሪዎች ተነሳሳሽንና ተሳትፎአቸው

ዝቅተኛ እንደ ሆነ ነው መገንዘብ የተቻለው፡፡ አጥኚዋ በምልከታ ወቅት እንደታዘበችው ተማሪዎች ተቀራራቢ የሆኑትን ሆሄያት ማለት "መ" እና "ወ"፣ "ለ" እና "ሰ" "ደ" እና "ጸ"፣ "ዐ" እና "ፀ" ያልለዩ መሆናቸው ነው፡፡

**ምልከታ 2፡- የቃላትን አገባባዊ ፍች መጻፍ**

በዚህ በሁለተኛ ምልከታ ተማሪዎች የቃላት ትክክለኛ ፍቻቸው በአረፍተ ነገር ውስጥ ገብተው የሚሰጡት ፍች የተለያዩ መሆኑን ለማስገንዘብ ነው፡፡ አጥኚዋ በዚህም ምልከታ እንደታዘበችው ከመጻፍም ሆነ መምህሯ በጥቁር ሰሌዳ ላይ የፃፈችውን በትክክል መጻፍም ሆነ ቃላት በአረፍተ ነገር ውስጥ ሲገቡ እንዴት የተለያዩ አውዳዊ ፍች እንደሚኖራቸው በጽሑፍ ማሳየት የቻሉት በክፍል ውስጥ ካሉት 70 ተማሪዎች ግማሾቹ ናቸው፡፡ የቀሩት ተማሪዎች ቃላት የተለያዩ አውዳዊ ፍቺ መኖራቸውን በአረፍተ ነገር ውስጥ በማስገባት ማሳየት ይቅርና በትክክል መጻፍ የሚቸገሩ መሆናቸውን አጥኚዋ ተገንዝባለች፡፡

**ምልከታ ሦስት፡- ለመልመጃዎች እርማት መስጠት**

በዚህ ምልከታ መምህሯ/መምህሩ እርማት በሚሰጡበት ጊዜ የተወሰኑት ምንም መልመጃዎች ያልሰሩና የሰሩትም የማይነበብ ሲሆን በአንደኛ ደረጃ ትምህርትቤት የአማርኛ መምህር አግኝተው በአግባቡ የተማሩት ተማሪዎች የተሰጣቸውን መልመጃዎች በምነበብ መልኩና በአግባቡ የሰሩ መሆናቸውን አጥኚዋ ታዝባለች፡፡

በዚህ ምልከታ የነዚህ የተወሰኑት ተማሪዎች መልመጃውን የማይሰሩና መልመጃውን ሰርተው ጽሑፋቸው የማይነበበው በምልከታ አንድ ስር እንደተጠቀሰው ከ5ኛ እስከ 8ኛ ክፍል በተማሩበት ትምህርት ቤት በስርዓት መምህር ሳያገኙና ሳይማሩ 9ኛ ክፍል ላይ ብቻ የአማርኛ ቋንቋ መማራቸው ተፅዕኖ አሳድሮባቸዋል፡፡

**ምልከታ አራት፡- መጻፍ "የአንቀፅ ምንነት**

በዚህ ምልከታ መምህሯ/መምህሩ ስለ አንቀፅ ምንነት ካስረዱ በኋላ የአንቀፅ ኃይለቃል አብራርተው በስዕል መልክ አስረድተው ብዙ ማብራሪያ ከሰጡ በኋላ ተማሪዎች ለሙከራ ያህል አንቀፅ እንዲፅፉ የክፍል ስራ በመስጠት አብራርተዋል፡፡ በዚህ በአራተኛ ምልከታ በሁለቱም ክፍል ማለት በ9ኛ "ሀ" እና "መ" ከበፊቱ ተማሪዎች የተሻለ የመጻፍ ችሎታቸው የዳበረ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ለዚህም ምክንያት መምህሩ/መምህሯ በሚያስተምርበት ጊዜ ሌላ ተጨማሪ መምህር ገብቶ ሲመለከታቸው ከበፊቱ የበለጠ ሞራልና ተነሳሽነት እንደሚፈጥርባቸው ገልፀዋል፡፡

ከተገኘው መረጃ በመነሳት በምልከታ ክፍለ ጊዜያት የትምህርት ትኩረት ሲጠቃለል ጽህፈት እና ለመልመጃዎች እርማት መስጠት ላይ መሆኑ ግልፅ ነው፡፡ እነዚህ ርዕሰ ጉዳዮች ደግሞ መምህራኑ የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል ለማሻሻል እና ከፍ ለማድረግ አመቺ ናቸው፡፡

**ለምሳሌ** የእለቱ የትኩረት አቅጣጫ የአንቀፅ ምንነት ከሆነ ተማሪዎች የአንቀፅን ምንነት ከተገነዘቡ በኋላ በራሳቸው ርዕስ በመምረጥ መምህራቸው ባዘዛቸው መልኩ በመረጡት ርዕሰ ጉዳይ ዙርያ አንቀፅ ይጽፋሉ፡፡ በዚህም ሂደት ማለትም አንቀፅ በሚፅፉበት ወቅት የመጻፍ ክሂላቸውን ከፍ እያደረጉ ነው፡፡

## 4.2. የተተኳሪ መምህራን ዳራዊ መረጃ

### 4.2.1 መምህራን በቋንቋ ትምህርት የመጻፍ ክሂል አቀራረብ ላይ ያላቸው ግንዛቤ እና እውቀት

**ሰንጠረዥ 2፡- የመምህራን መረጃ እድሜ በትምህርት ደረጃ፣ በጾታ እና በአገልግሎት ዘመን**

| ተ/ቁ | የት/ቤቱ ስም | መምህር/ት | እድሜ | የት/ደረጃ | ፆታ | በዋናነት የተመረቀበት/ችበት | የአገልግሎት ዘመን |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ሌመን ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት | መ1<br>መ2 | 35<br>50 | BED<br>MA | ሴ<br>ወ | አማርኛ<br>አማርኛ | 10<br>30 |

ከሰንጠረዥ ሁለት መረዳት እንደሚቻለው ሁለቱም ተተኳሪ መምህራን በዋናነት የሰለጠኑበት የትምህርት መስክ በአማርኛ ቋንቋ ነው፡፡ የትምህርት ደረጃ እና ጾታ ስንመለከት ወንዱ መምህር MA (ሁለተኛ) ዲግሪ ያለው ሲሆን ሴቷ መምህርት የትምህርት ደረጃ የመጀመሪያ ዲግሪ ያላት መሆኗ ነው፡፡ የአገልግሎት ዘመናቸውን በተመለከተ ሴቷ መምህርት 10 ዓመት አገልግሎት ያላት ሲሆን ወንዱ 30 ዓመት አገልግሎት ያለው መሆኑን መረጃው ያሳያል፡፡ ይህ መረጃ ደግሞ መምህራን ያላቸው የትምህርት ደረጃና የአገልግሎት ዘመን ቋንቋውን ለማስተማር ለክፍል ደረጃው የሚመጥን እንደሆነና በዕለት ተእለት የማስተማር ተግባራቸውን በመጻፍ ክሂል ላይ ብቻ ሳይሆን ስለ ክሂሎች ሊኖራቸው የሚችለው ግንዛቤ የተሻለ እንደሆነ ያሳያል፡፡

## 4.2.2 ለመምህራን ከቀረቡት ቃለ-መጠይቅ የተገኘ ምላሽ

የመምህራኑ የመጻፍ ክሂል አቀረረብ እውቀት በተዘዋዋሪ ለማወቅ በጥያቄ ተ.ቁ.1. የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል ብቃት ለማዳበር ትኩረት ሰጥተው ማስተማር የሚለውን አቀራረብ ያውቁታል? ጥያቄ ተ/ቁ.3. በተማሪዎቹ የቋንቋ ችሎታ ላይ ለውጥ ያመጣል ብለው ያስባሉ? ከሆነ እንዴት? ካልሆነ ለምን?በጥያቄ ተ.ቁ.4 የመጻፍ ክሂል የቀሩት ሦስት ክሂሎች ማለትም ማንበብ፣ መናገር እና በማዳመጥ ጊዜ እንዴት እንደሚያግዝ በቋንቋ ትምህርት ክፍለ ጊዜ ተማሪዎችን ያስገነዝባሉ? ያስረዳሉ? ካስረዱ እንዴት? ካላስረዱ ለምን?

በጥያቄ ተ.ቁ.5. በሰለጠኑበት የትምህርት ተቋም የመጻፍ ክሂል አቀራረብ በተናጠል ነው? ወይስ በቅንጅት?በጥያቄ ተ.ቁ.2. የመጻፍ ክሂልን በተፈጥሮአዊ መንገድ ማግኘት ይቻላል? ወይስ በት/ቤት ብቻ? ጥያቄዎች ቀርበው የተገኙት ምላሾች እንደሚከተለው ተተንትነዋል፡፡

ለጥያቄ ቁጥር 1 መምህራን የሰጡት ምላሽ ስንመለከት ሁለቱም መምህራን የተማሪዎች የመጻፍ ችሎታን ለማዳበር በትኩረት መሰጠት እንዳለበት ግንዛቤ ያላቸው መሆኑን ከምላሻቸው ለመረዳት ተችሏል፡፡ ሆኖም ግን ተማሪዎች ከተለያየ 1ኛ ደረጃ ትምህርትቤቶች ስለሚመጡና ከአንዳንድ ትምህርትቤቶች የሚመጡ ተማሪዎች በደንብ ፊደል ሳይለዩ የሚመጡ ከመሆናቸው የተነሳ የመጻፍም ሆነ የተቀሩትን ሶስቱን ክሂሎች ለተማሪዎች ለማስጨበጥ የሚቸገሩ መሆናቸውን ገልፀዋል፡፡

ለጥያቄ ቁጥር 2 የመጻፍ ክሂል አፈ-ፈቱም ሆነ ኢ-አፈ-ፊት ተማሪዎች የሚያገኙው በትምህርት ቤት ብቻ መሆኑንና በአሁን ጊዜ ለቋንቋው ትኩረት ካለመስጠትና በቋንቋው የሰለጠኑ መምህራን ባለመኖራቸውና በ1ኛና መለስተኛ ደረጃ ትምህርትቤቶች አንድ መምህር/ት ቋንቋዉን በመናገሩ/ሯ ብቻ ያለ ፍላጎቱ/ቷ የምያስተምር/ የምታስተምር ከመሆኑ የተነሳ በተማሪዎቹ ላይ የከፋ ጉዳት መድረሱን ገልፀዋል፡፡

ጥያቄ ተ.ቁ.3 የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል ብቃት ለማዳበር ትኩረት ሰጥተው ማስተማር በተማሪዎች የቋንቋ ችሎታ ላይ ለውጥ ያመጣል ብለው •ያስባሉ? ለሚለው የተሰጠው ምላሽ ሁለቱም መምህራን የመጻፍ ክሂልን ትኩረት ሰጥቶ ማስተማር በጣም አስፈላጊ እንደሆነ ገልፀዋል፡፡ ለዚህም ማብራርያ ሲሰጡ ተማሪዎች በመምህር ገለፃ በሚደርግበት ጊዜ፣ የተለያዩ የፅሑፍ መረጃዎችን በሚያነቡበት ጊዜ፣ እንዲሁም ስለአንድ ርዕሰ ጉዳይ በሚወያዩበት ጊዜ

ሐሳባቸውን የሚያሰፍሩት እና እንዳይረሱት የሚያግቸው በጽህፈት አማካኝነት ስለሆነ፣ የመጻፍ ክሂልን ትኩረት ሰጥቶ ማስተማር የበለጠ አስፈላጊ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

ለጥያቂ ተ.ቁ.4 የተሰጠው ምላሽ የትምህርት ደረጃው 2ኛ ዲግሪ የሆነ ነው፡፡ መምህር በማስረጃ በማስደገፍ ገልፀዋል፡፡ ይህም ተማሪው ማንኛውንም የትምህርት አይነት በሚማሩበት ጊዜ ከመምህር የሚያገኘውን ገለፃ፣ ሰፋፊ ምንባብ በሚያነብበት ጊዜ እንዲሁም ከተለያዩ ምንጮች የሚያገኘውን እውቀት አደራጅቶ የሚያስቀምጠው እንዳይረሳው አጋዥ የሚሆነው በፅህፈት አማካኝነት እንደሆነ አስረግጠው ለተማሪዎች እንደሚያስረዱ አብራርቷል፡፡ ሁለተኛዋ መምህርት በትምህርት ደረጃ 1ኛ ዲግሪ የሆነችው የክሂሉን ምንነት ከማስተማር ባሻገር ለሁሉም የትምህርት አይነት መሰረት መሆኑን እንደማታስገነዝብ ነው፡፡ ከምላሽዋ መረዳት የተቻለው፡፡

ለጥያቂ ተ.ቁ.5. አንደኛው መምህር የሰጠው ምላሽ ማለትም የትምህርት ደረጃው ሁለተኛ ዲግሪ የሆነው አራቱንም የቋንቋ ክህሎች በተናጠል መማራቸውንና የመጻፍ ክሂል ክሂለ ብዙ ተግባር እንደሆነ የምሁራንን ሀሳብ ጠቅሰው ገልፀዋል፡፡ ምክንያቱ በማዳመጥ፣ በማንበብ የተገኘውን መረጃ ለረጅም ጊዜያት የምናስቀምጠው በፅህፈት አማካኝነት መሆኑን በመጥቀስ ሁለተኛዋ መምህርት የትምህርት ደረጃዋ 1ኛ ዲግሪ የሆነና 10 ዓመት የሥራ ልምድ ያላት አራቱንም ክሂሎች በተወሰነ ደረጃ መማራቸውንና በአመዛኙ ትኩረት ያደረጉት በንግግር ክሂል ላይ እንደሆነና በጥልቀት ስለመጻፍ ክሂል እንዳልተማሩ ነው ከምላሽዋ መረዳት የተቻለው፡፡

ከሁለቱ መምህራን ምላሽ መረዳት እንደሚቻለው የትምህርት ደረጃዋ 1ኛ ዲግሪ የሆነው አራቱንም ክሂሎች በተናጠል በስፋትና በጥልቀት ግንዛቤ የሌላት መሆኑንና የትምህርት ደረጃው 2ኛ ዲግሪ የሆነው መምህር በተማሩበት ተቋም የመጻፍም ሆነ ሌሎች የተቀሩትን ክሂሎች ሰፋ ያለ ግንዛቤ እንዳለው ነው ከምላሹ መረዳት የተቻለው፡፡

## 4.3.የመምህራን የመፃፍ ክሂል ትምህርት አቀራረብ

የመምህራኑ የመጻፍ ክሂል ትምህርት አቀራረብ ለማወቅ ከተለያየ መረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች የተገኘው መረጃ እንደሚከተለው ተተንትኗል፡፡

### 4.3.1. ከምልከታ የተገኘ መረጃ ትንተና

***ሠንጠረዥ 3፡- የመምህራንን የመፃፍ ክሂል ትምህርት አቀራረብ ለማወቅ ከምልከታ የተገኘ መረጃ፡፡***

| ተ/ቁ | የመከታተያ ነጥብ | ሀ | ለ | ሐ | መ |
|---|---|---|---|---|---|
| 2.1.1. | መምህሩ/ትዋ የመጻፍ ክሂልን ትኩረት ሰጥተው ያስተምራሉ? | 3 (30%) | 4 (40%) | 2 (20%) | 1 (10%) |

በሰንጠረዥ 3 ላይ እንዳየነው በ3 (30%) ክፍለ ጊዜያት ከፍተኛ በ4 (40%) ክፍለ ጊዜያት መካከለኛ በ2 (20%) ክፍለ ጊዜያት አነስተኛ በ1 (10%) ክፍለ ጊዜያት በጣም አነስተኛ የመጻፍ ክሂል አቀራረብ መኖሩ ታውቋል፡፡ ከዚህ መረዳት እንደሚቻለው የመጻፍ ክሂልን ትኩረት ሰጥቶ የሚያስተምሩ መምህራን አነስተኛ መሆናቸው ነው፡፡ መምህራን የመጻፍ ክሂልን ትኩረት ሰጥቶ ለማስተማር የሚያደርጉት ጥረት ምን ይመስላል? በሚለው መከታተያ ነጥብ መነሻነት ከምልከታ የተገኘውን መረጃ ስንመለከት በአንዱ መምህር የመጻፍ ክሂልን ለተማሪዎች በማስረዳት ረገድ የሚያደርገው ጥረት እጅግ በጣም ጥሩ የሚባል ባይሆንም ጥሩ ጥረት ተስተውሏል፡፡

የትምህርት ደረጃዋ 1ኛ ዲግሪ የሆነችዋ መምህርት ላይ የታየው ደግሞ መምህርቷ ጥሩ ጅማሮች ይታይባትና በመሀል ገለፃዎችን በማብዛት ክፍሉን የመቆጣጠር ሁኔታ እንዳለ ማወቅ ተችሏል፡፡

በዚህም ተማሪዎች ሃሳባቸውን ለመግለፅ ገና አንድ ሁለት ቃላት እንደተናገሩ “አዎ” ወይም “እሷ” “እሱ” እንዳለው ብለው ዘለግ ያለ ገለፃ ሲያደርጉ ለማየት ተችሏል፡፡ ደግሞ ተማሪዎች በቋንቋው ሃሳባቸውን እንዳይገልፁ እንቅፋት ሲሆን ተስተውሏል፡፡

በተ. ቁ. 12 ላይ የመጻፍ ክሂል ለተቀሩት ለሶቱ ክሂሎች ማለትም በማዳመጥ ጊዜ፣ በንግግር ጊዜና በማንበብ ጊዜ ምን ያህል ጥቅም እንዳለው ለተማሪዎች የማስረዳት አዝማሚያ ይታያል? በሚለው መከታተያ ነጥብ መነሻነት ከምልከታ የተገኘው መረጃም በአንደኛዋ መምህርት ላይ የመጻፍ ክሂል ሦስቱን ክሂሎች መሰረት ለማስያዝ ያለውን ጥቅም ለተማሪዎች የማስገንዘብ ሁኔታ አልታየም ማለት ቢቻልም በሁለተኛው መምህር ግን የመጻፍ ክሂል ሌሎች ክሂሎች መሰረት ለማስያዝ ጥቅም ያለው መሆኑን ጭምር ለተማሪዎች ሲያስገነዝብ ተስተውሏል፡፡

በተ.ቁ.14 ላይ በጠቅላላ በመማር ማስተማር ሂደቱ የመጻፍ ክሂል አቀራረብ አጠር ያለ ግላዊ አስተያየት የሚል መከታተያ ነጥብ ቀርቦ የተገኘው አጠቃላይ መረጃ ሲታይ በሁለቱም መምህራን የነበረው የመፃፍ ክሂል አቀራረብ ሂደት ደህና ነው ሊባል የሚያስችል ነው፡፡

በተናጠል ሲታይ ወንዱ መምህር እና ሴቷ መምህርት ምንም እንኳን በርከት ያሉ ዘዴዎች ወይም ብልሀቶች የመጠቀም ሁኔታ አናሳ ቢሆንም የመጻፍ ክሂልን ትኩረት ሰጥቶ በማስተማር ረገድ በመምህሩ ላይ ጥሩ ነገር ታይቷል፡፡ ሴቷ መምህርት ግን ተማሪዎች የመጻፍ ክሂላቸውን እንዲያሻሽሉ ለማሳተፍ ሙከራ ቢያደርጉም በአብዛኛው ግን በተወሰኑት ክሂሎች ላይ ብቻ ትኩረት ስለሚያደርጉ የመጻፍ ክሂልን ትኩረት ሰጥቶ በማስተማር ላይ ክፍተቶች አሉ፡፡ ምልከታ በተደረገባቸው ክፍለጊዜያት የመማር ማስተማር ሂደትም የተማሪዎችን የመፃፍ ክሂል ብቃታቸውን ከፍ ለማድረግ ፍፁም የተመቸ አልነበረም፡፡

### 4.3.2 ለመምህራን ከቀረበው ቃለመጠይቅ የተገኘ መረጃ

በተ.ቁ.9 ላይ ተማሪዎች በመደበኛ ክፍለ ጊዜያት የመጻፍ ክሂል ትምህርት ከሚማሩት ባሻገር ተማሪዎችን በልምምድ ብቁ የቋንቋ ተጠቃሚ የሚያደርግ የመማርና ማስተማር ሂደትን ይከተላሉ? የሚል ጥያቄ ቀርቦላቸው ሁለቱም መምህራን አብዛኛውን ጊዜ የሚል ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ ሆኖም ግን በምልከታ ክፍለ ጊዜ ከታየው ጋር ሲነፃፀር ልዩነት አለው፡፡

ይህ ደግሞ መምህራኑ የመጻፍ ክሂልን በመማርያ መጽሐፍ ውስጥ በመኖሩ ብቻ የመጻፍ ክሂልን በማለማመድ የተማሪውን የመጻፍ ችሎታ ያዳበሩ ይመስላቸዋል፡፡ ይህ ግን ስህተት ነው፡፡ ምክንያቱም በምዕራፍ ሁለት የተዛማጅ ፅሁፍ ቅንጅት ላይ ማስተማር ተማሪዎች እንዲያከናዉኑ የሚፈለገውን ግብ ወስኖ ወደዚያ ግብ ለመድረስ የሚከናወን ተግባር እንደሆነ (Ornstyinand Lsli (2000) ይገልፃሉ፡:

## 4.4. መምህራን የመፃፍ ክሂልን ለማስተማር የሚጠቀሙባቸው ብልሃቶች

ይህ ክፍል ትኩረት የሚያደርገው መምህራኑ የመጻፍ ክሂልን ለማስተማር የሚጠቀሙባቸው ዘዴዎች ወይም ብልሃቶች ላይ ነው፣ በመሆኑም ከተለያዩ መረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች የተገኙት ምላሾች ተቀናጅተው ይተነተናሉ፡፡

### 4.4.1 ከክፍል ምልከታ የተገኘ መረጃ

**ሰንጠረዥ 4፡- መምህራን የሚጠቀሙባቸው ዘዴዎች ወይም ብልሃቶች ለማወቅ ከምልከታ የተገኘ መረጃ**

| ተ/ቁ | የመከታተያ ነጥቦች | ሀ | ለ | ሐ | መ |
|---|---|---|---|---|---|
| 2.3.1. | የምንባቦችን ሀሳብ በራሳቸው አባባል እንዲፅፉ የማድረግ ሁኔታ | 4 (40%) | 2 (20%) | 3 (30%) | 1 (10%) |
| 2.3.2. | ምንባቡን መነሻ በማድረግ ሀሳቦችን አመንጭተው እንዲፅፉ የማድረግ ሁኔታ | 3 (30%) | 1 (10%) | 5 (50%) | 1 (10%) |
| 2.5. | ተማሪዎች በሚሰጣቸው ተግባር አማካኝነት | - | - | - | - |
| 2.5.1. | እርስ በርስ እንዲከራከሩ የማድረግ ሁኔታ | 2 (20%) | 3 (30%) | 4 (40%) | 1 (10%) |
| 2.5.2. | እርስ በርስ እንዲወያዩ የማድረግ ሁኔታ | 4 (40%) | 2 (20%) | 4 (40%) | - |
| 2.9. | ከተማሪው መጽሐፍ ውጭ የተማሪዎችን ፍላጎት የሚጨምር ይዘት የማቅረብ ሁኔታ | 2 (20%) | 3 (30%) | 4 (40%) | 1 (10%) |
| 3.8. | ድራማዎችን የመስራት የተለያዩ ጭውውቶችን በሚና ጨዋታ አማካኝነት የመተግበር ሁኔታ | 3 (30%) | - | - | 7 (70%) |

በሰንጠረዥ 4 ላይ እንደሚታየው በሁለቱ መምህራን ላይ በተደረጉ ምልከታዎች ለ2..3.1 ተ.ቁ. የተገኘው መልስ 4(40%) ክፍለ ጊዜ ከፍተኛ 2 (20%) ጊዜ መካከለኛ 3 (30%) ጊዜ አነስተኛ ሲሆን 4 (40%) ጊዜ በጣም አነስተኛ፣ ለጥ.ተ.ቁ 2.3.2. የተገኘው ምላሽ 3 (30%) ጊዜ ከፍተኛ 1 (10%) ጊዜ መካከለኛ 5 (50%) ጊዜ አነስተኛ እንዲሁም 1 (10%) ጊዜ በጣም አነስተኛ ሆኗል፡፡ ለጥ.ተ.ቁ.2.5.1. የተገኘው ምላሽ 2 (20%) ጊዜ ከፍተኛ 3 (30%) ጊዜ መካከለኛ 4 (40%) ጊዜ አነስተኛ እና 1 (10%) ጊዜ በጣም አነስተኛ ሆኗል፡፡

ለጥያቄ ተ.ቁ.2.5.2. የተገኘው ምላሽ 4 (40%) ጊዜ ከፍተኛ 2 (20%) ጊዜ መካከለኛ 4 (40%) ጊዜ አነስተኛ ሆኗል፡፡

ለጥ.ተ.ቁ.2.9. የተገኘው መልስ 2 (20%) ጊዜ ከፍተኛ 3 (30%) ጊዜ መካከለኛ 4 (40%) ጊዜ አነስተኛ 1 (10%) ጊዜ በጣም አነስተኛ ሆኗል፡፡ ለጥ.ተ.ቁ.. 3.8. የተገኘው መልስ 3 (30%) ጊዜ ከፍተኛ 7 (70%) በጣም አነስተኛ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ በምልከታ መከታተያ ቅፅ ተ.ቁ.10. የቡድንና የጥንድ ውይይቶች ምን አይነት መልክ አላቸው? የመጻፍ ክህሎትን ለማጐልበት ያላቸው ፋይዳስ? ተ.ቁ. 11 ላይ መምህራን የመጻፍ ክሂልን ለማስተማር የሚጠቀሙባቸው (የሚያቀርቧቸው) ተግባራት ምን ምን ናቸው? ተ.ቁ. 13 ላይ መምህራን የመጻፍ ክሂልን ለማስተማር የሚጠቀሙባቸው ዘዴዎች ወይም ብልሀቶች ምንድን ናቸው? የሚሉ ጥያቄዎች ቀርበውላቸው የተገኘው ምለሽ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ምልከታ ከተደረገባቸው መምህራን (መ1) በ5 ክፍለ ጊዜያት የነበረው የቡድን ውይይት ጥሩ የሚባልና የመጻፍ ክሂልን ለማጐልበት (ለማዳበር) እገዛ የሚያደርጉ ሲሆን በ(መ/ርት 2) በጠቅላላ በ5 ክፍለ ጊዜያት የነበረው የቡድን ውይይት ግን የታቀደለትን ዓላማ የሚያሳካ አልነበረም፡፡ ለ11ኛው ጥያቄ ሁለቱም መምህራን የክፍልና የቤት ስራ መስጠትና ተማሪዎች የሰሩትን መልስ በቃል አንዳንዴም በንባብ እንዲያቀርቡ የሚያደርጉበት ሁኔታ እንዳለ ለመመልከት ተችሏል፡፡

በአንደኛዋ መምህርት ከመማርያ መፅሐፍ ውጭ የተማሪዎችን ፍላጎት የሚጨምር ይዘት የማቅረብ ሁኔታ የታየ ሲሆን በሁለተኛ መምህር በተወሰነ ክፍለ ጊዜያት በመጻፍ ላይ በቀረቡ ይዘቶች ላይ የበለጠ ማሻሻያዎች በማድረግ ለመጠቀም ጥረት ሲያደርግ ታይቷል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በ2 ክፍለ ጊዜያት ብቻ ተማሪዎች የተለያዩ ጭውውቶችን በክፍል ውስጥ ሲያቀርቡ ለመመልከት ተችሏል፡፡

ለ13ኛው ጥያቄ በሁለቱም መምህራን በጽሐፍ የቀረቡትን ይዘቶች መነሻ በማድረግ ተማሪዎች ሀሳባቸውን በቃል እንዲገልፁ አልፎ አልፎም በጽሑፍ እንዲገልፁ (እንዲያቀርቡ) ሙከራዎችን ሲያደርጉ ለማየት ተችሏል፡፡ በተ.ቁ.11 ላይ እንደተገለፀው በ2 ክፍለ ጊዜያት ጭውውት የታየ ሲሆን በሁለቱም መምህራን ላይም ተማሪዎቹን በቡድን እንዲወያዩ የማድረግ ሁኔታ ተስተውሏል፡፡

ከላይ ያለው መረጃ ሲጠቃለል ይዘት ተኮር፣ ተግባር ተኮር፣ ስነ-ፅሑፍን መሰረት ማድረግ እና ሚና ጨዋታ እጅግ በመጠኑ የተስተዋሉ ሲሆኑ የቡድን ውይይወቶችና ሀሳብን በቃል የማቅረብ ብልሀቶችን ግን በተሻለ መልኩ ተንጸባርቀዋል፡፡

### 4.4.2. ለመምህራን ከቀረበ ቃለመጠይቅ የተገኘ መረጃ

በዚህ ክፍል የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የመጻፍ ክሂልን ለማስተማር የሚጠቀሙባቸውን ዘዴዎች ወይም ብልሀቶች ለመመርመር ለመምህራን የቃል ጥያቄዎች ቀርበውላቸው የሚከተሉትን መልስ ሰጥተዋል፡፡ በጥያቄ ተ.ቁ.10. ላይ ተማሪዎች አንድን ንግግር አዳምጠው የተረዱትን ሀሳብ እንዲፅፉ ያደርጋሉ? በጥያቄ ተ.ቁ.11 ተማሪዎች የተለያዩ ርዕሶችን መርጠው እንዲወያዩና እንዲከራከሩ ያደርጋሉ?

በጥያቄ ተ.ቁ.12 ለተማሪዎች ከመማርያ መጽሐፍት ውጪ ሌሎች ምንባቦች ያነቡላቸዋል?በጥያቄ ተ.ቁ.13. የሚያነቡላቸውን ምንባቦች መነሻ በማድረግ የራሳቸውን ፈጠራ በማከል አስፋፍተው እንዲጽፉ ያደርጋሉ? የሚሉ ጥያቄዎች ቀርበውላቸው የተገኘው ምላሽ ጠቅለል ተደርጎ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ለጥያቄ ተ.ቁ. 10. አንደኛው መምህር እብዛኛውን ጊዜ የሚል መልስ ሲሰጥ፣ አንደኛዋ መምህርት አንዳንድ ጊዜ የሚል ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ ለጥያቄ ተ.ቁ.11. ሁለቱም አብዛኛውን ጊዜ የሚተገብሯቸውን ብልሀቶች መሆናቸውን ገልፀዋል፡፡

ለጥያቄ ተ.ቁ.12ም ሁለቱም ብዙውን ጊዜ የሚል ምላሽ ነው የሰጡት፡፡ ለጥያቄ ተ.ቁ.13. አንደኛው መምህር በታሪክ መነሻነት ተማሪዎች አስፋፍተው እንዲፅፉ ማድረግ ልምድ እንዳላቸው የገለፁ ሲሆን አንደኛዋ መምህርት አንዳንድ ጊዜ ብቻ የሚያከናውኑት ተግባር መሆኑን ገልፃለች፡፡

በጥ.ተ.ቁ. አራት ቀደም ሲል በ4.2.2 ስር ግንዛቤ ይሰጣሉ ወይስ አይሰጡም የሚለውን ምላሽ በመውሰድ ብቻ መጠቀማችን ይታወሳል፤ በዚህ ክፍል ደግሞ በዚሁ ጥያቄ ላይ መምህራኑ የመጻፍ ክሂል እንዴት እንደሚተገብሩ (እንደሚያቀርቡ) ከሰጡት ዝርዝር ምላሽ በመነሳት የሚጠቀሙባቸውን ዘዴዎችና ብልሀቶችን ለመመርመር ጠቅለል አድርገን እንመለከታለን፡፡

- በተማሪው መማርያ መጽሐፍ የቀረቡትን አንዳንዴ በግል የምናቀርባቸውን ምንባቦች የተወሰኑት እንዲያነቡ፣ ሌሎች እንዲያዳምጡ ከምንባቡ ያገኙትን ግንዛቤ እንዲፅፉ በማድረግ፣
- አንድ ተማሪ ሃሳቡን በንግግር ሲገልፅ ሌሎች እንዲያዳምጡ ማስታወሻ እንዲፅፉ በማድረግ በተቻለ መጠን የመጻፍ ክሂላቸውን እንዲያሳድጉ እንጥራለን፡፡

መምህራኑ ከሰጡት ምላሽ በመነሳት በአብዛኛው በመማርያ መጽሐፍ የቀረቡትን ምንባብና ከምንባቡ የወጡ ጥያቄዎችን ተከትለው በዚያው ላይ ብቻ ተማሪዎችን ማወያየት የጥያቄዎችን ምላሽ በፅሑፍ እንደያቀርቡ ማድረግ፣ ምንባቦችን በማንበብ ወይም በማስነበብ ተማሪዎቹ እንዲያዳምጡ በማድረግ፣ በመጽሐፍ ላይ የቀረቡትን ጥያቄዎች በክፍል ስራና በቤት ስራ መልክ ጽፈው እንዲመጡ እንደሚያደርጉ የሚያመለክት ነው፡፡ ነገር ግን ይህ ምላሽ በምልከታ ከተገኘው መረጃ ጋር የሚጋጭ ነው፤ ምክንያቱም በምዕራፍ ሁለት ላይ የተገለፀበትን የተዛማጅ ፅሁፍ ቅኝት መሰረት አድርገን ስንመለከታቸው፣ ከተወሰኑት መምህራን በቀር አብዛኞቹ የተማሪዎቹን ተነሳሳሽነት የሚጨምር ይዘት የማያቀርቡ  መሆኑንና ከሌሎች ዘዴዎችና ብልሀቶች በተሻለ ይተገበሩታል የተባለውን የቡድን ውይይት እንኳን በጥሩ ሁኔታ ተግባራዊ ሆኖ የታየው በአንዱ መምህር ላይ ብቻ መሆኑ ነው፡፡

ስለዚህ ከላይ በመምህራኑ ይተገበራሉ ተብለው የተጠቀሱት ተግባራት አለ ቢባልም እንኳን የሚኖሩት በስም ደረጃ እንጂ በአብዛኛዎቹ መምህራን ትኩረት ተሰጥቶባቸው የሚተገበሩ አለመሆናቸውን ከምልከታ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

በጥያቄ ተ.ቁ. የቀረበው ጥያቄ ተማሪዎች ከትምህርት ጋር በተያያዘ መልኩ ሰዎችን ጠይቀው ወይም የተለያዩ ጽሁፎችን አንብበው ማስታወሻ በመያዝ ዘገባዎችን እንዲያቀርቡና እንዲወያዩ የማድረግ ልምድ አለዎት? ካልሆነስ? ችግሩ ምንድን ነው? የሚል ነበር፡፡ ከሁለቱ መምህራን አንዱ (50%) ተማሪዎች ከትምህርት ጋር በተያያዘ መልኩ ሰዎችን ጠይቀው ወይም የተለያዩ ጽሁፎችን አንብበው ማስታወሻ እንዲወስዱና ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያነቡላቸው፣ እንዲወያዩ የማድረግ ልምድ አለ፤ ገነገር ግን ተግባራዊ የሚሆነው አልፎ አልፎ ለዚያውም በርዕስነት ሲመጣ ካልሆነ ሁልጊዜ ተግባራዊ አላደርገውም የሚል ምላሽ የሰጡ ሲሆን አንዷ መምህርት ግን ይህን አይነት ሁኔታ በብዛት እንደማትጠቀም ገልፃለች፡፡

ከላይ የተሰጡት ተግባራት ለምን አልፎ አልፎ ለዚያውም በርዕስነት ሲመጣ ብቻ እተገብረዋለሁ ብሎ ምላሽ እንደሰጠ ተጠይቆበዋናነት የክፍለ ጊዜውን ማነስ ለዚያውም በሳምንት አንድ ክፍለ ጊዜ ብቻ ከመሆኑ የተነሳ መሆኑን ገልፆአል፡፡

አጠቃላይ ለዚህ ጥያቄ አንዱ መምህር አሉታዊ ምላሽ ሲሰጥ አንደኛዋ መምህርት አዎንታዊ ምላሽ ሰጥታለች፡፡ በእርግጥ ሁለቱም መምህራን የተጠቀሱት ዘዴዎችንና ብልሀቶችን እንደሚጠቀሙባቸው ምልከታ የሚያሳይ ቢሆንም ከሁለቱ አንዱ(ዷ) የሚሰጠው (የምትሰጠው)

ምላሽ ከምልከታ ውጤት ጋር የሚጋጭ ነው። ምክንያቱም ሁለቱም በብዛት የሚጠቀሙባቸው ከሆነ ምልከታ በተደረገባቸው ክፍለጊዜያት ውስጥ መታየት ነበረበትና ነው።

### 4.4.3. ለተማሪዎች ከቀረበ የፅሁፍ መጠይቅ የተገኘ መረጃ

በሰንጠረዥ 5 መምህራን የመጻፍክ ክሂልን ለማስተማር የሚጠቀሙባቸው ዘዴዎች ወይም ብልሀቶች ለመመርመር እና ለማወቅ ከተማሪዎች የተሰጠ የፅሁፍ መጠይቅ ምላሽ

በዚህ ክፍል ከፅሁፍ የተገኙትን ለማመልከት በቀረቡት ሰንጠረዦች ላይ "ሀ" ሁልጊዜ፣ "ለ" ብዙውን ጊዜ፣ "ሐ" በመጠኑ፣ "መ" አንዳንድ ጊዜና "ሠ" በጭራሽን ያመለክታሉ፡

| ተ/ቁ | የቀረቡት ጥያቄዎች | ሀ | ለ | ሐ | መ | ሠ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 7 | የአንድንተውኔት፣አጭር ልቦለድ ወዘተ ገፀ ባህርያት ወክለን በክፍል ውስጥ እናቀርባለን | 6 (4.28) | 9 (6.92) | 33 (25.38) | 38 (29.23) | 44 (33.84) |
| 8 | ድራማዎችን፣ ክርክሮችን፣ ወዘተ ተለማምደን ክፍል ውስጥ የምናቀርብበት ሁኔታ ይመቻችልናል። | 9 (6.92) | 12 (9.23) | 20 (15.38) | 29 (22.30) | 60 (46.15) |

ከሠንጠረዥ 5 መረዳት እንደሚቻለው የ7ኛው ጥያቂ ከ130 ተማሪዎች 6ቱ (4.28%) ሁልጊዜ 9 (6.92%) ብዙ ጊዜ 33ቱ (25.38%) በመጠኑ 38ቱ (29.23%) አንዳንድ ጊዜ፣ 44ቱ (33.84%) በጭራሽ የሚል ምላሽ የሰጡ ሰሆን 8ኛው ጥያቂ 9ኙ (6.92%) ሁልጊዜ፣ 12ቱ (9.23%) ብዙ ጊዜ 20 (15.38%) በመጠኑ፣ 29ኙ (22.3%) አንዳንድ ጊዜ፣ 60ዎቹ (46.15%) የሚል ምለሽ ሰጥተዋል። ከነዚህ መረጃዎች በመነሳት በክፍል ውስጥ የሚተገበረው ሚና ጨዋታ በጣም አነስተኛ ነው ማለት ይቻላል።

በአጠቃላይ ከምልከታ፣ ከቃለመጠይቅ የተገኘው ምላሽ መምህራን የመጻፍ ክሂልን ትኩረት ሰጥተው በማስተማር በተወሰነ ደረጃ ተመሳሳይነት ያላቸው መሆኑ ነው። ተማሪዎች በመፅሀፍ ላይ የቀረቡ ምንባቦችን እንዲያነቡ፣ በምንባብ ሀሳብና ጥያቄዎች ላይ እንዲወያዩ፣ የተወያዩትን በፅሑፍ እንዲያቀርቡ በመምህራን ተግባራዊ ተደርገዋል። ከተማሪ መጽሐፍ ውጭ

የተማሪዎችን ፍላጎት የሚጨምር ይዘት ማቅረብ ተማሪዎችን በሚና ጨዋታ ማሳተፍ፣ በተማሪዎች መሃል የነቃ ክርክር እንዲኖር ማድረግ በአንዱ መምህር ብቻ የተተገበረ ነበር፡፡

በክለሳ ድርሳናት እንደተጠቀሰው መጻፍ አዲስ ሀሳብን የማመንጨት ዘዴ በመሆኑ ሀሳብን በሚታይ እና ግልፅ በሆነ መልኩ መዝግቦ ለሌሎች ለማስተላለፍ ምሁራን እውቀታቸውን እንዲያንፀባርቁ አስፈላጊ ይሆናል በማለት (Triyohub)ያስረዳሉ፡፡

ይህ ተግባራዊ የሚሆነው ደግሞ ሁሉም ዘዴዎች ወይም ብልሀቶች በተገቢው መጠን መተግበር ሲችሉ ነው፡፡ ለመምህራን ከተሰራጨው የፅሁፍ መጠይቅ መረጃ የተገኘውም መምህራን በአብዛኛው ተማሪዎች በቡድን ተወያይተው በጽሑፍ እንዲያቀርቡ በማድረግ ሂደትን የሚከተሉ ሲሆን ይዘት ተኮር፣ ተግባር ተኮር፣ ስነ-ፅሁፍ በመጠቀም በሚና ጨዋታና የፕሮጀክት ስራዎችን የማሰራት ሁኔታ እጅግ አናሳ መሆኑ ታውቋል፡፡

እነዚህን ዘዴዎችና ሂደቶች ለምን እንደማይጠቀሙ ተጠይቀው ሁለቱም መምህራን ያለውን የክፍለ ጊዜ ማነስ እንደ ችግር ጠቅሰዋል፡፡ ለተማሪዎች ከተሰራጨው የፅሁፍ መጠይቅ የተገኘው መረጃ ከላይ የቀረቡትን መረጃዎች የሚያጠናክር ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በተለያየ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች የተገኙት መረጃዎች ሲጠቃለሉ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ከክፍለ ጊዜ ማነስ አንፃር ሲታይ የሚጠቀሙት ብልሃት ተማሪዎች ውይይት አድርገው ሀሳባቸውን በቃል እንዲያቀርቡ የማድረግ ሂደትን ነው፡፡

ይህ ግን የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል ብቃት ለማሳደግ የሚያስችልና ብቁ አይደለም፡፡ የተለያዩ ዘዴዎችን ወይምብልሃቶችን በመጠቀም ብዙውን ጊዜ በቃል ከመናገር ይልቅ አንዳንድ ርዕሶችን በመስጠት ተማሪዎች ተወያይተው በፅሑፍ እንዲመልሱ በማድረግ የተማሪዎችን የፅህፈት ብቃት ማሳደግ ይችሉ ነበር፡፡

## 4.5.መምህራን የመጻፍ ክሂሎትን የማሳደግ ሚና

### 4.5.1.ከምልከታ የተገኘ መረጃ

**ሠንጠረዥ 6፡- የመምህራን ሚናን ለማወቅ ከምልከታ የተገኘ መረጃ**

| ተ/ቁ | ዝርዝር የምልከታ ነጥብ | ሀ/ለ | ሐ | መ | ሠ |
|---|---|---|---|---|---|
| 2.1 | መምህሩ/ዋ ተማሪዎች ቋንቋውን ለትክክለኛ ዓላማ እንዲጠቀሙበት የማድረግ ጥረት | 4 (40%) | 3 (30%) | 2 (20%) | 1 (10%) |
| 2.2 | ተግባቦታዊ አቀራረብ የመጠቀም ሁኔታ | 2 (20%) | 3 (30%) | 4 (40%) | 1 (10%) |
| 2.3.1 | ተማሪዎች በራሳቸው ርዕስ መርጠው ድርሰት እንዲፅፉ የማድረግ ሁኔታ | 5 (50%) | 2 (20%) | 2 (20%) | 1 (10%) |
| 2.3.2 | የምንባብ ሀሳብን በራሳቸው አባባል እንዲፅፉ የማድረግ ሁኔታ | 3 (30%) | 2 (20%) | 3 (30%) | 2 (20%) |
| 2.3.3 | በምንባብ መነሻነት ሀሳቦችን አመንጭተው እንዲፅፉ የማድረግ ሁኔታ | 3 (30%) | 1 (10%) | 5 (50%) | 1 (10%) |
| 2.4 | ተማሪዎች ሀሳባቸውን በትክክል በፅሁፍ እንዲገልፁ በቂ ጊዜ የመስጠት ሁኔታ | 4 (40%) | 3 (30%) | 2 (20%) | 1 (10%) |
| 2.5.1 | ተማሪዎች እርስ በርስ እንዲከራከሩ የማድረግ ሁኔታ | 2 (20%) | 3 (30%) | 3 (30%) | 2 (20%) |
| 2.5.2 | እርስ በርስ እንዲወያዩ የማድረግ ሁኔታ | 4 (40%) | 2 (20%) | 4 (40%) | 0 |
| 2.5.3 | እርስ በእርስ እንዲተራረሙ የማድረግ ሁኔታ | 2 (20%) | 3 (30%) | 4 (40%) | 1 (10%) |

ከላይ ከቀረቡት 9 ነጥቦች ውስጥ ማለትም (2.3.2፣ 2.3.3.እና2.5.2) መምህራኑ የሚጠቀሙባቸው ዘዴዎች ወይም ብልሀቶች ለማወቅ ተግባር ላይ የዋሉ ሲሆን መምህራን ሚናቸውን እንደሚወጡ ለማወቅ በድጋሚ እንመለከታቸዋለን፡፡

በሰንጠረዥ 6 ላይ እንደሚታወቅ በሁለቱ መምህራን ላይ በተደረጉት ተከታታይ ምልከታዎች ውስጥ ተ.ቁ. 2.1 የምልከታ ነጥብ የተገኘው ምላሽ ተተኳሪ መምህራኑ ተማሪዎች ቋንቋውን ለትክክለኛ አላማ አውለው እንዲጠቀሙበት ያደረጉት ጥረት ከ10 ተከታታይ ምልከታዎች 4 (40%) ጊዜ ከፍተኛ፣ 3 (30%) ጊዜ መካከለኛ፣ 2 (20%) ጊዜ አነስተኛ እና 1 (10%) ጊዜ በጣም አነስተኛ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል። ለጥያቄ ተ.ቁ.2.2. የምልከታ ነጥብ መምህራን ተግባቦታዊ ስልት ትምህርትን የተጠቀሙባቸው ክፍለ ጊዜያት ከ10ሩ ምልከታዎች 2 (20%) ከፍተኛ፣ 3 (30%) መካከለኛ፣ 4 (%) አነስተኛ እና 1 (10%) በጣም አነስተኛ እንደሆነ ተረጋግጧል። ለጥያቄ ተ.ቁ. 2.3.1. መከታተያ ነጥብ ተማሪዎች በራሳቸው ርዕስ መርጠው ድርሰት እንዲፅፉ ያደረጉባቸው ክፍለ ጊዜያት 5 (50%) ጊዜ ከፍተኛ፣ 2 (20%) ጊዜ መካከለኛ፣ 2 (%) ጊዜ አነስተኛ እና 1 (10%) ጊዜ በጣም አነስተኛ ሆኗል።

ለጥያቄ ተ.ቁ.2.3.2. መከታተያ ነጥብም የምንባቡን ሀሳብ በራሳቸው አባባል እንዲፅፉ የተደረገው 3 (30%) ጊዜ ከፍተኛ፣ 2 (20%) ጊዜ መካከለኛ፣ 3 (30%) ጊዜ አነስተኛ እና 2 (20%) ጊዜ በጣም አነስተኛ መሆኑ ታውቋል። ለጥ.ተ.ቁ.2.3.3. መከታተያ ነጥብ በምንባቡ መነሻነት ሀሳቦችን አመንጭተው እንዲፅፉ የተደረገው 3 (30%) ጊዜ ከፍተኛ፣ 1 (10%) ጊዜ መካከለኛ፣ 5 (50%) ጊዜ አነስተኛ 1 (10%) ጊዜ በጣም አነስተኛ መሆኑ ታውቋል።

ለጥ.ተ.ቁ. 2.4. መከታተያ ነጥብ ተማሪዎች ሀሳባቸውን በትክክል በፅሁፍ እንዲገልፁ በቂ ጊዜ የመስጠት ሁኔታ 4 (40%) ጊዜ ከፍተኛ፣ 3 (30%) ጊዜ መካከለኛ፣ 2 (20%) ጊዜ አነስተኛ እና 1 (10%) ጊዜ በጣም አነስተኛ ነው። ለጥያቄ ተ.ቁ. 2.5.1 መከታተያ ነጥብ በተደረጉት ተከታታይ ምልከታዎች ተማሪዎች እርስበርስ እንድከራከሩ የማድረግ ሁኔታ 2 (20%) ጊዜ ከፍተኛ፣ 3 (30%) ጊዜ መካከለኛ፣ 3 (30%) ጊዜ አነስተኛ እና 2 (20%) ጊዜ በጣም አነስተኛ ነበር። ለጥ.ተ.ቁ. 2.5.2 መከታተያ ነጥብ እርስ በርስ እንድወያዩ የማድረግ ሁኔታ 4 (40%) ጊዜ ከፍተኛ፣ 2 (20%) ጊዜ መካከለኛ፣ 4 (40%) ጊዜ አነስተኛ  መሆኑ ታውቋል።

ከፍ ሲል በዝርዝር ከቀረበው መረጃ የሚገረዳው ሚናቸውን የሚወጡ፣በመጠኑ የሚወጡ እና የማይወጡ መምህራን እንዳሉ ነው።ከሰንጠረዥ 6 የተገኘው መረጃ እንደሚያስረዳው በመከታተያ ከቀረቡት 9 የመከታተያ ነጥቦች 6ቱ ከፍተኛ ሲሆኑ 3ቱ የመከታተያ ነጥቦች አነስተኛ ሆነዋል።

## 4.6 መምህራን የመጻፍ ክሂሎትን ለማስተማር ተግባራቸውን በአግባቡ ስለመወጣታቸው

### 4.6.1 ከምልከታ የተገኘ መረጃ

**ሰንጠረዥ 7፦የመምህራን ተግባር ለማወቅ ከምልከታ የተገኘ መረጃ**

| ተ/ቁ | ዝርዝር የምልከታ ነጥቦች | ሀ/ለ | ሐ | መ | ሠ |
|---|---|---|---|---|---|
| 2.6 | የትምህርቱን ይዘት ነባራዊነት ባለው መልኩ የማቅረብ ሁኔታ | 4 (40%) | 3 (30%) | 1 (10%) | 2 (20%) |
| 2.7 | ተማሪዎች በቋንቋው እንዲጠቀሙ የማድረግ ሁኔታ | 4 (40%) | 3 (30%) | 2 (20%) | 1 (10%) |
| 2.8.1 | ተማሪዎች በሚከራከሩበት እና በሚወያዩበት ጊዜ ክትትል የማድረግ ሁኔታ | 3 (30%) | 2 (20%) | 4 (40%) | 1 (10%) |
| 2.8.2 | እርማት (ማስተካከያ) የመስጠት ሁኔታ | 4 (40%) | 3 (30%) | 2 (20%) | 1 (10%) |
| 2.9 | ከተማሪ መጽሐፍ ውጪ የተማሪዎችን ፍላጐት የሚጨምር ይዘት የማቅረብ ሁኔታ | 2 (20%) | 3 (30%) | 4 (40%) | 1 (10%) |
| 2.10 | ተማሪዎችን የማሳተፍ ሁኔታ | 4 (40%) | 2 (20%) | 3 (30%) | 1 (10%) |
| 2.11 | ተማሪዎች በተግባራት እንዲሳተፉ የማድረግ ሁኔታ | 4 (40%) | 2 (20%) | 4 (40%) | 0 |
| 2.12 | ከተማሪ ልምድ ጋር የተገናዘበ ጥያቄዎችን የማቅረብ ሁኔታ | 4 (40%) | 3 (30%) | 1 (10%) | 2 (20%) |

ለጥያቄ ተ.ቁ.2.6. እና 2.12 የምልከታ ነጥቦች የተገኘው ምላሽ በተደረጉት ተከታታይ ምልከታዎች የትምህርቱ ይዘት ነባራዊነት ባለው መልኩ እና ከተማሪ ልምድ ጋር የተገናዘበ ጥያቂ ቀርቦ 4 (40%) ከፍተኛ፣ እና በ2 (20%) ጊዜ በጣም አነስተኛ ሆኗል፡፡ ለጥ.ተ.ቁ. 2.8.2 መከታተያ ነጥብ ለተማሪዎች እርማት የመስጠት ሁኔታ 4 (40%) ጊዜ ከፍተኛ እና 1 (10%) ጊዜ በጣም ዝቅተኛ ሲሆን ለጥ.ተ.ቁ.2.9 መከታተያ ነጥብ ከተማሪዎች መጽሐፍ ውጪ የተማሪዎችን ፍላጐት የሚጨምር ይዘት የማቅረብ ሁኔታ 2 (20%) ጊዜ ከፍተኛ፣ 3 (30%) ጊዜ መካከለኛ፣ 4 (40%) ጊዜ አነስተኛ እና 1 (10%) ጊዜ በጣም ዝቅተኛ ነበር፡፡

ለጥ.ተ.ቁ. 2.10 መከታተያ ነጥብ ተማሪዎችን የማሳተፍ ሁኔታ 4 (40%) ጊዜ ከፍተኛ፣ 2 (20%) ጊዜ መካከለኛ፣ 3 (30%) ጊዜ አነስተኛ፣ 1 (10%) ጊዜ በጣም አነስተኛ መሆኑን

ለመረዳት ተችሏል፡፡ ከሰንጠረዥ 6 እና 7 መረዳት እንደተቻለው ሁለቱም መምህራን ተማሪዎች እንዲወያዩ ድርሰት እንዲፅፉ፣ ተማሪዎች በቋንቋ እንዲጠቀሙ የሚያደርጉ ሲሆን ሌሎች ተግባራት ላይ ትንሽ ደከም የማለት አተገባበር ተስተውሏል፤ ይህ ደግሞ የመጻፍ ክሂልን የማሳደጉን ሁኔታ ዝቅ ያደርገዋል፡፡

በአጠቃላይ ሲታይ ከምልከታው የተገኘው መረጃ የመጻፍ ክሂልን ለማሳደግ መምህራኑ ሚና እና ተግባራቸውን በመካከለኛ ሁኔታ እየተወጡ እንዳለ ለማወቅ ተችሏል፡፡

## 4.6.2. የመምህራንን ሚና እና ተግባር ለማወቅ ለመምህራን ከቀረበው ቃለ መጠይቅ የተገኘ መረጃ

በዚህ ክፍል መምህራን የመጻፍ ክሂልን የማሳደግ ሚና እና ተግባራቸው ምን እንደሚመስል ለመመርመር መምህራን የሚጠቀሙባቸውን ዘዴዎች ወይም ብልሃቶች ለመመርመር ተግባር ላይ የዋለውን ጥ.ተ.ቁ 6፣ 10፣11፣13፣14ን ለመጠቀም ታምኖበታል፡፡

ለጥ.ተ.ቁ.6 ተማሪዎች ከትምህርቱ ጋር በተያያዘ መልኩ ሰዎችን ጠይቀው ወይም የተለያዩ ጽሑፎችን አንብበው ማስታወሻ እንዲወስዱ እና ዘገባዎችን እንዲያቀርቡና እንዲወያዩ የማድረግ ልምድ አሉት? እንዴት? የሚል ሲሆን ከሁለቱ ተተኳሪ መምህራን 1 (50%) አልፎ አልፎ አንዷ መምህርት ግን በብዛት ተግባራዊ እንደምታደርግ ገልፃለች፡፡

በጥ.ተ.ቁ.10 ተማሪዎች አንድን ንግግር አዳምጠው የተረዱትን ሀሳብ እንዲፅፉ ያደርጋሉ የሚል ሲሆን አንደኛው መምህር አብዛኛውን ጊዜ የሚል ሲሆን ሌላኛዋ መምህርት አንዳንድ ጊዜ የሚል ምላሽ ሰጥታለች፡፡ ለጥያቄ ተ.ቁ.11 ተማሪዎች የተለያዩ ርዕሶችን መርጠው እንዲወያዩ እና እንዲከራከሩ ያደርጋሉ ለሚለው ጥያቄ አብዛኛውን ጊዜ የሚተገብሯቸው ብልሀቶች መሆናቸውን ገልፀዋል፡፡

ለጥ.ተ.ቁ. 13 የሚያነቡላቸውን ምንባቦች መነሻ በማድረግ የራሳቸውን ፈጠራ በማከል አስፋፍተው እንዲፅፉ ያደርጋሉ ለሚለው ጥያቄ አንደኛው መምህር በታሪክ መነሻነት ተማሪዎች አስፋፍተው እንዲፅፉ የማድረግ ልምድ እንዳለ የገለፀ ሲሆን አንደኛዋ መምህርት አንዳንድ ጊዜ ብቻ የሚያከናውኑት ተግባር መሆኑን ገልፃለች፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በጥ.ተ.ቁ.14 ላይ ተማሪዎች የሚጽፏቸውን ፅሁፎች ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያነቡላቸው ያደርጋሉ? የሚል ጥያቄ ቀርቦ ሁለቱም መምህራን የብዙ ጊዜ ተግባራቸው መሆኑን ገልፀዋል፡፡

በአጠቃላይ እነዚህን ዘዴዎች ወይም ብልሀቶችን በመጠቀም ሚናና ተግባራቸውን ሁለቱም መምህራን የተወሰኑ ሙከራዎችን ከማድረግ ባለፈ እነሱ እንደሰጡት ምላሽ በብዛት የሚተገብሯቸው ተግባራት አለመሆናቸውን ከምልከታው ለማወቅ ተችሏል፡፡

### 4.6.3 ለተማሪዎች ከቀረበው የጸሑፍ መጠይቅ የተገኘ መረጃ

***ሠንጠረዥ 7 መምህራን የመጻፍ ክሂልን ለማሳደግ ያላቸው ሚናና ተግባራቸው ምን እንደሚመስል ለማወቅ ከተማሪዎች የተገኘ የፅሑፍ ምላሽ፡፡***

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | ሀ | ለ | ሐ | መ | ሠ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የጥንደና የቡድን ተግባራት እንድናከናውን ያደርጋሉ | 30 (23.07) | 40 (30.76) | 30 (23.07) | 20 (15.38) | 10 (7.69%) |
| 4 | ተግባራትንስናከናው በመምህራን ተገቢ የሆነ ድጋፍና ክትትል ይደረግልናል | 26 (20%) | 30 (23.07) | 36 (27.69) | 22 (16.92) | 16 (12.3%) |
| 6.1 | በየግላችን የተለያዩ ጽሑፎችን እንድናነብ ይደረግልናል | 28 (21.53) | 40 (30.76) | 30 (23.07) | 20 (15.38) | 12 (9.23%) |
| 6.2 | በየግላችን ጽሑፎችን እንድንፅፍ ደርጋሉ | 26 (20%) | 20 (15.38) | 40 (30.76) | 12 (9.23%) | 32 (24.6%) |
| 9 | አዳዲስ ተግባራትን እንድናመነጭ ከመምህራችን የሞራል ድጋፍ ይደረግልናል | 42 (32.3%) | 28 (21.53) | 30 (23.07) | 20 (15.38) | 7 (5.38%) |

ከሰንጠረ¾ዥ 7 መረዳት እንደሚቻለው ለጥያቄ ቁ. 1 ከ130 ተማሪዎች ውስጥ 70 (53.84%) ሁልጊዜና ብዙውን ጊዜ የሚል ምላሽ የሰጡ ሲሆን 30 (23.07%) በመጠኑ፣ 20 (15.38%) አንዳንድ ጊዜና 10 (7.69%) በጭራሽ የሚል መልስ ሰጥተዋል፡፡ ለጥ.ተ.ቁ. 4 68 (43.07%) ሁልጊዜ እና ብዙውን ጊዜ የሚል ምላሽ የሰጡ ሲሆን 36 (27.69%) በመጠኑ፣ 22 (16.92%) አንዳንድ ጊዜ እና 16 (12.3%) በጭራሽ የሚል ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ ለጥ.ተ.ቁ. 6.1፣ 68 (52.3%) ሁልጊዜ እና ብዙውን ጊዜ የሚል ምላሽ ሲሰጡ 30 (23.07%) በመጠኑ 20 (15.38%) አንዳንድ ጊዜ እና 12 (9.23%) በጭራሽ የሚል ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ ጥ.ተ.ቁ. 6.2 46 (35.38%) ሁልጊዜ እና ብዙውን ጊዜ የሚል ምላሽ የሰጡ ሲሆን 40 (30.76%) በመጠኑ 12 (9.23%) አንዳንድ ጊዜ እና 32 (24.6%) በጭራሽ የሚል መልስ ሰጥተዋል፡፡

ጥ.ተ.ቁ.5. 70 (53.84%) ሁልጊዜ እና ብዙውን ጊዜ የሚል ምላሽ ሲሰጡ 30 (23.07%) በመጠኑ 6.20 (15.38%) አንዳንድ ጊዜ እና 7 (5.38%) በጭራሽ የሚል መልስ ሰጥተዋል፡፡

## 4.7 ተማሪዎቸ የመጻፍ ክሂልን ለመማርና ለመጠቀም ያላቸው ፍላጐት

በመደበኛ የመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ በዋናነት የሚጠቀሱት ይዘት መምህሩና ተማሪዎች ናቸው፡፡ ቀደም ሲል በተለያዩ መርጃ መሳሪያዎች አማካኝነት ትንታኔ የተሰጠባቸው ጥያቄዎች አጠቃላይ ትኩረት የነበረው ይዘቱና መምህሩ ላይ ሲሆን የነዚህ ጥምረት ውጤት ተጠቃሚም ተማሪው መሆኑ እሙን ነው፡፡ የዚህ ጥናት አላማ የመጻፍ ክሂል አተገባበር እና የተማሪዎችን ተነሳሽነት መመርመር እንደመሆኑ መጠን በእያንዳንዱ መምህራን ላይ አምስት፣ አምስት ተከታታይ ክፍለ ጊዜያት የነበሩት የቋንቋ ማስተማሪያ ይዘቶች እና የመምህሩ አተገባበር በስፋት ተዳሷል፡፡ ከላይ ለመግለፅ እንደተሞከረው የመጻፍ ክሂልን አቀናብሮ ለማቅረብ የሚያመቹ ይዘቶችን መርጦ በሚገባ መተግበር ተማሪዎች ብቁ የቋንቋ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማስቻል ነው፡፡ ለዚህ ደግሞ የተማሪዎች ተነሳሽነት ከፍተኛ ድርሻ ይኖረዋል፡፡ በመሆኑም የተማሪዎችን ተነሳሽነት ለመመርመር ከምልከታ እና ከቃለመጠይቅ የተገኙ መረጃዎች በሁለት መሰረታዊ ነጥቦች ስር እንደሚከተለው ይተነተናሉ፡፡

### 4.7.1 ከምልከታ የተገኘ መረጃ ትንተና

**ሰንጠረዥ 8 ተማሪዎች የመጻፍ ክሂልን ለመማርና ለመጠቀም ያላቸውን ፍላጐት ለመመርመር ከምልከታ የተገኘ መረጃ**

| ተ/ቁ | የመከታተያ ነጥብ | ሀ/ለ | ሐ | መ | ሠ |
|---|---|---|---|---|---|
| 3.1. | አዳምጠው ለመጻፍ የሚያሳዩት ፍላጎት | 3 (30%) | 4 (40%) | 2 (20%) | 1 (10%) |
| 3.2. | ለመናገር የሚያሳዩት ፍላጎት | 3 (30%) | 2 (20%) | 3 (30%) | 1 (10%) |
| 3.3. | አንብበው ለመጻፍ የሚያሳዩት ፍላጐት | 4 (40%) | 2 (20%) | 3 (30%) | 1 (10%) |
| 3.4. | ከተለዩ መረጃ ምንጮች ያገኙት እውቀት በፅሁፍ ለማቅረብ ያላቸው ፍላትት | 3 (30%) | 1 (10%) | 4 (40%) | 2 (20%) |
| 3.5. | በክፍል ውስጥ የሚያሳዩት ተሳትፎ | 4 (40%) | 3 (30%) | 2 (20%) | 1 (10%) |
| 3.6. | ሀሳባቸውን አደራጅተው በፅሁፍ የመግለፅ ሁኔታ | 4 (40%) | 3 (30%) | 2 (20%) | 1 (10%) |
| 3.7 | ለመከራከር /ለመወያየት/ የሚያሳዩት ፍላጐት | 3 (30%) | 2 (20%) | 4 (40%) | 1 (10%) |

በሰንጠረዥ 8 እንደሚታየው የመከታተያ ምልከታዎች ውስጥ ተማሪዎች አዳምጠው ለመጻፍ የሚያሳዩት ተነሳሽነት በ3 (30%) ክፍለ ጊዜያት ከፍተኛ በ4 (40%) መካከለኛ በ2 (20%) አነስተኛ በ1 (10%) በጣም አነስተኛ ሆኗል። በጥያቄ ተራ ቁጥር 2.3. በ3 (30%) ክፍለ ጊዜ ከፍተኛ፣ 2 (200%) መካከለኛ፣ በ3 (30%) አነስተኛ፣ በ3 (30%) ክፍለ ጊዜ አነስተኛ እና በ1 (10%) ክፍለ ጊዜ በጣም አነስተኛ ሲሆን፤ በጥ.ተ.ቁ. 3.3 በ4 (40%) ክፍለ ጊዜ ከፍተኛ፣ በ2 (20%) ክፍለ ጊዜ መካከለኛ፣ በ3 (30%) ክፍለ ጊዜ አነስተኛ እና በ1 (10%) ክፍለ ጊዜ በጣም አነስተኛ ነበር። በጥ.ተ.ቁ.4 በ3 (30%) ክፍለ ጊዜ ከፍተኛ፣ በ1 (10%) ክፍለ ጊዜ መካከለኛ፣ በ4 (40%) ክፍለ ጊዜ አነስተኛ እና በ2 (20%) ክፍለ ጊዜ በጣም አነስተኛ ሆኗል። በጥያቄ ተ.ቁ.3.5 በ4 (40%) ክፍለ ጊዜ ከፍተኛ፣ በ3 (30%) ክፍለ ጊዜ መካከለኛ፣ በ2 (20%) ክፍለ ጊዜ አነስተኛና በ1 (10%) ክፍለ ጊዜ በጣም አነስተኛ ሲሆን በጥያቄ ተ.ቁ. 3.6 በ4 (40%) ክፍለ ጊዜ ከፍተኛ፣ በ3 (30%) ክፍለ ጊዜ መካከለኛ፣ በ2 (20%) ክፍለ ጊዜ አነስተኛ እና በ1 (10%) ክፍለ ጊዜ በጣም አነስተኛ ሆኗል።

በጥ.ተ.ቁ. 3.7 በ3 (30%) ክፍለ ጊዜ ከፍተኛ፣ በ2 (20%) ክፍለ ጊዜ መካከለኛ፣ በ4 (40%) ክፍለ ጊዜ አነስተኛ እና በ1 (10%)ክፍለ ጊዜ በጣም አነስተኛ ነበር። በዚህ ክፍል መግያ ላይ የመጻፍ ክሂልን ለማሳደግ የሚያስችል ይዘት ተመርጦ በሚገባ ቢተገበር ተማሪው ዋነኛ ተጠቃሚ እንደሚሆን ተገልፆአል። ከላይ በዝርዝር የቀረበ መረጃም ይህንን የሚያመለክት ሆኖ ተገኝቷል። ይህም የመምህሩ የትምህርት አቀራረብ በተማሪዎች አቀባበል ላይ ከፍተኛ ደረጃ እንዳለው የሚያመላክት ነው።

ከተገኘው የምልከታ ውጤት በመነሳት ትክክለኛ የመጻፍ ክሂል አተገባበር ባሉበት ክፍል ውስጥ ተማሪዎች አዳምጠው ለመጻፍ ያላቸው ፍላጐት፣ ካነበቡት ምንባብ ያገኙት እውቀት በፅሑፍ ለማቅረብ ያላቸው ፍላጐት፣ ከተለያዩ መረጃ ምንጮች ያገኙትን እውቀት በፅሁፍ ለማቅረብ ያላቸው ፍላጐት ከፍተኛ፣ መካከለኛ ሁኔታ፣ በሚተገበርበት ክፍል ውስጥ መጠነኛ እና ትክክለኛ አተገባበር በሌለበት ሁኔታ ላይ እጅግ ዝቅተኛ የሆነ የመማር ፍላጐት እንዳለ ለማወቅ ተችሏል። ስለሆነም ከሁለቱ መምህራን አንዱ መምህር የመጻፍ ክሂልን ጥሩ በሆነ ሁኔታ ባቀረቡላቸው ክፍለ ጊዜያት ተማሪዎች ክሂሉን ለመማር እና ለመጠቀም ያሳዩት ፍላጐት ከፍተኛ፣ መካከለኛ አቀራረብ በነበረበት ክፍለ ጊዜያትም መጠነኛና ደካማ አቀራረብ በነበረበት ክፍለ ጊዜያት በግል ወሬና መሳሳቅ መበራከት የፍላጐት ማጣት ውጤቶች ተስተውለዋል።

### 4.7.2 ለተማሪዎች ከቀረቡት የፅሁፍ መጠይቅ የተገኘ መረጃ ትንተና

**ሰንጠረዥ 9 ተማሪዎች የመጻፍ ክሂልን ለመማር እና ለመጠቀም ያላቸው ፍላጐት ለመጨመር ከተማሪዎች የተገኘ የፅሁፍ ምላሽ**

| ተ/ቁ | ጥያቄዎች | ሀ | ለ | ሐ | መ | ሠ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 10. | አዲስ ተግባራትን ለማመንጨት ያለኝ ፍላጐት | 6.3 (48.46%) | 30 (23.07%) | 21 (16.15%) | 11 (8.46%) | 5 (3.84%) |
| 11 | ተግባራትን መነሻ በማድረግ በክፍልም ሆነ ውጭ የሚሰጡትን ተግባራት ለመስራት ያለኝ ፍላጐት | 17 (51.5%) | 23 (17.69%) | 35 (26.9%) | 5 (3.84%) | |

በሰንጠረዥ 9 ላይ የተገኘው መረጃ በምልከታ ከተገኘው መረጃ ጋር ሲታይ ለተማሪዎች የትምህርት አቀባበል መምህራን ወሳኝ ሚና እንዳላቸው የሚያመለክት ነው፡፡ ተማሪዎቹ አዳዲስ ተግባራትን ለማመልከት የተለያዩ ተግባራትን ለማከናወን ከፍተኛ ፍላጐት እንዳላቸው የገለፁ ሲሆን በሰንጠረዥ 9 ላይ የቀረበው መረጃ ላይ አሁን የተገኘው ምላሽ ተፈጻሚ እንዲሆን መምህራን ሁኔታዎችን ማመቻቸት እንዳለባቸው ጠቋሚ ነው፡

## 4.8. ተማሪዎች በመጻፍ ክሂል ትምህርት ወቅት ሚናቸውንና ተግባራቸውን በአግባቡ ስለመወጣታቸው

የመጻፍ ክሂል ትምህርት አቀራረብ የታለመበትን አላማ ያሳካ ዘንድ ተማሪዎች ከፍተኛ ድርሻ አላቸው፡፡

### 4.8.1. ከምልከታ የተገኘ መረጃ

**በሰንጠረዥ 10 የተማሪዎችን ሚናና ተግባር ለማወቅ ከምልከታ የተገኘ መረጃ**

| ተ/ቁ | የመከታተያ ነጥብ | ሀ/ለ | ሐ | መ | ሠ |
|---|---|---|---|---|---|
| 3.9 | ተማሪዎች ምንባብ ያነባሉ | 4 (40%) | 2 (20%) | 3 (30%) | 1 (10%) |
| 3.9.1. | የምንባቡን ሀሳብ በራሳቸው አባባል ይፅፋሉ | 4 (40%) | 2 (20%) | 3 (30%) | 1 (10%) |
| 3.9.2 | በምንባቡ መነሻነት ሀሳቦችን አመንጭተው ይጽፋሉ | 3 (30%) | 1 (10%) | 5 (50%) | 1 (10%) |
| 3.10. | በተለያዩ ተግባራት ይሳተፋሉ | 5 (50%) | 2 (20%) | 2 (20%) | 1 (10%) |
| 3.11. | በሚሰጧቸው ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ይወያያሉ | 4 (40%) | 2 (20%) | 3 (30%) | 1 (10%) |

ከሠንጠረዥ 10 መረዳት እንደተቻለው ከተከታታይ ምልከታዎች ለጥ.ተ.ቁ.3.9 የተገኘው ምላሽ 4 (40%) ጊዜ ከፍተኛ፣ 2 (20%) ጊዜ መካከለኛ፣ 3 (30%) ጊዜ አነስተኛ 1 (10%) ጊዜ በጣም አነስተኛ የሚሉ ምላሾች ተገኝተዋል፡፡ ለጥ.ተ.ቁ.3.9.1 በ4 (40%) ጊዜ ከፍተኛ፣ 2 (20%) ጊዜ መካከለኛ፣ 3 (30%) ጊዜ ዝቅተኛና 1 (10%) ጊዜ በጣም አነስተኛ የሚል ሆኗል፡፡ ለጥ.ተ.ቁ.3.9.2 3 (30%) ጊዜ ከፍተኛ፣ 1 (10%) መካከለኛ፣ 5 (50%) ጊዜ አነስተኛ እና 1 (10%) ጊዜ በጣም አነስተኛ የሚል ሆኗል፡፡ ለጥ.ተ.ቁ. 3.10 5 (50%) ጊዜ ከፍተኛ፣ 2 (20%) መካከለኛ፣ 2 (20%) አነስተኛ እና 1 (10%) ጊዜ በጣም አነስተኛ ሆኗል፡፡ ለጥያቄ ተ.ቁ.11 4 (40%) ጊዜ ከፍተኛ፣ 2 (20%) ጊዜ መካከለኛ፣ 3 (30%) ጊዜ አነስተኛ እና 1 (10%) ጊዜ በጣም አነስተና መሆኑን ያሳያል፡፡

ከዚህ ጋር በተያያዘ በጥ.ተ.ቁ.9 ላይ ተማሪዎች ክሂሉን ተጠቅመው መልስ ሲሰጡ ትርጉም አዘል ቋንቋን ይጠቀማሉ የሚል ነጥብ ቀርቦ የተገኘው ውጤት በሰንጠረዥ ላይ ከተገኘው ውጤት ጋር ተመሳሳይ በመሆኑ እንደሚከተለው ተጠቃሎ ይቀርባል፡፡ ከመረጃው በመነሳትም ተማሪዎች በመጻፍ ክሂል አቀራረብ ወቅት ሚናና ተግባራቸውን ይወጣሉ፡፡ በመጠኑ ይወጣሉ፣ አይወጡም ብለን መመደብ እንችላለን፡፡ ምክንያቱም ተከታታይ ምልከታ ከተካሄደባቸው 10 ክፍለ ጊዜያት ውስጥ በተወሰኑት በመጻፍ ክሂል አቀራረብ ወቅት ጥሩ በሆነ መልኩ ሚናና ተግባራቸውን የሰጡ ሲሆን፤ አብዛኛው ክፍለ ጊዜያት በመካከለኛ ሁኔታ የሚወጡና ጥቂት ክፍለ ጊዜያት ሚናና ተግባራቸውን የማይወጡ ሁኔታ እንዳለ ከምልከታ ለማወቅ ተችሏል፡፡

## 4.9. የመጻፍ ክሂልን ትኩረት ሰጥቶ ለማቅረብ እንቅፋት የሆኑ ጉዳዮች

### 4.9.1. ለመምህራን ከቀረበ ቃለመጠይቅ የተገኘ መረጃ

የመጻፍ ክሂልን ትኩረት ሰጥቶ ለማቅረብ አሉታዊ ተፅእኖ ያላቸው ሁኔታዎች ካሉ ክሂሉን በተፈለገው መልኩ ማቅረብ አስቸጋሪ ሊሆን ይችላል፡፡ ይህንን ለማወቅ ይቻል ዘንድ ሁለት መጠይቆች የያዙ ቃለ መጠይቅ ለመምህራን ቀርቧል፡፡ የተገኘው መረጃ እንደሚከተለው ተተንትኖ ቀርቧል፡፡

በዚህ ክፍል መምህራን የመጻፍ ክሂል በትኩረት ለማቅረብ አስበው ያጋጠማቸው ችግር እንዳለ ለማወቅ በጥ.ተ.ቁ. የመጻፍ ክሂልን በትኩረት ለማቅረብ አስበው ያጋጠመዎት ችግር ካለ ምን ነበር? በጥ.ተ.ቁ.. 17 ላይ የመጻፍ ክሂልን ትኩረት ሰጥተው የሚያቀርቡ ከሆነ ችግሩ ምንድነው? የሚል ጥያቄ ቀርቦ ለጥ.ተ.ቁ. 5 ሁለቱም መምህራን ተመሳሳይ መልስ ሰጥተዋል፡፡

ይኸውም የክፍለ ጊዜ ማነስ (በሳምንት አንድ ክፍለ ጊዜ መሆን)፣የተማርዎች ፍላጐት ማጣት የሚሉናቸው፡፡

ለጥ.ተ.ቁ. 17 የሰጡት ምላሽ ከመፍትሄው ጋር እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡ አንዷ መምህርት የክሂሉን አቀራረብ በጥልቀት ግንዛቤ የለኝም ስልጠና አግኝቼ አላውቅም፤ መፍትሄው ስልጠና ቢሰጥ መልካም ነው፡፡ ሁለተኛው መምህር አጋዥ መጽሐፍት በት/ቤት ውስጥ ባለመኖራቸው ምክንያት ነው፤ መፍትሄው መጽሐፍ ቢኖር መልካም ነው፡፡

- ተማሪዎች ለትምህርቱ ትኩረት ያለመስጠታቸው ነው፤ መፍትሄው በምናስተምርበት ጊዜ ለሁሉም ተማሪዎች ክትትል ለማድረግ እንድመች በአንድ ክፍል ውስጥ የሚገኝ የተማሪ ብዛት ቢቀንስ የተሻለ ነው፡፡ ሁለቱም መምህራን ከሰጡት መልስ መረዳት እንደተቻለው እና እንደችግር ያነሷቸው ነጥቦች የተማሪዎች ለትምህርት ትኩረት አለመስጠትና የወሰዱት ስልጠና አለመኖር፣ የክፍለ ጊዜ ማነስና አጋዥ መጽሐፍት አለመኖር መሆናቸውን ለማወቅ ተችሏል፡፡

በቋንቋ መማርናማስተማር ሂደት ውስጥ የመጻፍ ክሂልን ለማሳደግ እንደ ችግር ከጠቀሷቸው በዋናነት የተደጋገሙት የክፍለ ጊዜ ማነስ እና የተማሪዎች ፍላጐት ማጣት መሆናቸውን ነው፡፡ ሆኖም ግን እነዚህ የመጻፍ ክሂልን ለማሳደግ እንደችግር ሊጠቀሱ የሚችሉ አይደሉም፡፡

በምዕራፍ ሁለት እንደተጠቀሰው ሰው በመጻፍ በኩል ይማራል፣ ያስባል፣ እውቀትን የግሉ ገንዘብ ማድረግ ይችላል፡፡ የመጻፍ ክሂልን ለማስተማር በክፍል ብቻ የሚያበቃ ስራ ሳይሆን ከክፍል ውጭም ሊተገበር የሚችል ነው፡፡ ይህ ደግሞ መምህራኑ በመጻፍ ክሂል ላይ ያላቸው ግንዛቤ አነስተኛ መሆኑን ያሳያል፡፡

በአጠቃላይ በምዕራፍ አራት ስር የተነሱት ነጥቦች ሲጠቃለሉ የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል ለማሳደግ በየክፍለ ጊዜያቱ የነበሩ ይዘቶች አመቺ ናቸው፡፡በመሆኑም በነዚህ ይዘቶች አማካኝነት የመጻፍ ክሂልን ትኩረት ሰጥቶ የማቅረብ ግንዛቤ ያለው አንዱ መምህር የተለያዩ ዘዴዎች ወይም ብልሀቶችን በመጠቀም ሚናና ተግባሩን የሚወጣ ሲሆን አንዷ መምህርት ግን ይዘቱን ከማቅረብ ውጭ ትኩረት ሰጥታ እንደማታቀርብና የተማርዎች የመጻፍ ክሂል የመማር ፍላጎት ሚናና ተግባራቸውን መወጣት አለመወጣት ከመምህራኑ አቀራረብ ጋር በእጅጉ ቁርኝት እንዳለው ለማወቅ ተችሏል፡፡

## 4.10 የጥናቱ ግኝት ማብራሪያ

በሀገራችን ውስጥ በሚገኙ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በመጻፍ ክሂል ላይ ጥናታቸውን ያደረጉ የመጻፍ ክሂል ማስተማርያ ዘዴ የክፍል ውስጥ አተገባበር ለመመርመር ጥናታቸውን አካሂደዋል፡፡ ከእነዚህ አጥኚዎች ማረው (1987)፣ ስዩም (1988) እና ሰለሞን (1991) ይገኙበታል፡፡ እነዚህ ጥናቶች የፅህፈት ክሂል ትምህርትን ለማስተማር በመማርያ መፃህፍት ውስጥ የቀረቡት ይዘቶች አደረጃጀት ብቁ ሆኖ አለመገኘት፣ የይዘቶችና ክንውኖች የማስተማርያ ዘዴ ትግበራ ተማሪውን የሚያበረታታ ሆኖ ያለመቅረብና የመምህራን ፅህፈትን የማስተማርያ ዘዴያቸው የተማሪዎችን የመጻፍ ስትራቴጂ ብቃት የሚያሳድግ ሆኖ አለመገኘቱን ገልፀዋል፡፡ በአንጻሩ የተማሪዎች የጽህፈት ብቃት ለማሳደግ በቡድን ድርሰት ማጻፍ፣ እርማትና ጽህፈትን በሂደታዊ ዘዴ ማስተማር ለክሂሉ መዳበር ጠቀሜታዎች ሆነው መገኘታቸውን የጠቆሙ ጥናቶች ናቸው፡፡

ከነዚህ ጥናቶች በመነሳት በኦሮሚያ ክልል በደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞን በቀርሳ ማሊማ ወረዳ በሌማን ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች የመጻፍ ክሂል ብቃታቸው ምን ደረጃ ላይ እንደምገኝ ጥናት ተካህዶ የተገኘው ውጤት ስነጻጸር ልዩነት አለው፡፡ይህም ከዚህ በፍት የተካሄዱት ጥናቶች የፅህፈት ክሂል ትምህርት ለማስተማር በመማሪያ መፃህፍት ውስጥ የቀረቡት ይዘቶች ብቁ ሆኖ አለመገኘት የጠቆሙ ናቸው፡፡በአሁኑ ጊዜ ግን በተጨባጭ የሚታየው በኦሮሚያ ክልል በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ፊደላትን በትክክል ሳይለዩ ሁለተኛ ደረጃ ስለሚደርሱ በአማርኛ ቋንቋ ሀሳባቸውን በፅሁፍ በሚገባ መግለፅ ቀርቶ ፊደላትን በትክክል ለይቶ ቃላት መጻፍ ዳገት እንደሚሆንባቸው ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ለዚህም ምክንያት የሆኑት የአከባቢ እና የጊዜ ሁኔታ፣በክልሉ በቋንቋው የሰለጠኑ መምህራን በብዛት አለመኖር እና የክፍለ ጊዜ ማነስ ተማሪዎችለቋንቋነው ትኩረት እንዳይሰጡ እና በቋንቋው ተጠቅመው የመጻፍ ክሂል ብቃታቸውን እንዳያሳድጉ እንቅፋት የሆኑ ጉዳዮች ናቸው፡፡

# ምዕራፍ አምስት

# ማጠቃለያና የመፍትሔ ሃሳቦች

## 5.1.ማጠቃለያ

የዚህ ጥናት ዋና አላማ በኦሮሚያ ክልል በቀርሳ ማሊማ ወረዳ የሌማን ሁለተኛ ደረጃ ትምህርትቤት የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የመጻፍ ክሂልን የማስተማር አተገባበር እና የተማሪዎችን ተነሳሽነት መፈተሽ ነው፡፡ ይህን ዓላማ ከግብ ለማድረስ የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራንና ተማሪዎቻቸውን የጥናቱ ተተኳሪ በማድረግ ምልከታ በተደረገባቸው ክፍለ ጊዜያት የነበሩ ይዘቶች የመጻፍ ክሂልን ለማቅረብ ያላቸው እገዛ ክሂሉን በማስተማር ላይ መምህራኑ ያላቸው ግንዛቤ፣ እውቀት፣ ክሂሉን ለማስተማር የሚጠቀሙባቸው ዘዴዎች ወይም ብልሃቶችን ክሂሉን ትኩረት ሰጥቶ ለማስተማር ሚናና ተግባራቸውን ስለመወጣታቸው፣ ተማሪዎች ክሂሉን ለማዳበርና ለመጠቀም ያላቸው ፍላጐት፣ ተማሪዎች በመጻፍ ክሂል ትምህርት ወቅት ሚናና ተግባራቸውን ስለመወጣታቸውና የማስተማርያ መሳሪያዎቹ የመጻፍ ክሂሉን ለማሳደግ ያላቸው እገዛ ለማወቅ ለ10 ተከታታይ ክፍለ ጊዜያት የክፍል ምልከታ እና ለተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ ተበትኗል፡፡ ከእያንዳንዱ መረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች የተገኘ መረጃ ተተንትኖ የተገኘው ውጤት የሚከተለውን ይመስላል፡፡

ጥናቱ እንደተመለከተው መምህራን በተማሪ መጽሐፍ ላይ የቀረቡትን ይዘቶች ተከትለው ስለሚያስተምሩ በተማሪው መጽሐፍት የቀረቡት ይዘቶች ደግሞ ክሂል ተኮር በመሆናቸው ክሂሉን ለማስተማር አመቺ ናቸው፡፡

በየክፍለ ጊዜው የነበሩት ይዘቶች ተማሪዎች በተለያዩ የቋንቋ ክሂሎች እንዲሳተፉ፣ በቡድንና በጥንድ እንዲወያዩ፣ በክፍልም ሆነ ከክፍል ውጭ የተለያዩ ተግባራትን እንዲያከናውኑ የተመቹ ይዘቶች (ርዕሰ ጉዳዮች) መሆናቸው ተረጋግጧል፡፡

ከሁለቱ መምህራን የመጻፍ ክሂል ትምህርት አቀራረብ ላይ ያላቸው ግንዛቤ አንደኛው ጥሩ የሚባል ሲሆን አንዷ መምህርት ግን መካከለኛ የሆነ እውቀት እንዳላት ከማትተገብረው ተግባራት ለማወቅ ተችሏል፡፡

የ9ኛ ክፍል የአማርኛ መምህራን በአብዛኛው የሚጠቀሙባቸው ብልሃቶች ሀሳብን በቃል ማቅረብና ውይይት መሆናቸው ታውቋል፡፡ ነገር ግን ጥሩ የሚባልና የመጻፍ ክሂልን ለማበልፀግ እገዛ የሚያደርግ ከተለያዩ መረጃ ምንጮች ያገኙትን እውቀት በፅሁፍ እንዲያቀርቡ የማድረግ ሁኔታ የታየው ከሁለቱ መምህራን በአንዱ ብቻ ሲሆን፣ በአንደኛዋ የታለመለትን ዓላማ የሚያሳካ እንዳልነበረ ለማወቅ ተችሏል፡፡

አንደኛው መምህር ለተወሰኑ ክፍለ ጊዜያት ከመማርያ መጽሐፍት ውጪ የተማሪዎችን ፍላጐት የሚጨምር ይዘትን አቅርቧል፡፡ በመማር ማስተማር ሂደት የመጻፍ ክሂልን በአግባቡ ለማቅረብ ሚናና ተግባሩን የተወጣ አንዱ ሲሆን አንዷ መምህርት በመካከለኛ ሁኔታ ሚናና ተግባሯን ተወጥታለች፡፡

ከሁለቱ መምህራን አንዱ የተማሪዎችን ተሳትፎ ለማሳደግ፣ ስሜታቸውን ለመቆጣጠር፣ በቋንቋው እንዲጠቀሙ ለማበረታታት፣ በተለያዩ ተግባራት እንዲሳተፉ ለማድረግ ከፍተኛ ጥረት ሲያደርግ አንዷ መምህርት ጥሩ ጅማሬ አሳይታ ያለመዝለቅ ሁኔታ እንዳለ የጥናቱ ውጤት አመላክቷል፡፡

የመጻፍ ክሂል አተገባበር ባለበት ክፍል ውስጥ ተማሪዎች ድርሰት ለመጻፍ የምንባቡን ሐሳብ በራሳቸው አባባል ለመጻፍ በምንባቡ መነሻነት ሀሳባቸውን አመንጭተው ለመጻፍ፣ ተማሪዎች እርስ በእርስ የሚከራከሩትን በፅሑፍ ለማቅረብ ያላቸው ፍላጐት ከፍተኛ፣ በመካከለኛ ሁኔታ በሚተገበርበት ክፍል ውስጥ መጠነኛና ትክክለኛ አተገባበር በሌለበት ሁኔታ ላይ እጅ ዝቅተኛ የሆነ የመማር ፍላጐት እንዳለ ለማወቅ ተችሏል፡፡ አንዱ መምህር ክሂሉን ጥሩ በሆነ ሁኔታ በሚያቀርብበት ክፍለጊዜያት ተማሪዎች ክሂሉን ለመማርና ለመጠቀም ያሳዩት ፍላጐት ከፍተኛ፣ መካከለኛ አቀራረብ በነበረበት ክፍለ ጊዜያት መጠነኛና ደካማ አቀራረብ በነበረበት ክፍለጊዜያትም ጭራሽ ፍላጐት የማጣት ሁኔታ እንዳለ ይታያል፡፡

በመጻፍ ክሂል አቀራረብ ወቅት ተማሪዎች ሚናና ተግባር መከወንና አለመከወን መነሻው የመምህሩ ጥሩ የሆነ የክሂሉ አቀራረብ መኖር አለመኖር መሆኑ ታውቋል፡፡ በመሆኑ ጥሩ የሆነ የክሂሉ አቀራረብ በነበረባቸው ጥቂት ክፍለጊዜያት የነበረው የተማሪ ሚናና ተግባር ከፍተኛ፣ መካከለኛ አቀራረብ በነበረባቸው በርካታ፣ ጥቂት ክፍለጊዜያት ሚናና ተግባራቸውን አለመወጣት እንዳለ ለማወቅ ተችሏል፡፡

በአጠቃላይ ሲታይ ከሁለቱም መምህራን የመጻፍ ክሂልን ትኩረት ሰጥተው የሚያስተምር አንዱ ሲሆን የተማሪዎችን ተነሳሽነት የሚወስነው እንደ መምህራን የአተገባበር ሁኔታእንደሆነ ማወቅ ተችሏል፡፡

ክሂሉን ለማስተማርና ለማሳደግ እንዲሁም በተማሪዎች ግንዛቤ ለመፍጠር እንደ ዋና ምክንያት የሚያስቀምጡት የክፍለጊዜ ማነስን ሲሆን ከዚህም በተጨማሪ ግን የጥናቱ ውጤት የሚከተሉትን ነጥቦች እንደ ችግር አይቷል፡፡

- በተማሪው መጽሐፍ የቀረቡትን መልመጃዎች ለመጨረስ ብቻ ትኩረት መስጠት
- በተማሪው መጽሐፍ ላይ ብቻ መወሰን
- ሚናና ተግባርን በአግባቡ አውቀው አለመተግበር
- የተለያዩ ዘዴዎችን ወይምብልሀቶችን ተጠቅሞ ክሂሉን ለማስገንዘብ ካለው የጊዜ ጥበት አንፃር የማይቻል አድርገው ማሰብ
- ስለክሂሉ አተገባበር በስልጠና ያገኙት እውቀት አለመኖር

## 5.2. የመፍትሄ ሐሳቦች

የመጻፍ ክሂልን ትኩረት ሰጥቶ ለማስተማር ችግር የሚፈጥሩና በመማር ማስተማር ሂደት አሉታዊ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ነጥቦች ምን እንደሆኑ በጥናቱ ውጤት ታውቋል፡፡

ከዚህ በማስከተል የመፍትሄ ሀሳቦችን በዝርዝር እንመለከታለን፡፡

- መምህራን በመጽሐፍ የቀረቡትን ይዘቶች ለመጨረስ ትኩረት ከመስጠት ይልቅ የተወሰኑ ይዘቶችን መርጦ ተማሪዎች ጥሩ በሆነ ሁኔታ በቋንቋው ተጠቅመው እንዲፅፉ ሀሳባቸውን እንዲገልፁ የሚያደርጉበትን የመማርናማስተማር ሂደት ቢፈጠር፣
- አንድ መምህር ቋንቋውን መናገር በመቻሉ ብቻ በግዴለሽነት እንዲያስተምር ከማድረግ ይልቅ ለቋንቋው ትኩረት በመስጠት በቋንቋው የሰለጠነ መምህር ቢያስተምር፣
- መምህራን በቋንቋ መማር ማስተማር ሂደት መድረኩን ተቆጣጥረው ብዙ ገለፃ ከማድረግ ይልቅ እድሉን ለተማሪዎች በመስጠት ተማሪዎች ክሂሉን እንዲለማመዱ ሁኔታ ቢመቻች፣

- መምህራን የተለያዩ ዘዴዎችን ወይም ብልሀቶችን አውቀው በአግባቡ መተግበራቸው የተማሪዎችን ፍላጐት ለመጨመር በተለያዩ ተግባራት ላይ ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ ለማድረግና አጠቃላይ ብቁ የቋንቋ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማስቻል አጋዥ መሆኑን ቢገነዘቡ፣
- መምህራኑ የቋንቋ መምህራን እንደመሆናቸው መጠን በጥናትና በምርምር የተደገፈ የመጻፍ ክሂል ማስተማርያ ዘዴዎች ጋር የሚተዋወቁባቸው አጫጭር ስልጠናዎች ቢያገኙ፣
- በተማሪው መጽሐፍ የሚቀርቡ ይዘቶች ለመምህራኑ እንደመነሻ ሆነው እንዲያገለግሉ በመሆኑ፣ መምህራን የራሳቸውን የፈጠራ ችሎ ተጠቅመው የተለያዩ አስተማሪ፣ አዝናኝ የተማሪውን ስሜት ሊያገዙ የሚችሉ የፈጠራ ስራዎችንወዘተ በክፍል ውስጥ በማምጣትና ተማሪዎችን ንቁ ተሳታፊ በማድረግ ክሂሉን ለማሳደግ ቢጥሩ፣
- መምህራን የተማሪዎችን የመጻፍ ብቃታቸው ለማሳደግ በክፍል ውስጥ ብቻ እንዳልሆነ ተረድተው ከክፍል ውጭ የሚሰሩ ተግባራትን በመስጠት ሰዎች እንዲጠይቁ፣ እንዲያነቡ፣ እንዲከራከሩወዘተ በማድረግ፣ ከሰዎች፣ ካነበቡትና ከተከራከሩት ያገኙትን እውቀት በሚገባ አቀነባብረው በፅሑፍ እንዲያቀርቡ ማድረግ፣
- መምህራን በሚሰለጥኑባቸው ኮሌጆችና ዩኒቨርሲቲዎች የመጻፍ ክሂልን ትኩረት ሰጥተው በሚገባ ቢማሩት፡፡

# ዋቢ ምንጮች


ማረው ዓለሙ (1987) "በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ፅሁፍ ክፍል ለሁለተኛ ዓመት ተማሪዎች በግልና በቡድን የሚፃፍ በሳል ድርሰቶች ንፅፅራዊ ግምገማ ጥናት አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ለአማርኛ ማስተማሪያ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ። ያልታተመ።

ባዬ ይማም ።(1987)። የአማርኛ ሰዋሰው። ት.መ.ማ.ማ.ድ. አዲስ አበባ።

ያለው እንዳወቀ።(2001)። የምርምር መሰረታዊ መሪዎችና አተገባር:: ን.ማ.ድ. አዲስ አበባ።

Badger, R. and White, G. (2000) ``*Product Process and Gener Approaches to Writing in EAP*`` (Electronic version). ELT Jornal,

Barr, R. and J. Barbara (1997) *Teaching Reading and Writing in Elementary Class Room.*New York: Longman.

Bawarshi, A. (2003) Gener & the invention of the write Recorsicening the place of invention in compostion logan Utahi Utah state. up

Beli, J. and H. Burnaby (1984) *A Hand Book for ESL Literacy.* Toronto: OISE.

Bernstein, B. (1990) The structuring of pedagogic discourse, vol iv: class. Condes and control. London: Routledge Kegan Pav.

Berlin, J. (1984) writing instruction in nineteen-century America college. USA: Conference n College Composing & Communication.

Brown, H.D. (2000) *Principles of language learning and Teaching white Plawns,* NY: Addison Weslay Longman.

Brown, H.D. (2001) *Teaching by Principles: An Interative Approach to Language Pedagogy.* (2nd ed) New York: Addison weslay Longman.

Bums, A. (2001) Gener based approach to writing and Biginning adult ESL Learners. In C. Candin & N. Mercer English Language Teaching in Social Context Areader London: Rouledge.

Byram, M. (2004) Gener and Gener based Teaching the Encyclopidia of langage Teaching and Learning Byrne, Donn (1988) *Teaching Writing Skills.* London: Longman Group UK Ltd.

______(1991) *Teaching Writing Skills.*London: Longman Group Uk Ltd.

Christine, F. (1987) Gener as achoice. Reid (ed). ``the place of Gener in learning current dibates`` Deakin: University press.

Cope, B and M Kalantzis (1993) Background to Gener teaching in B. Cope M. Kantzis (eds). The Power of Literacy.Agener Approach to Teaching writing London Flamer press.

Davies (1988) `` Designing awriting Syllabus in English for academic purpose: process and product`` in Robinson (p.c) ed Academic writing: process and product londdon: modern English production- British council ``ELT Document.

Derewianka, B. (2003) ``Trends and issues in Gener based Approch`` RELC Jornal.

Devit, A. (2003) ``Generalizing about Gener: New conception of an old concept: college Compositin & Communication. ELT Journal.

Emelie Ahlsen and Nathalie Lunth (2007) *Teaching Writing in Theory and Practice.*Stockholm: Institute of Education.

Feez, S. (2002) ``Hertage and innovation in second language education. Gener in classroom: multiple perspective. ED Ann Johns Newjersy: Lawrence Eribaum Association. 43-69 printi.

Guth, H.P. (1989) The Writer's Agenda. California: Wards Worth Publishing Campany.

Hamond, J. and Drewiaka, B. (2001) Gener in R. Carter & D. Nunan (eds). The Cambridge guied to teaching English to Speakers other language Cambridge: Cambridge University press.

Harmer, J. (1994) Teaching and Learning Grammar. London: Longman group Ltd.

Hayland.K. (2002).Gener in primary Classrooms. The New Southern Watis (NSW) K.O Syllabus lne N. Candlin and D.R Hall Teaching and Resarching (pp.96-103) Harlw ESSEX.

_________ (2003a) ``Gener based pedagogy: Asocial response to process`` Jornal of seconed language writing

_________ (2003b) Second language writing New York: Cambridge University pre.

_________ (2004) Gener and second language writtin Ann. Arober M1: the University of Michigan press

________ (2007) Gener Pedagogy: literacy and L2 writing instruction. ``Gener pedagogy: Language Literacy and L2 writing instruction. ``Jornal seconed language writing.

Heaton, J.B. (1991) *Writing English Language Tests.* London: Longman UK Ltd.

Hedge, T. (1988) *Writing.* Oxford: Oxford University Press.

____________(2005) *Writing* Oxford: Oxford University Press.

Hyon, S. (1996) ``Gener in Three traditions Implicatin for ESL`` TESOL Quarterly.

Kay & Dudey-Evans. T. (1998) Gener what teachers think (Electronic Version) ELT Journal.

Kim. MS. (2007) Gener Based Approach to teaching writing Hawai Pacific Universty.

Kim and Kim.J. (2005) ``Teaching Korean University writing class Balancing the Process and the Gener Approach`` (Electronic Version) Asian EFL Jornal.

Konupetoh.S. (2006) ``Using AGener Based Approach to Teach writing to that Students`` Acase Study Prospect.

Kroll, B. (1990) *Second Language Writing: Research Insights for Class Room.*Cambridge: Cambridge University Press.

Kumar, R. (2005) *Research Methdology (2nd ed).* Calfornia: Sage publications.

Marks, J. (1994) *Inside Teaching*. London: Longman.

Neman, B. (1995) *Teaching Students to write.*Oxford: Oxford University Press.

Norrish, J. (1990) *Language Learning and their Errors.*London and Basingstok: Macmillan Publisher Ltd.

Nunan, D. (1989) *Designing Tasks for the Communicative Class Room.*Cambridge: Cambridge University Press.

Pallridge (2001) Gener and the language learning classroom. Ann Arbor. Unviversity of Michigan press.

_______ (2002) Gener text type and English for Academic Purpose (ECP).in A.M Johnes (ed) Gener in the class room: multiple perspective. Mahwah N.J.L Eribabum.

_______ (2007) Approch to Gener in ELT. In J. Cummins & C. Davison (eds).Intemational hand book of English language teaching Springer US.

Richards, J.C (1990) *The Language Teaching Matrix.*Cambridge: Cambridge University Press.

Rivers, W. (1981).*Teaching Foreign Language Skills.*Chicago: the University of Chicago Press.

Ur, P. (1996) *A Course in Language Teaching.*Cambridge: Cambridge University Press.

White, R. and Ardent, U. (1991) *Process Writing.* London: Longman.

Yan, G. (2005) Aprocess Gener model for Teaching writing English Teaching Forum.

# አባሪዎች

## አባሪ "ሀ"

### የመጻፍ ክሂል አተገባበርና ተነሳሽነት መመልከቻ ቅፅ

ት/ቤት ቀን ___ ወር _ ዓ/ም ____________

ክፍል _________________________ ት/ቤቱ የተጀመረበት ቀን ___________________

ክፍለ ጊዜ _______________ ት/ቤቱ የተጠናቀቀበት ቀን _________________________

መምህር __________ የተማሪው ብዛት _______________________________________

የትምህርቱ ዋና ርዕስ _______________________________________________________

የትምህርቱ ንዑስ ርዕስ ______________________________________________________

**መመሪያ፡-** ቀጥሎ ከቀረቡት መስፈርቶች መካከል አንዱን በመምረጥ በተሰጠው ቅፅ መልስ መስጫ ላይ (✓) ምልክት በማድረግ ማሳየት፡፡

ሀ/እጅግ ከፍተኛ ለ/ ከፍተኛ ሐ/ መካከለኛ መ/ አነስተኛ ሠ/በጣም አነስተኛ

| ተ.ቁ. | | ሀ | ለ | ሐ | መ | ሠ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የክፍለ ጊዜ ይዘት | | | | | |
| 1.1 | የመጻፍ ክሂልን ለማስተማር ያለው እገዛ | | | | | |
| 1.2 | አዳምጦ መጻፍን የማጐልበት ፋይዳ | | | | | |
| 1.3 | ፅህፈትን አደራጅተው ለማቅረብ ያለው ፋይዳ | | | | | |
| 1.4 | ንግግርን ለማጐልበት ያለው ፋይዳ | | | | | |
| 1.5 | ከተማሪው ህይወት ጋር ያለው ግንኙነት | | | | | |
| 2 | መምህሩ/ሯ | | | | | |
| 2.1 | ተማሪዎች ቋንቋውን ለትክክለኛ ዓላማ እንዲጠቀሙ የሚያደርጉት ጥረት | | | | | |
| 2.2 | ተግባቦታዊ ስልተ ትምህርት የመጠቀም ሁኔታ | | | | | |
| 2.3 | ተማሪዎች በራሳቸው ርዕስ መርጠው ድርሰት እንዲፅፉ የማድረግ ሁኔታ፡፡ | | | | | |
| 2.3.1 | የምንባቡን ሀሳብ በራሳቸው አባባል እንዲፅፉ የማድረግ ሁኔታ | | | | | |
| 2.3.2 | በምንባቡ መነሻነት ሀሳቦችን አመንጭተው እንዲፅፉ የማድረግ ሁኔታ | | | | | |
| 2.4 | ተማሪዎች ሀሳባቸውን በትክክል በፅሁፍ እንዲገልፁ በቂ ጊዜ የመስጠት ሁኔታ | | | | | |
| 2.5 | ተማሪዎች በሚሰጣቸው ተግባር አማካኝነት | | | | | |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 2.5.1 | ተማሪዎቹ እርስ በርስ እንዲከራከሩ የማድረግ ሁኔታ | | | | | |
| 2.6 | እርስ በርስ እንዲተራረሙ የማድረግ ሁኔታ | | | | | |
| 2.7 | ተማሪዎች በቋንቋው እንዲጠቀሙ የማበረታታት ሁኔታ | | | | | |
| 2.8 | ተማሪዎች በሚከራከሩበትና በሚወያዩበት ጊዜ፣ | | | | | |
| 2.8.1 | ክትትል የማድረግ ሁኔታ | | | | | |
| 2.8.2 | እርማት የመስጠት ሁኔታ | | | | | |
| 2.9 | ከተማሪው መጽሐፍ ውጪ የተማሪዎችን ፍላጐት የሚጨምር ይዘት የማቅረብ ሁኔታ | | | | | |
| 2.10 | ተማሪዎችን የማሳተፍ ሁኔታ | | | | | |
| 2.11 | ለመጻፍ ክሂል ትኩረት ሰጥቶ የማስተማር ሁኔታ | | | | | |
| 2.12 | ተማሪዎች በተግባራት እንዲሳተፉ የማድረግ ሁኔታ | | | | | |
| 2.13 | ከተማሪ ልምድ ጋር የተገናዘቡ ጥያቄዎችን የማቅረብ ሁኔታ | | | | | |
| 3 | ተማሪዎቹ | | | | | |
| 3.1 | አዳምጠው ለመጻፍ የሚያሳዩት ፍላጐት | | | | | |
| 3.2 | ለመናገር የሚያሳዩት ፍላጐት | | | | | |
| 3.3 | ከምንባቡ ያገኙትን ሀሳብ በፅሑፍ ለማቅረብ የሚያሳዩት ፍላጐት | | | | | |
| 3.4 | ከተለያዩ መረጃ ምንጮች ያገኙትን እውቀት በፅሑፍ ለማቅረብ ያላቸው ፍላጐት፡፡ | | | | | |
| 3.5 | በክፍል ውስጥ የሚያሳዩት ተሳትፎ | | | | | |
| 3.6 | ሀሳባቸውን አደራጅተው በፅሑፍ የመግለፅ ሁኔታ | | | | | |
| 3.7 | ለመከራከር /ለመወያየት የተወያዩትን በፅሑፍ ለማቅረብ የሚያሳዩት ፍላጐት | | | | | |
| 3.8 | የተለያዩ ጭውውቶችን በሚና ጨዋታ አማካኝነት የመተግበር ሁኔታ | | | | | |
| 3.9 | ተማሪዎች ምንባብ ያነባሉ | | | | | |
| 3.10 | የምንባቡን ሀሳብ በራሳቸው አባባል ይፅፋሉ፡፡ | | | | | |
| 3.11 | በምንባቡ መነሻነት ሀሳቦችን አመንጭተው ይጽፋሉ፡፡ | | | | | |
| 3.12 | በተለያዩ ተግባራት ይሳተፋሉ | | | | | |
| 3.13 | በሚሰጣቸው ርዕሰ ጉዳይ ላይ ይወያያሉ፡፡ | | | | | |

## አባሪ "ለ"

1. የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል ብቃት ለማዳበር ትኩረት ሰጥተው ማስተማር የሚለውን አቀራረብ ያውቃሉ?
2. የመጻፍ ክሂልን በተፈጥሮአዊ መንገድ ማግኘት ይቻላል ወይስ በት/ቤት ብቻ?
3. የመጻፍ ክሂል መዳበር በተማሪዎች የቋንቋ ችሎታ ላይ ለውጥ ያመጣል ብለው ያስባሉ? ከሆነ እንዴት? ካልሆነ ለምን?
4. የመጻፍ ክሂል የተቀሩትን ሦስት ክሂሎች ማለትም በማንበብ ጊዜ፣ በመናገርና በማዳመጥ ጊዜ እንዴት እንደሚያግዝ በቋንቋ ትምህርት ክፍለ ጊዜ ተማሪዎችን ያስገነዝባሉ (ያስረዳሉ)? ካስረዱ እንዴት? ካላስረዱ ለምን?
5. በሰለጠኑበት የትምህርት ተቋም የመጻፍ ክሂል አቀራረብ የተማሩት በተናጠል ነው? ወይስ በቅንጅት?
6. ተማሪዎች ከትምህርት ጋር በተያያዘ መልኩ ሰዎችን ጠይቀው ወይም የተለያዩ ጽሑፎችን አንብበው ማስታወሻ በመያዝ ዘገባዎችን እንዲያቀርቡና እንዲወያዩ የማድረግ ልምድ አለዎት? ካልሆነስ? ችግሩ ምንድነው?
7. በአንድ ክፍለጊዜ ሁሉንም የቋንቋ ክሂሎት ወይም በክፍል ተያይዘው እንዲመጡ ማድረግ ይቻላል? ከተቻለ እንዴት? ካልሆነስ ለምን?
8. የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል ለማዳበር አስበው እንቅፋት የሆነብዎት ወይም ያጋጠመዎት ችግር አለ?
9. ተማሪዎቹ በመደበኛ ክፍለ ጊዜያት የመጻፍ ክሂል ትምህርት ከሚማሩት ባሻገር ተማሪዎችን በልምምድ ብቁ የቋንቋ ተጠቃሚ የሚያደርግ የመማር ማስተማር ሂደትን ይከተላሉ?
10. ተማሪዎች አንድን ንግግር አዳምጠው የተረዱትን ሀሳብ እንዲፅፉ ያደርጋሉ?
11. ተማሪዎች የተለያዩ ርዕሶችን መርጠው እንዲወያዩ እና እንዲከራከሩ፣ የተወያዩትን በፅሁፍ እንዲያቀርቡ ያደርጋሉ?
12. ለተማሪዎች ከመማርያ መፅሐፍ ውጪ ሌሎች ምንባቦች ያነቡላቸዋል፡፡
13. የሚያነቡላቸውን ምንባቦች መነሻ በማድረግ የራሳቸውን ፈጠራ በማከል አስፋፍተው እንዲፅፉ ያደርጋሉ?
14. ተማሪዎቹ የሚጽፉላቸውን ጽሁፎች ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያነቡላቸው ያደርጋሉ?
15. በቋንቋ ትምህርት ክፍለ ጊዜ የመጻፍ ክሂልን ትኩረት ሰጥተው የሚያስተምሩ ከሆነ ችግሩ ምንድነው?

# አባሪ "ሐ"

## በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ የቋንቋዎች ጥናት ኮሙኒኬሽንና ጋዜጠኝነት ኮሌጅ የአማርኛ ቋንቋ ሥነ-ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል የድህረ-ምረቃ መርሃ ግብር በ2015 ዓ/ም የመጀመሪያ ወሰን ትምህርት በተመረጠው ቀርሳ ማሊማ ወረዳ በሌማን ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ9ኛ ክፍል ተማሪዎች የሚሞላ የጽሑፍ መጠይቅ፡፡

**ውድ ተማሪዬ**

በመጀመሪያ የተከበረ ጊዜህን/ሽን መስዋዕት በማድረግ ይህንን መጠይቅ ለመሙላት ፈቃደኛ በመሆንህ/ሽ ከልብ አመሰግናለሁ፡፡

የዚህ መጠይቅ አላማ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ውስጥ የመጻፍ ክሂል ትኩረት ተሰጥቶት ይቀርብላቸው እንደሆነ መፈተሽና የተማሪዎችን ተነሳሽነት ተመልክቶ የመፍትሄ ሀሳብ ለመጠቆም ለተዘጋጁ ጥናት መረጃ መሰብሰብ ነው፡፡ በመሆኑም ጥናቱ የተሳካ እንዲሆን በመጠይቁ የቀረቡትን ጥያቄዎች በርጋታ በማንበብ መልስህን/ሽን በማያሻማ መልኩ በተሰጠው ቦታ ላይ እንድታሰፍር/ሪ በትህትና እጠይቃለሁ፡፡

***<u>ማሳሰቢያ</u>***

ሀ. በመጠይቁ ላይ ስም መጻፍ አያስፈልግም

ለ. ጥናቱ ውጤታማ ይሆን ዘንድ የአንተ/ቺ ድርሻ ከፍተኛ በመሆኑ ትክክለኛ መረጃ መስጠት ተገቢ ነው፡፡

ሐ. የመጠይቁን ጥያቄዎች ከሌሎች ተማሪዎች ጋር በመመካከር ብትሞላ በጥናቱ ውጤት ላይ ተጽዕኖ ስለሚያድር ብቻህን/ሽን ሙላ/ዪ፡፡

መ. ከተነሱት ጥያቄዎች ተጨማሪ ሃሳብ ካለ በመጠይቁ መጨረሻ ላይ ማስፈር ይቻላል፡፡

***ሚያዚያ 2015***

**ክፍል አንድ፡-** አጠቃላይ መረጃ

1. ፆታ ____________________
2. እድሜ __________________
3. የክፍል ደረጃ _____________

**ክፍል ሁለት፡-** ከዚህ በታች የመጻፍ ክሂል አተገባበርና ተነሳሽነት የሚያመለክቱ ሀተታዎች ቀርበዋል፡፡ የትግበራ አይነቶች ምን ያህል ተግባራዊ እንደሆኑ ከተሰጡት አማራጮች መካከል ትክክል መልስ ይሏል የምትለውን/ይውን ሆሄ በመምረጥ የ() ምልክት አስቀምጥ/ጪ

ሀ/ ሁልጊዜ ለ/ ብዙውን ጊዜ ሐ/ በመጠኑ መ/ አንዳንድ ጊዜ ሠ/ በጭራሽ

| ተ.ቁ. | በአማርኛ ትምህርት ክፍለ ጊዜ | ሀ | ለ | ሐ | መ | ሠ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የጥንድም ሆነ የቡድን ተግባራትን እንዲከናወን ያደርጋሉ? | | | | | |
| 2 | በጥንድም ሆነ በቡድን በመደራጀት በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ሰዎችን እንጠይቃለን? | | | | | |
| 2.1 | የተለያዩ ምንባቦችን እናነባለን? | | | | | |
| 2.2. | ከክፍል ጓደኞቻችን ጋር እንወያያለን? | | | | | |
| 2.2.1 | የውይይቱን ውጤት በጽሁፍ እናቀርባለን? | | | | | |
| 2.2.2. | የውይይቱን ውጤት በቃል እናቀርባለን? | | | | | |
| 3 | በክፍልም ሆነ ከክፍል ውጪ እንዲሰሩ በሚሰጡት ተግባራት፡- | | | | | |
| 3.1. | እናነባለን | | | | | |
| 3.2 | ከጓደኞቻችን ጋር እንነጋገራለን | | | | | |
| 3.3 | የተለያዩ ሰዎችን እንጠይቃለን | | | | | |
| 3.4 | ከተለያዩ ሚዲያዎች መረጃዎችን አዳምጠን እንፅፋለን | | | | | |
| 3.5 | ከተለያዩ ምንጮች ያገኘናቸውን መረጃዎች | | | | | |
| 3.5.1 | ለክፍል ጓደኞቻችን በቃልና በፅሑፍ እናቀርባለን | | | | | |
| 4. | ተግባራትን ስናከናውን በመምህራችን ተገቢ ያልሆነ ድጋፍና ክትትል ይደረግልናል፡፡ | | | | | |
| 5. | መምህራችን የሚያቀርቡልንን ይዘት መሰረት በማድረግ | | | | | |
| 5.1. | የተለያዩ ፅሑፎችን እናነባለን ከምንባቡ ያገኘነውን ፍሬ ሐሳብ እንፅፋለን | | | | | |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 5.2. | እናዳምጣለን | | | | | |
| 5.3. | እንወያያለን | | | | | |
| 5.4. | እንፅፋለን | | | | | |
| 6 | በየግላችን የተለያዩ ጽሑፎችን እንድናነብ ይደረግልናል | | | | | |
| 6.1. | እንድናነብ ያደርጋሉ | | | | | |
| 6.2. | እንድንፅፍ ያደርጋሉ | | | | | |
| 7. | የአንድን ተውኔት፣ አጭር ልቦለድ ወዘተ ገፀባህርያት ወክለን በክፍል ውስጥ እናቀርባለን | | | | | |
| 8. | ድራማዎችን፣ ክርክሮችን ወዘተ ተለማምደን ክፍል ውስጥ የምናቀርብበት ሁኔታ ይመቻችልናል | | | | | |
| 9. | አዳዲስ ተግባራትን እንድናመነጭ ከመምህራችን የሞራል ድጋፍ ይደረግልናል | | | | | |

ከዚህ በታች የመጻፍ ክሂል አተገባበርና ተነሳሽነት የሚያመላክቱ ብዙ ሃተታዎች ቀርበዋል፡፡ በትግበራ አይነቶቹ ምን ያህል ተግባራዊ እንደሆኑ ከተሰጡት አማራጮች መካከል ትክክለኛ መልስ ይዟል የምትለውን/ይውን ሆሄ በመምረጥ () ምልክት አስቀምጥ/ጪ፡፡

ሀ/እጅግ ከፍተኛ ለ/ ከፍተኛ ሐ/ መካከለኛ መ/ አነስተኛ ሠ/በጣም አነስተኛ

| ተ.ቁ. | በአማርኛ ቋንቋ ክፍለ ጊዜ | ሀ | ለ | ሐ | መ | ሠ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 10 | አዳዲስ ተግባራትን ለማመንጨት ያለኝ ፍላጐት | | | | | |
| 11 | ተግባራትን መነሻ በማድረግ በክፍልም ሆነ ከክፍል ውጭ የሚሰጡትን ተግባራት ለመስራት ያለኝ ፍላጐት | | | | | |

**ክፍል ሦስት፡-** ክፍት ጥያቄዎች

***መመሪያ፡-*** ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች ተገቢ ነው የምትለውን/ይውን ምላሽ በተሰጠው ክፍት ቦታ ላይ አስፍር/ሪ ምናልባት የተሰጠው ክፍት ቦታ በቂ ካልሆነ በጀርባ ባለው ክፍት ቦታ ላይ መጠቀም ይቻላል፡፡

12. በመምህራችሁ ከመማርያ መጽሐፋችሁ ውጪ የመጻፍ ክሂልን ለማስተማር የሚጠቀሙበት የማስተማርያ መሳርያ አለ? ካለ ምን ምን? በምን አይነት ሁኔታ? __________

______________________________________________

______________________________________________

13. የእለት ተእለት (የገሀዱ አለም) የቋንቋ አጠቃቀም ክንዋኔዎች አማካኝነት የመጻፍ ክሂልን በመጠቀም እንድትለማመዱ ያደርጋል? እንዴት?________________________________________

________________________________________________________________

________________________________________________________________

________________________________________

14. መምህራችሁ የተለያዩ ታሪኮችን በማምጣት ድምጻቸውን ከፍ በማድረግ ያነባሉ? ወይም እናንተን ያስነብባሉ? ምላሻችሁ አወንታዊ ከሆነ ታሪኩን በመመርኮዝ ምን ምን አይነት ተግባራትን እንድታከናውኑ ያደርጋል?________________________________________

________________________________________________________________

________________________________________________________________

________________________________________________________________

___________________________________

## አባሪ "መ"

### ከሞባይል ቅጅ ወደ ጽሁፍ የተመለሰ የመምህራን የቃለመጠይቅ ምላሽ

ጥያቄ 1፡- የመጻፍ ክሂልን ትኩረት ሰጥተው ማስተማር ለተቀሩት ሦስት የቋንቋ ክሂሎች ጥቅም እንዳለው ያውቃሉ?

መ1. አውቀዋለው ምክንያቱም በማንበብ ጊዜ፣ በማዳመጥ ጊዜና በንግግር ጊዜ ሐሳብ እንዳይቆራረጥና እንዳያረጅ ማስታወሻ የምንይዘው በፅሁፍ ስለሆነ

መ2. አውቃለሁ ምክንያቱም አንዱን ክሂል ሳስተምር ሌሎችም ባንድ ላይ እንዲጠቀሙ ስለማደርግ፡፡

ጥያቄ 2. ክሂሉን ለማስተማር ሲያቅዱ የሚያቀርቧቸው በተናጠል ነው? ወይስ በቅንጅት?

መ1 በቅንጅት

መ2. በቅንጅትም በተናጠልም

ጥያቄ 3፡- በቋንቋ ማስተማር ክፍለ ጊዜ የመጻፍ ክሂልን ትኩረት ሰጥቶ ማስተማር በተማሪዎች ችሎታ ላይ ለውጥ ያመጣል ብለው ያስባሉ? ከሆነስ እንዴት?

መ1፡ አዎን ምክንያቱም የመጻፍ ክሂል ለማንኛውም ችሎታ መዳበር መሠረት በመሆኑ

መ2፡- አዎ ያመጣል ምክንያቱም አዳምጠው ይጽፋሉ፣ ጽፈውም ያነባሉ ወይም ይናገራሉ፤ በዚሁ ሁኔታ ልምምድ ካደረጉ ደግሞ በቋንቋ ችሎታቸው ላይ ለውጥ ያመጣል፡፡

ጥያቄ 4፡- በአንድ ክፍለ ጊዜ የቋንቋ ክሂሎች ወይም በክፍል ተያይዘው እንዲመጡ ማድረግ ይቻላል? ከተቻለ እንዴት? ካልተቻለ ለምን?

መ1፡- አይቻልም ምክንያቱም የክፍለ ጊዜ እጥረት ስላለ አይሞከርም፡፡

መ2፡- ይቻላል እንድትማር ሀሳቡን በንግግር ሲገልፅ ሌሎች እንዲያዳምጡ አደርጋለሁ፤ ሌሎች ያዳምጣሉ፣ እንዲወያዩ አደርጋለሁ፣ እንዲከራከሩ አደርጋለሁ በዚሁ ሁኔታ አቀርባለሁ፡፡

ጥያቄ 5፡- የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታ ለማሳደግ አስበው ያጋጠመዎት ችግር አለ? ካለ ችግሩ ምንድነው?

መ1፡- አዎ ያጋጠመኝ ችግር አለ፡፡ እሱም የተወሰኑት ተማሪዎች ፈጣን መሆንና ሌሎች ደግሞ ፊደል ራሱ ያለዩ መሆናቸው ነው፡፡

መ2፡- ችግሩ አለ፡፡ ችግሩ የመርሀ ትምህርቱና የመምህሩ መምሪያ ተሟልቶ አለመቅረብ በተማሪው መጻፍ ላይ ብቻ ተገድቦ በተፈለገው መጠን እንዳናስተምር አድርጓል፡፡ ሌላው ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የተሰጠው ክፍለ ጊዜ አናሳ መሆኑ ነው፡፡

ጥያቄ 6፡- ተማሪዎች ከትምህርቱ ጋር በተያያዘ መልኩ ሰዎችን ጠይቀው ወይም ፅሁፎችን አንብበው ማስታወሻ በማዘ ዘገባቸውን እንዲያቀርቡና እንዲወያዩ የማድረግ ልምድ አለዎት?

መ1፡- ጽሁፎቹን አንብበው ብቻ ሳይሆን ሌሎ ክስተቶችን ተመልክተው፣ አዳምጠው፣ ጠይቀው ማስታወሻ ጽፈው ዘገባዎችን እንዲያቀርቡና እንዲወያዩ አደርጋለሁ፡፡

መ2፡- አደርጋለሁ፣ ነገር ግን አልፎ አልፎ ነው፤ ምክንያቱም የክፍለ ጊዜ አናሳ መሆን ተማሪዎችን ለማለማመድ አዳጋች በመሆኑ ይማራሉ ለማለት ያህል እንጂ እነዚህንና ሌሎችን ተግባራት አቅርቦ ለማሰራት ጊዜው የሚፈቅድ ቅጽ አይደለም፡፡

ጥያቄ7፡- በሰለጠኑበት የትምህርት ተቋም የመጻፍ ክሂሎትን በተናጠል ነው ወይስ በቅንጅት?

መ1፡- የተማርኩት በተናጠል ነው፤ ነገር ግን በንግግር ክሂል ላይ ያደላ ነበር፡፡

መ2፡- የተማርኩት በተናጠል ነው፡፡

ጥያቄ 8፡- የተማሪዎች መጽሐፍ፣ የመምህሩ መምርያና መርሀ ትምህርቱ የቋንቋ ክሂሎችን እርስ በርስ ተያይዘው እንዲቀርቡ እገዛ በማድረግ የመማር ማስተማር ሂደቱን ለመምራት ምን ያህል አጋዥ ነው?

መ1፡- የመምህር መምርያ አለ፤ መርሀ ትምህርት ግን በትምህርት ቤታችን አለ ጥሩ እገዛ የደርጋል፡፡

መ2፡- መርሀ ትምህርት የለም፤ የመምህሩ መምርያና የተማሪ መጽሐፍ ግን ጥሩ እገዛ ያደርጋል፡፡

## አባሪ “ሠ”

በየክፍለ ጊዜው የነበሩ ይዘቶች ዋና ትኩረታቸው ምን ላይ እንደሆነ ለማወቅ ከምልከታ የተገኘ መረጃ፡፡

መ1፡- ጽህፈት መሸጋገሪያ ቃላትና አያያዥ ቃላትና ሀረጎች እንዲፅፉ ማድረግ፡፡

ምልከታ 2፡- ሰዋሰው መነሻና መድረሻ ጥያቄዎችን በመጠቀም ቃላትን መስርተው ዓ/ነገር እንዲሰሩ ማድረግ፤ የቃላትን እማሬያዊና እና ፍካሬያዊ ፍቺ መጻፍ፡፡

ምልከታ 3፡- ሰዋሰው የሐረግ አይነቶችን እንዲፅፉ ማድረግ

ምልከታ 4፡- ለመልመጃዎች እርማት መስጠት

ምልከታ 5፡- ቃላትን እንደ ባለቤት፣ ተሳቢና ማሰርያ አንቀፅ ተጠቅመው ዓ/ነገር መመስረት

መ2 ምልከታ፡- የቃላት አገባባዊ ፍቺ በአረፍተ ነገር ውስጥ አስገብተው እንዲፅፉ ማድረግ

ምልከታ 2፡- አንቀፅ መፃፍ

ምልከታ 3፡- ጅምር ስንኞችን ማሟላት

ምልከታ 4፡- ግጥም በራሳቸው ርዕስ መርጠው ግጥም እንዲፅፉ ማድረግ

ምልከታ 5፡- ለመልመጃዎች እርማት መስጠት፡፡

## አባሪ "ረ"

## የተማሪዎችን ሚናና ተግባር ለማወቅ ከተማሪዎች የተገኘ የጽሁፍ ምላሽ

| ተ.ቁ | በአማርኛ ትምህርት ክፍለ ጊዜ | ሀ | ለ | ሐ | መ | ሠ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 2 | በጥንድም ሆነ በቡድን በመደራጀት በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ሰዎችን እንጠይቃለን | - | - | 20 (15.38) | 90 (69.23) | 20 (15.38) |
| 2.1 | የተለያዩ ምንባቦችን እናነባለን? | 23 (17.69) | 50 (38.46) | 25 (19.23) | 25 (19.23) | 7 (5.38%) |
| 2.2. | ከክፍል ጓደኞቻችን ጋር እንወያያለን | 20 (15.38) | 33 (25.38) | 36 | 41 (31.53) | - |
| 2.2.1 | የውይይቱን ውጤት በጽሁፍ እናቀርባለን | 22 (16.92) | 18 (13.84) | 20 (15.38) | 56 (19.23) | 14 (43.07) |
| 2.2.2 | የውይይቱን ውጤት በቃል እናቀርባለን | 27 (20.76) | 23 (17.69) | 30 | | 13 (10%) |
| 3 | በክፍልም ሆነ ከክፍል ውጪ እንዲሰሩ በሚሰጡት ተግባራት፡- | | | | | |
| 3.1 | እናነባለን | 45 (34.61) | 23 (17.69) | 25 (19.23) | 25 (19.23) | 12 (9.23%) |
| 3.2 | ከጓደኞቻችን ጋር እንነጋገራለን | 25 (19.23) | 21 (16.15) | 33 (25.38) | 51 (39.23) | |
| 3.3 | የተለያዩ ሰዎችን እንጠይቃለን | - | | 23 (17.69) | 73 (59.23) | 30 (23.07) |
| 3.4 | ከተለያዩ ሚዲያዎች መረጃዎችን አዳምጠን እንፅፋለን | | | 18 (13.21) | 26 (20%) | 86 (66.15) |
| 3.5 | ከተለያዩ ምንጮች ያገኘናቸውን መረጃዎች | | | | | |
| 3.5.1 | ለክፍል ጓደኞቻችን በቃልና በፅሑፍ እናቀርባለን | 25 (19.23) | 20 (15.38) | 33 (25.38) | 42 (32.3%) | 10 |
| 5. | መምህራችን የሚያቀርቡልንን ይዘት መሰረት በማድረግ | | | | | |
| 5.1. | የተለያዩ ፅሑፎችን እናነባለን ከምንባቡ ያገኘነውን ፍሬ ሐሳብ እንፅፋለን | 43 (33.07) | 20 (15.23) | 27 (20.76) | 31 (23.84) | 9 (6.92%) |
| 5.2. | እናዳምጣለን | 17 | 23 (17.69) | 60 (46.15) | 21 (16.15) | 9 (6.92%) |
| 5.3. | እንወያያለን | 40 (30.76) | 13 (10%) | 34 (26.15) | 43 (33.07) | |
| 5.4. | እንፅፋለን | 12 (9.23%) | 23 (17.69) | 11 (8.46%) | 68 (52.3%) | 12 (10.76) |

# አባሪ "ሰ"

## በክፍል ምልከታ የተገኘ አጠቃላይ የሰንጠረዥ መረጃ

| ተ/ቁ | ሀ/ለ | | ሐ | | መ | | ሠ | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | በቁ. | በ% | በቁ. | በ% | በቁ. | በ% | በቁ. | በ% |
| 1 | **10** | **100%** | | | | | | |
| 2.1 | | | | | | | | |
| 2.2 | 4 | 40% | 3 | 30% | 2 | 20% | 1 | 10% |
| 2.3 | 2 | 20% | 3 | 30% | 4 | 40% | 1 | 10% |
| 2.3.1 | | | | | | | | |
| 2.3.2 | 5 | 50% | 2 | 20% | 2 | 20% | 1 | 10% |
| 2.3.2 | 3 | 30% | 2 | 20% | 3 | 30% | | |
| 2.3.3 | 3 | 30% | 1 | 10% | 5 | 50% | 1 | 10% |
| 2.4 | 4 | 40% | 3 | 30% | 2 | 20% | 1 | 10% |
| 2.5 | | | | | | | | |
| 2.5.1 | 2 | 20% | 3 | 30% | 3 | 30% | 2 | 20% |
| 2.5.2 | 4 | 40% | 2 | 20% | 4 | 40% | | |
| 2.5.3 | 2 | 20% | 3 | 30% | 4 | 40% | 1 | 10% |
| 2.6 | 4 | 40% | 3 | 30% | 1 | 10% | 2 | 20% |
| 2.7 | 4 | 40% | 3 | 30% | 2 | 20% | 1 | 10% |
| 2.8 | | | | | | | | |
| 2.8.1 | 3 | 30% | 2 | 20% | 4 | 40% | 1 | 10% |
| .8.2 | 4 | 40% | 4 | 40% | 2 | 20% | 1 | 10% |
| 3.9 | 2 | 20% | 3 | 30% | 4 | 40% | 1 | 10% |
| 2.10 | 4 | 40% | 2 | 20% | 3 | 30% | 1 | 10% |
| 2.11 | 3 | 30% | 4 | 40% | 2 | 20% | 1 | 10% |
| 2.12 | 4 | 40% | 3 | 30% | 1 | 10% | 2 | 20% |
| 2.13 | 4 | 40% | 3 | 30% | 1 | 10% | 2 | 20% |

| | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 3. | | | | | | | | |
| 3.1 | 3 | 30% | 4 | 40% | 2 | 20% | 1 | 10% |
| 3.2 | 3 | 30% | 2 | 20% | 3 | 30% | 1 | 10% |
| 3.3 | 4 | 40% | 2 | 20% | 3 | 30% | 1 | 10% |
| 3.4 | 3 | 30% | 1 | 10% | 4 | 20% | 2 | 20% |
| 3.5 | 4 | 40% | 3 | 30% | 2 | 20% | 1 | 10% |
| 3.6 | 4 | 40% | 3 | 30% | 2 | 40% | 1 | 10% |
| 3.7 | 3 | 30% | 2 | 20% | 4 | 40% | 1 | 10% |
| 3.8 | 3 | 30% | | | | | 7 | 70% |
| 3.9 | 4 | 40% | 2 | 20% | 3 | 30% | 1 | 10% |
| 3.9.1 | 4 | 40% | 2 | 20% | 3 | 30% | 1 | 10% |
| 3.9.2 | 3 | 30% | 1 | 10% | 5 | 50% | 1 | 10% |
| 3.10 | 5 | 50% | 2 | 20% | 2 | 20% | 1 | 10% |
| 3.11 | 4 | 40% | 2 | 20% | 3 | 30% | 1 | 10% |

# ማረጋገጫ

ይህ ጥናት የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች የመጻፍ ክሂል ብቃት ትንተና (በቀርሳ ማሊማ ወረዳ፣በሌማን ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተተኳሪነት) በሚል ርዕስ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ ኮሚዩኒኬሽንና ጋዜጠኝነት ኮሌጅ፣ የአማርኛ ቋንቋ ስነጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል የድኅረ- ምረቃ መርሐ ግብር አማርኛን ለማስተማር (TeAm) ማስተር ዲግሪ ማሟያ የቀረበው ጥናት፣ የራሴ ወጥ ስራ መሆኑን አረጋግጣለሁ፡፡

ስም፡- ______________________

ፊርማ፡- ______________________

ቀን፡- ______________________